**DSpace Institution**

**DSpace Repository** **http://dspace.org**

Folklore/Cultural Studies Thesis and Dissertations

2019-02-12

# þÿ è È í c - 5 Ø u c C @ “ è $ “ J
# þÿ ` ¬ 4 ¨ p

þÿ è s ¥ 8 u , ® • •

http://hdl.handle.net/123456789/9281

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

ፎክሎር (ባህልጥናት) ትምህርትክፍል

ድህረ-ምረቃ መርሀ ግብር

# የወይባ ጭስ አዘገጃጀት፣ አጠቃቀም ና የጤና ፋይዳ በኬሚሴ ከተማ

በ

የማታእሸት መኮንን

ለፎክሎር የኤም. ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ዋልተንጉስ መኮንን (ዶ/ር)

ጥር፣ 2011 ዓ.ም

ባህር ዳር

ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

ፎክሎር (ባህልጥናት) ትምህርትክፍል

ድህረ-ምረቃ መርሀ ግብር

# የወይባ ጭስ አዘገጃጀት፣ አጠቃቀም ና የጤና ፋይዳ በኬሚሴ ከተማ

በ

የማታእሸት መኮንን

ለፎክሎር የኤም. ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ዋልተንጉስ መኮንን (ዶ/ር)

ጥር፣ 2011 ዓ.ም

ባህር ዳር

ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

ፎክሎር (ባህልጥናት) ትምህርት ክፍል

ድህረ-ምረቃ መርሀ ግብር

# የወይባ ጭስ አዘገጃጀት፣ አጠቃቀም ና የጤና ፋይዳ በኬሚሴ ከተማ

በ

የማታእሸት መኮንን

ጥር፣2011 ዓ.ም

ባህር ዳር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | ስም | ፊርማ |
|---|---|---|
| አማካሪ | --------------------- | ---------------- |
| የውስጥ ፈታኝ | -------------------- | ------------------- |
| የውጭ ፈታኝ | ------------------ | ----------------- |

# ማውጫ

ይዘት ገፅ


አህጽሮተ ቃላት መፍቻ .......... IV

አበርክቶ .......... V

ምስጋና .......... VI

አጠቃሎ .......... VIII

ምዕራፍ አንድ .......... 1

1. መግቢያ .......... 1
   1.1. የጥናቱ ዳራ .......... 1
   1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት .......... 2
   1.3. የጥናቱ ዓላማ .......... 3
   1.4. የጥናቱ ወሰን .......... 3
   1.5. የጥናቱ ፋይዳ .......... 3
   1.6. የጥናቱ አደረጃጀት .......... 4

ምዕራፍ ሁለት .......... 5

2. ክለሳ ድርሳናት .......... 5
   2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት .......... 5
   2.2. ጽንሰ ሃሳብ ዳሰሳ .......... 7
      2.2.1. ባህላዊ እጥነት .......... 7
      2.2.1. የዕጽዋት እጥነት .......... 10
      2.2.2. ክዋኔ .......... 13
      2.2.3. አውድ .......... 15

ምዕራፍ ሶስት .......... 19

3. የጥናቱ ዘዴ .......... 19
   3.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች .......... 19
      3.1.1 ምልከታ .......... 20
      3.1.2 ቃለ መጠይቅ .......... 22
      3.1.3 ተተኳሪ ቡድን ውይይት .......... 24

3.2. የመረጃ አቀባዩች ምልመላ ........................................................................................................24
3.3. የመረጃ መቀንበቢያና መተንተኛ ዘዴ ..........................................................................................25
3.4. የመስክ ተሞክሮ ዘገባ ..................................................................................................................26
3.5. ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሂዎቻቸው ....................................................................................30

ምዕራፍ አራት .................................................................................................................... 31

4. የኬሚሴ ማህበረሰብ አካባቢያዊ ገጽታና ማህበረ -ባህላዊ ዳራ .....ERROR! BOOKMARK NOT DEFINED.
4.1. የኬሚሴ ከተማ አጠቃላይ ገጽታ...................................................................................................32
4.2. የጋብቻ ሥነ-ስርዓት ..................................................................................................................33
4.3. ባህላዊ የአለባበስና አጊያጊያጥ ስርአት ......................................................................................34
4.4. ባህላዊ ምግቦች..........................................................................................................................35

ምዕራፍ አምስት ................................................................................................................. 38

5. የመረጃ ትንተና .................................................................................................................. 38
5.1. የወይባ ጭስ ምንነት ....................................................................................................................38
5.2. የማጠኛ ቁሳቁሶችና ውክልናቸው...............................................................................................40
5.2.1.የወይባ እንጨት በእጥነት ውስጥ.......................................................................................40
5.2.2. ቦለቅያ በእጥነት ውስጥ .....................................................................................................41
5.2.3. ለጋ ቅቤ በእጥነት ውስጥ ...................................................................................................43
5.2.4. ጀንዲ (ከሌ) በእጥነት ውስጥ...............................................................................................45
5.3. የወይባ ጭስ አዘገጃጀት ..............................................................................................................46
5.4. የወይባ ጭስ እጥነት የሚከወንባቸው አጋጣሚዎች .....................................................................48
5.4.1. የወይባ ጭስ እጥነት በጫጉላ ቤት.....................................................................................48
5.4.2. የወይባ ጭስ እጥነት በአራስ ቤት......................................................................................52
5.4.3. የወይባ ጭስ እጥነት በአዘቦት............................................................................................54
5.5. የወይባ ጭስ አሚሚቅ ስርአት.......................................................................................................59
5.6. በወይባ ጭስ የመታከም ፋይዳ.....................................................................................................61
5.6.1 የወይባ ጭስ ፈውስ..................................................................................................................61
5.6.1.1. ለአካላዊ ፈውስ.................................................................................................................62
5.6.1.1.1 ሰውነትን ከማጠንከር......................................................................................................62
5.6.1.1.2. አለስፈላጊ ፈሳሾችን በማድረቅ በሽታዎችን ማከም.........................................................63
5.6.1.1.3. የሰውነት ጠረንን ለመቀየር ..............................................................................................65
5.6.1.2. ስነ-ልቦናዊ ፈውስ............................................................................................................66

5.6.1.3. ውልደትን ማፋጠን ......67

ምዕራፍ ስድስት ...... 70

6. ማጠቃለያና ይሁንታ ...... 70

6.1. ማጠቃለያ ......70

6.2. ይሁንታ ......71

ዋቢ ጽሑፍ...... 73

አባሪ ...... 77

# አህጽሮተ ቃላት መፍቻ

- የኬ.ከ.ባ.ቱ.ጽ/ቤት = የኬሚሴ ከተማ ባህል ቱሪዝም ጽህፈት ቤት፡፡
- የኬ.ከ.ን.ኢ.ል.ጽ/ቤት = የኬሚሴ ከተማ ንግድ ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት፡፡
- የኬ.ከ.ገ.ኢ..ል.ጽ/ቤት = የኬሚሴ ከተማ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት፡፡

# አበርክቶ

ይህ ሥራ መታሰቢያነቱ እኔ ተምሬ የተሻለ ሕይወት እንዲኖረኝ አስባ ልጆቼን ለመያዝ ከወረኢሉ ከተማ እኔ ወደ ምኖርበት ወደ ደሴ ከተማ መጥታ ስትመለስ በመኪና አደጋ ሕይወቷ ላለፈው ለውዷ እህቴ ኮኮቤ አጥሌ ይሁንልኝ::

# ምስጋና

ይህ ጥናት ከዚህ እንዲደርስ ርዕሱን ከማቃናትና የሆሄያትን ግድፈት ከማረም  አንስቶ እያንዳንዱን ችግር በማሳየትና በማስተካከል፣ ለመረጃ የሚሆኑ ምንጮችን  ያለመሰልቸት በመጠቆም፣ ውድ ጊዜያቸውንንና እውቀታቸውን ለአካፈሉኝ ለአማካሪዬ፣ ለዶክተር ዋልተንጉሥ መኮንን ከፍ ያለ የከበረ ምስጋናዬን ላቀርብላቸው እወዳለሁ።

በዚህ ትምህርት መርሃ ግብር እንድማር እድሉን ለሰጠኝ ለአማራ ሴቶች ፌደሬሽን ምስጋናየ የላቀ ነው። የወር ደመወዜን እየከፈለ ላስተማረኝ  ለደሴ ከተማ አስተዳደር እና ለደሴ ከተማ ሴቶች ህጻናት መምሪያ  የተለየ ምስጋና አለኝ።

ኃይለማርያም ፣ ምን ብየ እንደማመሰግንህ አላውቅም። በደረሰብኝ ፈተና ሁሉ ከጎኔ ሆነህ ለእኔ መለወጥ አንተ ደክመህ፣ ከአንተ አልፎ ቤተሰቦችህን አስቸግረህ በሃሳብ፣ በገንዘብህ ሁሉ ላደረክልኝ እገዛ አምላክ ብድሩን ይክፈልህ እንጅ ሌላ ምን እላለሁ፤

ብቸኛው ወንድሜ፣ ሲሳይ ብርሃን፣ ታናሽ ሳለህ እንደ ታላቅ ለችግሮቸ ሁሉ ማለፊያ እየቀየስክ ከጎኔ ሳትለይ ለዚህ አብቅተኸኛል። በተደናገረኝ ሰዓት፣ በገንዘብም ሆነ በሃሳብ ላደረክልኝ ነገር ሁሉ ፈጣሪ አንተን፣ አንዱን ብዙ ያድርግልኝ። ከልጆችህ ፒሎፓደርና ቲዩብስታ ጋር እድሜ ከጤና ጋር አብዝቶ ይስጥልኝ እላለሁ። ባለቤትህ ህይወት ደረጀም ለኔ ስኬት  ያለመሰልቸት ደክማለች። ልጅ እናት ባጣችበት ወቅት እናት በመሆን ፣ አዛውንት እናቴን በመንከባከብ ላደረግሽልኝ ድጋፍ ሁሉ ምስጋናየ ከፍ ያለ ነው።

እናቴ ወ/ሮ ተዋበች መንግስቴ፣ እናትም አባትም ሆነሽ  በእሳት ተቃጥለሽ ለቁምነገር ማብቃትሽ ሳያንስ፣ አሁንም ለእኔ በማሰብና በመጨነቅ ዘወትር ደስታየን ስትመኝ ኖርሽ አሁን፣ ሁሉም ሊያልፍ ነው መሰል ፈጣሪ እረጅም እድሜና ጤና ይስጥልኝ ።

የእናት ፍቅር አጥታችሁ በያለበት ተበትናችሁ የእኔን ስኬት ለጠበቃችሁት ልጆቼ፣ ማትያስ ክበር እና ሚሮን ክበር፣ ምንጊዜም ምኞቴ የናንተን ጥሩ ነገር ማየት ነው። ልጀ ከኔ ጋር አብረሽ መንከራተትሽ፣ ሊያበቃ ነው እደጉልኝ።

ይህን ጥናት ለዚህ እንዲደርስ የምፈልገውን መረጃ ሁሉ በመስጠት ያለመታከት ለረዳችሁኝ መረጃ አቀባዩቸ የከበረ ምስጋና አቀርባለሁ ። በዋልኩበት ውላችሁ በሄድኩበት ሄዳችሁ የተሻለ መረጃ እንዳገኝ በማድረግና መንገድ በማመላከት ለደከማችሁት አይናለም ሰይድ እና ሙሃመድ አህመድ ከልብ አመሰግናለሁ ።

<<ከፍትፍቱ ፊቱ >> እንደሚባለው ቤትሽን እንደ ቤቴ እንዳይ፣ የምፈልገውን ሁሉ አድርገሽ ከኔ ጋርወጥተሽ ወርደሽ በገንዘብሽም በሃሳብሽም ለደገፍሽኝ ጓደኛየ፣ ሽቶ ነጋ አምላክ ዋጋሽን ይከልልኝ። ከቤተሰባችሁ እንደ አንድ አይታችሁ ስትቀበሉኝ ለነበራችሁ ልጆቿ ዘመድ አብዱሮህማን፣ ተስፋየ ጌታቸው፣ ካሌብ ሃብተ ከልብ አመሰግናለሁ።

አቶ ዑመር ሰይድ የኬሚሴ ከተማ ባ.ቱ.ጽ/ቤት ኃላፊና ባለሙያዎች  ከአቀባበላችሁ ጀምሮ የምፈልጋቸውን የመቅረጫ ቁሶች በመዋስ ፣ መንገድ መሪ  ፣ የታተሙ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበራችሁኝ ለኬሚሴ ከተማና ለዞን ባህል ቱሪዝም ሰራተኞች፣ ኮሚኒኬሽን ሰራተኞች፣ ለአቶ ስነ ጊወርጊስ፣ ለአቶ ግሩም ተሰማ አመሰግናለሁ።

ከጎኔ ሆናችሁ የችግሬ ሁሉ መሸፈኛ ለነበራችሁት የክፍል ጓደኞቸ ማህሌት ዘነበ እና አንተነህ ብርሃኑ ምስጋናየ ከፍያለ ነው። በሃሳብ በማበረታታትና የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በማፈላለግ ላገዛችሁኝ ጓደኞቸ ለይኩን ሲሳይ፣ መለሰ ዝናቡ፣ ምህረትአብ እስጢፋኖስ፣ አብዱል አዚዝ ጌታቸው፣ ኑሩ በዛብህ፣ ሙሃመድ ፈንታው፣ ምሳየ ከድር፣ አወቀ መንግስቴ፣ አገሪቱ አሻግሬ ፣ ሂሩት ደመቀ፣ እንዲሁም፤ ከጎኔ ሆናችሁ ስታበረታቱኝ፣ ስትደግፉኝ ለነበራችሁ ጓደኞቸ በሙሉ እጅግ አመሰግናለሁ።

በአጠቃላይ ወደር የሌለው እውቀታችሁን  ሰጥታችሁ ለዚህ ያበቃችሁኝ  መምህሮቸ ዶክተር ዋልተንጉሥ መኮንን ፣ ዶክተር አስቴር ሙሉ፣ ዶክተር ጥላሁን በጅቷል ምስጋናየ ከፍ ያለ ነው።

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት፣ በኬሚሴ ከተማ ማህበረሰብ ዘንድ ተዘውታሪ የሆነውን በወይባ ጭስ የመታጠን ባህል ጤናን መሰረት አድርጎ የመረመረ ነው። የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት የወይባ ጭስ የሚከወንባቸውን አጋጣሚዎች ለይቶ መመርመር፣ ለማጠኛነት የሚውሉ ቁሶችን ተምሳሌታዊ ውክልና ማሳየት፤ እጥነቱ ለአካል፣ ለመንፈስና ለህሊና የሚሰጠውን ጥቅም መግለጽ የሚሉ ንዑሳን ዓላማዎችን አካቷል። እነዚህን ዓላማዎች መሰረት ያደረጉ መረጃዎች ከቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች በኢትኖግራፊያዊ ዘዴ ተሰብስበዋል።

በጥናቱ የኬሚሴ ማህበረሰብን ይወክላሉ የተባሉ ሦስት ቀበሌዎችን በመምረጥ፣ አንድ የገጠር ቀበሌ ቀበሌ ሰባት እንዲሁም ሁለት የከተማ ቀበሌዎች ቀበሌ ሦስትና ቀበሌ ስድስት ላይ መሰረት በማድረግ የመስክ መረጃዎችን በተፈጥሯዊ መቼታቸው ሦስት አይነት አጋጣሚዎችን መሰረት ባደረገ ምልከታ እንዲሁም በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ከሃያ ሁለት መረጃ አቀባዮች ተሰብስቧል።

በመረጃ ትንተናው የወይባ ጭስ ምንነት፣ አዘገጃጀት ፣ አሚሚቅና የወይባ ጭስ የሚሞቅባቸው አጋጣሚዎች ሦስት እንደሆኑ አሳይቷል ። እነዚህም የጫጉላ ቤት እጥነት፣ የአራስ ቤት እጥነት ፣እና የአዘቦት እጥነት ናቸው። በእነዚህ አጋጣሚዎች ጭስ የሚሞቁ ጾታዊ ግንኙነት የጀመሩ ሴቶች እንደሆኑ በጥናቱ ተመላክቷል ።በተጨማሪም በወይባ ጭስ እጥነት ፋይዳው አካላዊና ስነልቦናዊ ህመሞችን መፈወሻና ውልደትን /መራባት/ ማፋጠኛ ዘርን ማስቀጠያ አድርገው የሚጠቀሙበት ስለመሆኑ ተደርሶበታል።

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የሰው ልጅ በህይወት ሲኖር ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቱን ለማሟላት የሚተገብራቸው ልማዶች አሉት።ፈ.ቃደ(1991) እነዚህን ልማዶች የሚከውናቸው ማህበረሰቡ እንደራሱ እምነታዊ ቀኖና ቀምሮ ፣ ልማድ አበጅቶ ፣ ማህበራዊ ሕግ መስርቶ፣ ከአካቢያዊ ሁኔታ፣ ከኢኮኖሚያዊ ፍላጎት፣ ከስነ-ልቦናዊ መልክ፣ ወ.ዘ.ተ ጋር አስተሳስሮ ያሰርጻቸዋል። ልማድ በዘመን ሂደት ትውልድ ተሸጋሪ የሆነና ትውልድ ሥርዓት አበጅቶ የሚቀባበላቸው ናቸው። ይህንን በተመለከተ Dorson (1972፡3) "ሃገረሰባዊ ልማዶች ማህበረሰቡ ካለፈው ትውልድ የወረሳቸው እና አንደኛው ለሌላኛው በክዋኔ አማካኝነት የሚያሳተላልፋቸው የፎክሎር ዘርፎች ናቸው" በማለት ይገልጿቸዋል።

ልማድ ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ ለመኖር፣ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ህግ ለማበጀት፣ ከችግሮች ለማምለጥ እና ስነ-ልቦናዊ ጫናን ለመቀነስ ፣ ስሜትን ለማርካት ማህበረሰቦች ባህላዊ የመቆጣጠሪያ ዘዴ አድርገው የፈጠሯቸውና በተደጋጋሚ የሚያከናውኗቸው ተግባሮች ናቸው። ልማዶች ከእምነት፣ ከዘመን፣ ከማህበራዊ ማንነት አንጻር የተያያዙ ተግባሮች አሏቸው። በመሆኑም፣ ችግርን እንደመወጫነት ሲጠቀሙባቸው የየልማዶቹ ተግባራት፣ አይነት እና የመተላለፊያ መንገዱም የተለያየ ነው። በዓለም ላይ የሰው ልጅ በተደጋጋሚ ከሚገጥሙት እንደሃዘን፣ መከራ፣ ቁጣ፣ ህመም፣ ጭንቀትና ፍርሃትን የመሳሰሉ ነገሮች የሚያመልጥበት፣ የሚጽናናበት፣ ፈውስን የሚያገኝበት የማከሚያ ስርአቶች አሉት።

ባህላዊ ልምዶች በመዝፈን፣ በመጨፈር፣ በመልበስ፣ እንፋሎት በመታጠን እና ጭስ በመታጠን ወዘተ የሚከወኑ ናቸው። Dorson (1972፡245 ይሁን እንጅ የየልማዶቹ ፋይዳ እንደየ ማህበረሰቡ እምነት ሁኔታ ይለያያል። ለምሳሌ፡- በአሜሪካ የሚኖሩ ፊላንዳውያን ባህላዊ የእንፋሎት እጥነት ልማድን ውበትን ለመጠበቂያነት በተጨማሪም አዕምሮንና መንፈስን ለማንጻትም ያዘወትሩታል። ከእነዚህ ተግባሮች ጎን ለጎን ማህበረሰቡ የማንነቱ ማሳያ (identity) አድርጎ ይገለገልባቸዋል። ይህ ልማድ የገላን ዕድፍ ከማስወገድ በዘለለ የነፍስን ፅዳት(ንጽኸት) ያመጣል በሚል እምነት እየተከወነ ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ የመጣ

ነው። የመንፃት ስርዓቱ አላማም ሰውነትን ለማጽዳት ብቻ ሳይሆን አእምሮን እና መንፈስን ለማንፃት ጭምር ነው LockWood.( 1981: 309) ።

የእንፋሎት እጥነት ፊላንዳውያን የሰውነትን ጡንቻ ከማፍታታት ባለፈ ከተለያዩ ስነልቦናዊ ጫናዎች ፋታ ለማግኘትና ለባህላዊ ህክምና እንደሚጠቀሙበት የተለያዩ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡ Mesfin (1997)። በተጨማሪም፣ ጭስ የመታጠን ልማድን በአንዳንድ ባህሎች ዘንድ የማህጸን ጤንነትና ንጽህናን ለመጠበቅ ሲጠቀሙበት ይስተዋላል። ከዚህ አንጻር የኢንዶኔዥያ ህዝቦች የሴትነት ጣጣቸውን ማለትም እንደ ወርአበባ፣ እርግዝና፣ በወሊድ ጊዜ የሚደርሱባቸውን ጫናዎች ለመፈወሻነት ይጠቀሙበታል። Dioszegi (1981: በተጨማሪም በፊኒሽ አሜሪካውያን በሳውና እጥነት ሂደት ጥሩ መአዛ ያለውና (vita በሚል ስያሜ የሚጠራውን) የዛፍ ቅርንጫፍ እሳት ላይ *በመ*ጨመር እና በመታጠን ከተለያዩ በሽታዎች ይፈወሱበታል በማለት ይገልጻሉ።LockWood.( 1981፡307) በመሆኑም፣ ይህ ልማድ በተለያዩ ሀገራት የተለያየ ፋይዳ ይዞ ይከወናል።

በመሆኑም፣ በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገበት፣ የህገረሰባዊ ልማድ አካል የሆነውን የወይባ ጭስን የመታጠን ልማድ ነው። ይህ ልማድ በአማራ ክልል በኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር በኬሚሴ ከተማ ማኅበረሰብ ጾታዊ ግንኙነት በጀመሩ ሴቶች ትኩረት ተሰጥቶ የሚተገበረውን የወይባ ጭስን አዘገጃጀት፣ አጠቃቀምና የጤና ፋይዳ መርምሮ የሚያሳይ ይሆናል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የኬሚሴ ከተማ ማህበረሰብ የሚከውናቸው በርካታ የፎክሎር ሃብቶች አሉት። ከበርካታዎቹ መካከል የወይባጭስ አዘገጃጀት፣ አጠቃቀምና የጤና ፋይዳ በሚል ርዕስ ላይ ትኩረት ማድረግን መርጫለሁ፤ ለዚህም ሁለት ምክንያቶች አነሳስተውኛል። የመጀመሪያው ከርዕስ አንጻር በተለያዩ ጽሁፎች እንዳነበብኩትና ከሰዎች እንደሰማሁት የወይባ ጭስ እጥነት በአሁኑ ሰዓት የሴቶችን ህይወት በመቅጠፍ ላይ ያሉ እንደ ኢንፌክሽን፣ የማህጸን ካንሰርና የመሳሰሉ በሽታዎች እንዳይከሰቱ የቅድመ መከላከያ መንገድ በመሆን እንዲሁም ንጽህናን በማምጣትና በሽታ አምጭ ተህዋሲያንን በማጥፋት ለተለያዩ በሽታዎች ቅድመ መከላከል ይሆናል የሚል እምነት ስላለኝ ሲሆን፣ ሁለተኛው ምክንያት ከቦታ አንጻር ያለው ኬሚሴ ከተማ እኔ ካለሁበት ቦታ ቅርበት ስላለውና ልማዱ በስፋት የሚከወንበት ቦታ በመሆኑ

ትክክለኛውን የጭስ እጥነት ፋይዳ የሚያሳይ መረጃ ማግኘት ስለሚያስችለኝ ባህሉን ሰንዶ ለማቆየት እንዲሁም ለሌሎች ለማስተዋወቅ ጉጉት ስላደረብኝ ነው።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኬሚሴ ከተማ የወይባ ጭስ አዘገጃጀት፣ አጠቃቀምና ለጤና የሚኖረውን ፋይዳ ማሳየት ነው። በመሆኑም፣ ጥናቱ በዚህ ዋና ዓላማ ላይ ተመርኩዞ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች መልሷል ።

- የወይባ ጭስ የእጥነት ሥርዓት የሚከወንባቸውን አጋጣሚዎች መመርመር ፣
- እጥነቱ ለአካል፣ ለመንፈስና ለህሊና የሚሰጠውን ጥቅም ማሳየት
- የወይባ ጭስን ለመታጠን የሚውሉ ቁሶችን ተምሳሌታዊ ውክልና ማሳየት ናቸው

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር የወይባ ጭስ አዘገጃጀት፣ አጠቃቀምና የጤና ፋይዳ ማሳየት ነው። ለዚህም የወሊድ፤ የጫጉላ ቤትና የአዘቦት አጋጣሚዎችን የሚያካትት ነው። ከቦታ አንጻር ደግሞ በአማራ ክልል በኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር ዋና ከተማ ኬሚሴ ከሚገኙ ሰባት ቀበሌዎች መካከል በሶስት ቀበሌዎች (ቀበሌ ሶስት፣ ስድስት እና ሰባት) ላይ የተወሰነ ነው። እነዚህ ሶስት ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያት ለዚህ ጥናት ዋናውን መረጃ (Originality) ለማግኘት ምቹ በመሆናቸውና የወይባ ጭስ ተጠቃሚዎች በብዛት የሚኖሩባቸው ሰፈሮች ስለሆኑ ነው።

## 1.5. የጥናቱ ፋይዳ

የአንድ ማህረሰብ የፎክሎር ሀብቶችን ማጥናትና መሰነድ ለባለቤቱ፣ ለሌላው ማኅበረሰብና ለአጥኚዎች በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል። በእኔ ዳሰሳ ወይባ ጭስን ለማህበረሰቡ ባለው በባህላዊ መድኃኒትነት ዙሪያ የተጠና ጥናት አላገኘሁም። በመሆኑም፣ ይህ ጥናት የሚከተሉት ፋይዳ ይኖሩታል፡-

- የወይባ ጭስ የሚኖረውን የጤና ፋይዳ በማሳየት እንደ አንድ የበሽታ ቅድመ መከላከያ መንገድ ትኩረት እንዲሰጠው ያደርጋል፤
- በወይባ ጭስና በሌሎች የማህበረሰቡ ባህላዊና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ጥናት ለሚያካሂዱ ተመራማሪዎች ግብዓት በመሆን ያገለግላል፤

- የአካባቢው ማህበረሰብ ከትውልድ ትውልድ ሲያስተላልፈው የቆየውን ባህሉን በጽሁፍ መሰነዱ የማህበረሰቡ ልማድ ትኩረት ተሰጥቶት የበለጠ እውቅና እንዲያገኝ ያደርጋል፤
- አካባቢውና ማህበረሰቡ በህክምና ቱሪዝም ተጠቃሚ እንዲሆን በር ሊከፍት ይችላል::

## 1.6. የትናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት፣ በኬሚሴ ከተማ ማህበረሰብ ዘንድ ተዘውታሪ የሆነውን በወይባ ጭስ የመታጠን ባህል ለመመርመር የተካሄደ ሲሆን፣ በውስጡ ስድስት ምዕራፎችን ይዞ ቀርቧል። በመጀመሪያው ምዕራፍ አምስት ርዕሰ ጉዳዮች የተዳሰሱ ሲሆን የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ ዋና አላማ ፣የጥናቱ ወሰንና ጥናቱ የሚያስገኘው ፋይዳ፣ የጥናቱ አደረጃጀት በሚል ተጠናቅሯል።

በምዕራፍ ሁለት፣ በወይባ እና በባህላዊ መዋቢያ መድሃኒቶች ዙሪያ የተሰሩ ተዛማጅ የመመረቂያ ጽሁፎች፣ ንድፈሃሳቦችና ጽንሰ ሃሳቦች ተዳስሰዋል። ከዚያም፣ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ንድፈ ሃሳቦችና ጽንሰ ሃሳቦች በመስኩ ምሁራን በተሰጡ ሃሳቦች መሰረት ተቃኝተዋል።

በሶስተኛው ምዕራፍ ደግሞ፣ የጥናቱ ስነዘዴዎች በሚል፣የጥናቱን መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ፣የናሙና አመራረጥ ፣የመረጃ መቀንበቢያና መተንተኛ ዘዴ፣የመስክ ተሞክሮ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች ቀርበውበታል።

በአራተኛው ምዕራፍ በጥናቱ አካባቢ ገጽታና ዳራ ዙሪያ መግለጫ ቀርቦበታል፡ ኢኮኖሚያዊ፣ ኃይማኖታዊ በአጠቃላይ ከጥናቱ ጋር ቀጥታም ሆነ ኢቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውንና ማህበረሰቡን የሚገልጹ ሀቆች የተገለጹበት ነው።

በአምስተኛው ምዕራፍ፣ ጥናቱ በተካሄደበት ቦታ የወይባ ጭስ ምንነት፣ የማጠኛ ቁሶችና ውክልናቸው ፣ የወይባ ጭስ አዘገጃጀት፣ የወይባ ጭስ መታጠን የሚከወንባቸው አጋጣሚዎች፣ የወይባ ጭስ ፋይዳ፣ ትንተና ተሰጥቶባቸዋል። በምዕራፍ ስድስት፣ በጥናቱ የተደረሰበት ግኝት መሰረት ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳብ የተካተተበት የመጨረሻ ክፍል ነው ።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ክፍል ሁለት ጉዳዮች ተዳስሰውበታል፡፡ በመጀመሪያው ንዑስ ርዕስ፣ ከጥናቱ ጋር በተወሰነ መልኩ ተያያዥነት ያላቸው ቀደምት ጥናታዊ ጽሁፎች ተቃኝተዋል፡፡ የፅንሰ ሀሳብ ዳሰሳን አስመልክቶ ባህላዊ እጥነት፣ የመታጠን አይነቶች ፣ የእጽዋት እጥነት፣ ክዋኔ ምንነት፣ አውድ የሚሉት ሃሳቦች ተቃኝተዋል፡፡ የንድፈ ሀሳብ ዳሰሳ በተመለከተ ከጥናቴ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በመረጃ መተንተኛነት ዝምድና ያለው ተግባራዊ ቲወሪ በመስኩ ምሁራን የተሰጡት ብያኔዎች ተዳሰውበታል፡፡

## 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከእኔ የምርምር ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በቂ ቀደምት ጥናቶች አላገኘሁም፡፡ ይሁን እንጂ በኬሚሴ ማህበረሰብ አለባበስና አጊያጊያጥ ላይ እና በተለያዩ ቦታዎች የተጠኑ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ሁለት የሁለተኛ ድግሪ የማሚያ ጽሁፎች ተቃኝተዋል፡፡

በቅድሚያ ይህ ጥናት በሚያተኩርበት የኬሚሴ ማህበረሰብ ላይ የተሰራው ጽሁፍ ይዳሰሳል፡፡ ይህ እንዲሆን የተፈለገበትም ምክንያት ማህበረሰቡን የተመለከቱ መረጃዎችን አስቀድሞ መገንዘብ ተገቢ ነው በሚል ነው፡፡ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ባደረኩት አሰሳ በዚህ ማህበረሰብ ላይ የተጠኑ ጥናቶች ባላገኝም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟሙያ የተሰራው የሰይድ ይማም ጥናት የዳሰሳው አንዱ አካል ነው፡፡

**ሰይድ ይማም** (2002 )‹‹በኬሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ገጠር ቀበሌዎች የወጣት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ ፎክሎራዊ ገፅታ›› በሚል ርዕስ ያጠናው ጥናት፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተሰራ ነው፡፡ በጥናቱ በከሚሴ ዙሪያ አምስት የገጠር አካባቢዎች ወጣት ወንዶችና ሴቶች የሚለብሷቸውን ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦችን ምንነት፣ አገልግሎትና ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ የመረመረ ነው፡፡ በጥናቱ የተዳሰሱ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ሲሆኑ፣ በተለይም ሴቶች ከመታጨታቸው በፊት፣ በሚታጩበት ወቅትና ካገቡ በኂላ በሚለበሷቸው ስድስት አልባሳትና አሥራ አምስት ጌጣጌጦች

ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት የሰበሰባቸውን መረጃዎች በገላጭ የምርምር ዘዴ ተንትኗቸዋል፡፡

የሰይድ እና የእኔ ጥናት የሚገናኘው ከተሰራበት ቦታ አንፃር እና በተጠቀምናቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ነው፡፡ ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር የእኔ ጥናት የወይባ ጭስን አዘገጃጀት አጠቃቀምና የጤና ፋይዳ መርምሮ ማሳየት በመሆኑ ከእኔ የሚለይበት ነው፡፡

ሁለተኛው ጥናት **ማርታ እሸቱ** (2001) ‹‹ወይባ ባህላዊ የሴቶች መዋቢያ በወሎና በአዲስ አበባ›› የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተሰራ ነው፡፡

የጥናቱ አላማ በወሎ አራት አካባቢዎች ማለትም ባቲ፣ ኮምቦልቻ፣ ሃርቡና ኬሚሴ እንዲሁም በአዲስ አበባ በተመረጡ አራት ባህላዊ የውበት ሳሎኖች ያለውን የወይባ ጢስ አሟሟቅ በማሳየት በሁለቱ አካባቢዎች የሚታየውን ተመሳሳይነትና ልዩነት በማነጻጸር ያሳየ ነው፡፡ በሁለቱ አካባቢዎች ያለውን የወይባ ጭስ አሟሟቅ ስርአት ለማነጻጸር

በኮምቦልቻ፣ ሃርቡ፣ ባቲና ኬሚሴ ውስጥ ያሉ ሴቶች ወይባ ጭስ እንዴት እንደሚሞቅ ባህላዊ ስርአቱን ማሳየት፣ በወሎ ያሉ የጭሱ ተጠቃሚዎች መዋቢያው የሚሰጠውን አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ ማሳየት፣ በአዲስ አበባ ወይባ ጭስ የሚሞቅባቸውንባህላዊ የውበት ሳሎኖች አሟሟቅ ስርአት ማሳየት፣ አዲስ አበባያሉ የጭሱ ተጠቃሚዎች ከመዋቢያው የሚያገኙትን አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ ማሳየት፣በወሎና በአዲስ አበባ ያለውን የወይባ የጭስ በንጽጽር በማቅረብ ልዩነትን አንድነቱን ማሳየት የሚሉ ዝርዝር አላማዎችን ነድፋለች፡፡

ማርታ እነዚህን ዘርዝር አላማዎች ከግብ ለማድረስ መረጃዎችን በምልከታና በቃለ መጠይቅ ሰብስባለች፡፡ ማርታ የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝትና የንድፈሃሳብ ዳሰሳ አድርጋለች፡፡ በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በእርሷ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተሰራ ጥናት እንዳላገኘች ገልጻ፣ በተወሰነ መልኩ የሚቀራረብ አንድ ጥናት ተቃኝቷል ፡፡

የማርታ ጥናት ወይባ በባህላዊ መዋቢያነት ለሴቶች የሚሰጠውን ፋይዳ በማሳየትና በወሎና አዲስ አበባ ያለው የወይባ ጭስ አሟሟቅ ሥርዓት ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት ያሳየ ነው፡፡ በዚህ ጥናት እንደ ጉድለት ካየኋቸው አንዱ በጥናቷ ያካተተቻቸው አካባቢዎች በርካታ ከመሆናቸው የተነሳ የአንዱ አካባቢ ዳራዊ መግለጫ በሌላው ተውጦ ለማለፍ መሞከሩ ነው፡፡ ሌላው፣ ለእኔ እንደ እጥረት የታየኝ በወሎና አዲስ አበባ ያለውን የወይባ ጭስ መታጠን ልማድ

አንድነትና ልዩነት የሚያሳይ መረጃ ለመሰብሰብ በየአካባቢያቸው የተተኳሪ ቡድን አለመጠቀሟ ነው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ ያየሁት ክፍተት ጥናቱ የተቃኘበት ንድፈሃሳብ በግልጽ የተጠቀሰ አለመሆኑ ነው፡፡

ማርታ የወይባ ጭስን ለሴቶች ውበት መጠበቂያነት ያለውን ፋይዳ አሳይታለች፡፡ ይህንንም አስመልክታ በይሁንታ ሃሳቧ ለተከታይ አጥኝዎች ለመድሃኒትነት የሚሰጠው ፋይዳ ቢጠና አስተዋጽኦ እንዳለው አመላክታለች፡፡ በመሆኑም፣ የእኔ ጥናት ሙሉ በሙሉ ያተኮረበትን አካባቢ በናሙናነት ማካተቷ የሚያመሳስለን ቢሆንም፣ የእኔ ጥናት የወይባ ጭስን አዘገጃጀት፣አጠቃቀም በማሳየት የፈውስ ፋይዳውን በጥልቀት የሚመረምር በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል፡፡

## 2.2. ጽንሰ ሃሳብ ዳሰሳ

በዚህ ክፍል ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸውን ጉዳዩችን የሚመለከቱ ጽንስ ሃሳቦች በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን ከጻፏቸው ውስጥ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና ጽንሰ ሀሳቦች ምንነትን መግለጽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በመሆኑም፣ ባህላዊ እጥነት ፣የመታጠን አይነቶች ፣ የዕጽዋት እጥነት፣ ክዋኔ እና የአውድ ምንነትና አይነቶች የሚሉ ጽንሰ ሐሳቦች ተዳስሰውበታል፡፡

### 2.2.1. ባህላዊ እጥነት

በባህላዊ ዘዴ በእንፋሎት ሙቀት የመታጠን ልማድ ጥንታዊና በተለያዩ ባህሎች ሲፈጸም የኖረ ነው Dioszegi (1981: 244) ፡፡ ይህ ድርጊት ቆሻሻን በላብ መልክ በማስወጣት ንጽህናና ጤንነትን የመጠበቅ ተግባር ነው፡፡ lockwood (1981;309 ) እንዳሉት በፊላንድ ባህላዊ እጥነት አዕምሮን ለማዝናናት፣ ውበትን ለመጠበቅና አካላዊ ጥንካሬን ለማምጣት ሲያገለግል በጃፓን ደግሞ በተለያዩ ነፍሳት ሲነከሱ እንደመድሃኒ ይጠቀሙበታል፡፡ በመሆኑም ባህላዊ የመታጠን ልማድ በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ያለው አሰራር ክዋኔና ተምሳሌታዊ ትርጉም አንደተጠቃሚ ማህበረሰብ አኗኗር ዘይቤ የሚለይ ሲሆን፣ አተገባበሩና ተደራሽ ግቡ የተለያየ መሆኑን ያሳየናል፡፡ በዚህ ጥናት ግን ማህበረሰቡ የወይባ ጭስ እጥነትን ከተለያዩ በሽታዎች ለመፈወስና ቀድሞ ለመከላከል በመዋል አካላዊና ስነልቦናዊ ፈውስ የሚያገኙበት ልማድ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ለዚህ ነው ወይባ ጭስ መታጠንን አንዳንዱ ማህበረሰብ ለተዝናኖት፣

ማህበራዊ ችግር መፍቻ፣ ለውበት ቅድሚያ በመስጠት ሲጠቀምበት፣ በኬሚሴ አካባቢ ግን ውበት ተዛመጅ ጠቀሜታው አድርጎ በዋናነት በመድሃኒትነቱ ይጠቀሙበታል፡፡

‹‹Sauna have been used for many years as away to relax and improve the bodies look and feel…. They leave the skin soft, supple and glowing in short healthey›› .lockwood (1981;306 ) ባህላዊ የእንፋሎት ፣ ተጠቀሚ ሰዎች ለመዝናናት አካላቸውንና ገጽታቸውን ለማሳመር ሲጠቀሙበት የኖሩት ዘዴ ሲሆን ተግባሩም፣ የቆዳን ልስላሴ፣ ተጣጣፊነትና ፍካት በአጠቃላይ ጤነኛ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ባህላዊ የእንፋሎት እጥነት ለውበትና ለንጽህና የሚጠቀሙበት ቢኖሩም፣ አካልን የማዝናናት ጡንቻን የማፍታታትና የተለያዩ የመገጣጠሚያ ህመሞችን ለመፈወስ፣ በሽታን የመከላከል አቅምን ለመጨመር፣ የአተነፋፈስ ሥርዓትን ጤናማ ለማድረግ፣ ለጤናማ ቆዳና ክብደትን ለመቀነስ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ Lopatin (1960፡977) ፡፡ በመሆኑም፣ አብዛኛውን ጊዜ በተጠቃሚዎቹ የሚመረጠው ግን ለፈውስ ካለው ጠቀሜታ አኳያ ነው፡፡ ሰዎች ወደ እንፋሎት መታጠቢያው በሚገቡበት ሰዓት ከዘወትራዊና ከእለታዊ እንቅስቃሴያቸው ለጊዜው በአካልም በአምሮም ይነጠላሉ፡፡ lockwood (1981;307)፡፡

በዚህ አጋጣሚ ከማህበራዊ ግርግር የመራቅ ስሜት ስለሚሰማቸው ስነልቦናዊ እረፍት ያገኛሉ፡፡ ከዚህ የእረፍትና የመዝናናት ሂደት በኋላ ሰዎች የነፍስ ጽዳት (መንጻት) እንደገና የመታደስ ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ የተጨናነቀና በሃሳብ የተወጠረ አእምሮን ያክማል፡፡ በዚህም፣ የግለሰቦቹ አካላዊና አዕምሯዊ ይዞታ መልካም እንዲሆን ይረዳል በሚል ያስባሉ፡፡ lockwood (1981;307)፡፡

በተጨማሪም፣ በጋራ የሚከወኑ መታጠቢያዎች ውስጥ በጋራ የሚጠቀሙ ሰዎች እርስ በእርስ እንዲተዋወቁና እንዲጨዋወቱ የጠበቀ ማህበራዊ ግንኙነት እንዲፈጥሩ እድል ይሰጣቸዋል በሚል ለማህበራዊ ትስስር የሚያበረክተውን ፋይዳም ያሳያሉ፡፡ clark (1994፡ 106) ለምሳሌ፣ በጥንታዊ ጃፓኖች ባህላዊ መታጠቢያ በተለያዩ እድሜ ክልል ያሉ ሰዎች በጋራ የሚጠቀሙባቸው የህዝብ መታጠቢያዎች (public baths) ይገኛሉ፡፡ ሰዎቹ ወደመታጠቢያ የሚመጡት በቡድን በቡድን በመሆን ነው፡፡ በዚህ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ከአቻቸው ጋር የመጨዋወት የመመካከር ሃሳብ የመለዋወጥ እድል ያገኛሉ፡፡ እርስ በእርስ በሚፈጥሯቸው ቀልዶች ይዝናናሉ፡፡ clark (1994; 106) ፡፡

በዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በባህላዊ መንገድ ለተለያዩ ህመሞች መፈወሻነት ጥቅም በሚውለው የእጥነት አይነት ላይ ሲሆን፣ ይህም በሃገረሰባዊ ልማድ ዘርፎች በሆነው ሃገረሰባዊ መድሃኒት ዘርፍ የሚካተት ይሆናል፡፡

Blum, (2007) and Brown, (2002 ) መታጠንን "የተለያየ እንደሆነ ይገልጻሉ ፡፡ ቀጥተኛ ባዝ (ሀማም) እና በውሀ እንፋሎት ባዝን (the water vapor bath) በመለየት በኩል ችግር ገጥሟቸዋል፡፡ የባዝ አይነቶች ብዙ ናቸው፡፡ የደረቅ አየር ባዝ (dry hot air bath) እና የቀዘቀዘ ውሀ ባዝን (the cold watr bath} ን ጨምሮ ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ዋና ዋና የባዝ (ሀማም) አይነቶችን እንመለከትና እኔ ይገኘ ከተነሳሁት ርዕስ ጋር የሚገናኘውን በትኩረት እንይ ፡፡

## የመታጠን ዓይነቶች

በተለያዩ የአለም ሃገራት እና ህዝቦች የሚከወኑ በርካታ የመታጠን አይነቶች ሲኖሩ፣ አገልግሎታቸውም እንደ አይነታቸው፣ እንደማህበረሰቡ አስተሳሰብና ባህል የተለያየ ነው፡፡ ድርሳናት ዋና ዋናዎቹ የባዝ (ሀማም) አይነቶችን በአራት ይከፍሏቸዋል፡፡ እነሱም **በገንዳ የመጥለቅ ባዝ** (pool or the plung bath) ፣ የቀጥታ የእሳት ነበልባል (ጭስ) በዝ (the dairect fire sweat bath}፣ የውሀ ትነት ባዝ (the water vapor sweat bath} እና ቅይጥ ባዝ (mixed type} ናቸው፡፡ እነዚህን በዝርዝር እንመልከት Lopatin (1960፡ 278)፡፡

**የገንዳ ወይም የመጥለቅ በዝ (ሀማም)** የቆየና በአብዛኛው ተፈጥሮአዊነትን የተላበሰ የመታጠን ዓይነት ነው፡፡ ይህ አይነቱ ባዝ በቀደምት ግብጾች፣ ሰርቦች፣ ፍልስጤሞች ወዘተ ሀገሮች የተለመደ ነው፡፡ ባዙ ይከናወን የነበረበት ቦታ በተፈጥሮ የውሀ አካሎች ተጀምሮ ቀስ በቀስ በመዋኛ ገንዳዎች የተተካ ነው፡፡ ለእኛም ሀገር ይኸው በቀዝቃዛም ሆነ በፍል ውሀዎች እስካሁን እየተደረገ ያለ ነው፡፡ አብዛኛው የዚህ አይነት ባዝ ሚና ለአካላዊ ንጽህና ነበር፡፡ Lopatin (1960፡ 279)፡፡

**የቀጥተኛ የእሳት ነበልባል ባዝ** (the dairect fire sweat bath) ይህ የእጥነት አይነት እንደ መጥለቅ ባዝ ለረጅም ጊዜ ሲተገበር የቆየ ሲሆን፣ እስካሁንም ድረስ በካሊፎርኒያ ህንዶችና ኤስኪሞዎች ወዘተ እንደሚተገበር ይነገራል፡፡ Lopatin ( 1960፡ 278)

የዚህ ባዝ ዋና ዓላማ ሰውነት እንዲያልበው በማድረግ በሙቀት ምክንያት የሚገኘውን እርካታ ለማጣጣም ነበር፡፡ በእርግጥ ኤስኪሞዎቹ በጣም በረዷማ በሆነ ቦታ በመኖራቸው ምክንያት ዓላማው ለአካላቸው ሙቀት ለመፍጠር ነው፡፡ በእኔ ጥናት ላይ የሚታየው የጭስ እጥነት ደግሞ የተለያዩ አካላዊና ስነልቦናዊ ህመሞችን ለመፈወስ የሚውል በመሆኑ ተጠቃሚዎች በአብዛኛው ለጤናቸውና ሲቀጥልም ለተያያዘ የተለየ ዓላማቸው ይጠቀሙበታል፡፡ Lopatin (1960፡ 278) በመሆኑም፣ በዚህ ጥናት ትኩረት የሚደረ ግበት የመታጠን (bath) አይነት ከቀጥተኛ የእሳት ነበልባል ባዝ ጋር የሚቀራረብ ቢሆንም፣ የእኔ ጥናት ለመታጠን አገልግሎት የሚውለው እሳቱ ሳይሆን፣ ጭሱ በመሆኑ የጭስ እጥነት ላይ ያተኮረ ነው

የትነት ባዝ (the water vapor bath) የሚባለው የእጥነት አይነት በብዛት የሚከወነው፣ ረጅም የክረምት ጊዜን በሚያሳልፉ ሀገራት ነው፡፡ ይኸ የእጥነት አይነት አሁንም ድረስ እየተከወነ እንደሆነ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡ አሁን አሁን ሞቃት የአየር ጠባይ ያላቸው ሀገሮችም በትነት (diffusion} እየተተገበረ ሲሆን የተገኘውም ከቀጥታ የእሳት ነበልባል ባዝ ነው፡፡ Lopatin (1960፡279)

ቅይጥ ባዝ (mixed type) የገንዳ ውሀ ባዝና የውሀ ትነት ባዝ እንድም ከላይ የተጠቀሱትን የባዝ ዓነቶች በማቀላቀል የሚደረግ እንደሆነ ይነገራል፡፡ Lopatin (1960፡ 279)

## 2.2.1. የዕጽዋት  እጥነት

ህክምና በተለምዶ እንደሚታወቀው በህመም ስሜት ውስጥ ያሉ ሰዎችን ከስቃያቸው ፈውስ የመስጠት ተግባር ነው፡፡ በሀገራችን ዘመናዊ ህክምና ከመምጣቱ በፊት ሰዎች ከህመማቸው ብቸኛ መፈወሻ ባህላዊ ህክምና ሲሆን አሁንም የዘመናዊው ህክምናን ጥበብ በማሳደግ የመድሃኒት/ ፈውስ /አዋቂዎች አቅም እንዲጎለብት በማድረግ በበሽታዎች ዙሪያ ፈውስን በመስጠትና በሽታን በመከላከል፣ ወረርሽኞችን በመቀነስ ለማዳን የምንጠቀምበት ነው፡፡ Thomas ( 2005፡391) በተለያዩ ድርሳናት እንደሚገልጹት ባህላዊ ፈውሶች በተለያየ መንገድ ይከወናሉ፡፡ ለምሳሌ በመታጠን ፣ በመብላት፣ በመጠጣት በመቀባት ወ.ዘ.ተ የሚሰጡ ናቸው፡፡

ባህላዊ መድሃኒቶች ከተለያዩ እጽዋቶችና ንጥረ ነገሮች ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ ሲውሉ ይስተዋላል፡፡ ለዚህም ህክምናዎች ከመቆረጥ፣ ከመቀመም ጀምሮ የራሳቸው የሆኑና በየማኅበረሰቡ የራሳቸው የሆኑ ልማዳዊ ስርዓቶች አሏቸው፡፡ በሚቆረጥበት ቀን፣ በሚቆረጥበት ጊዜ መሟላት ያለባቸው ቅድም ሁኔታዎች ወ.ዘ.ተ…ጉዳዮች አሏቸው፡፡

በባህላዊ ሕክምና[1] መድኃኒቱ ከሚቆረጥበት ዕለትና ጊዜ ጀምሮ መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች አሉ፡፡ ዕፀዋት የተፈጠሩት በዕለተ ማክሰኞ ነው ተብሎ ስለሚታመን ባህላዊ ሐኪሙ ለመድኃኒትነት የሚውሉ ዕፀዋትን የሚቆርጠው በዚሁ ዕለት ነው፡፡ መድኃኒቱን ለመቁረጥ ከመውጣቱ አስቀድሞ መደረግ ያለባቸው የተለያዩ ጥንቃቄዎች ያሉ ቢሆንም፣ በዚህ ጥናት ማህበረሰብ ወይባ እንጨትን ለመቁረጥ የሚጠቀሙበት የተለየ ቀንም ሆነ የአቆራረጥ ቅድመ ሁኔታን አይጠይቅም፡፡ ይልቁንም የሚቆረጠው የወይባ እንጨት ዓይነት ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡ በመሆኑም፣ ይህ ዕፅ የሴቶች የመራቢያ አካላትን ያክማል፤ ውልደትን ለማፋጠን ይውላል ተብሎ ስለሚታመን  ወይባውን የሚቆርጠው ሰው ትል ያልወጋውን ( ለእጥነት የሚፈለገውን) እንጨት መርጦ ይቆርጣል፡፡

ባህላዊ ህክምና እንደዘመናዊ ህክምና ማንኛውም ሰው አጥንቶና ተምሮ የሚሰጠው ሳይሆን ስርዓቱም ሆነ ተስተላፎው ልማዳዊ እንደሆነ ያሳየናል፡፡ በተለያዩ አገሮች እጾች የተለያየ የህክምናና የፈውስ መስጫ ተግባራት አላቸው:: አንድን ተክል ከሌሎች ተክሎች መርጦ ለተለየ ዓላማ የሚያውልበት የራሱ የሆነ ልማድ አለው፡፡

በዋናነት በኢንዶኔዝያ ከአንድ በላይ እጾችን በመቀየጥ/blend/ እና በማጠን የወላድ ሴት ጤና ይጠበቅበታል፡፡ Burkil (2004:418) ። በእኔ ጥናት አካባቢ ወይባ እንጨት ጭሱን ለእጥነት በማዋል ለተለያዩ በሽታዎች ማከሚያነት ይውላል፡፡ ባህለዊ ልማዶቹ ሰዎች አካላዊ ጥንካሬ እንዲኖራቸው የሚያግዙ ናቸው፡፡ የእጽዋት ቅርንጫፎችን በመጨመርና በመታጠን የመገጣጠሚያ ህመሞች የሙቀት ሳውናው የተለያዩ የዛፍ ቅርንጫፎች በጋለ ድንጋይ ላይ በማድረግና በሙቀት ላብን በማስወጣት የሚፈጸም ሲሆን በእንፋሎት ሙቀት በመታጠብ ቆሻሻን በላብ መልክ ማስወገድ የሚከውኗቸው ልማዶች ናቸው፡፡ read (1966 :33)::

[1] *WHO (2001ዓ.ም)እንደሚገልጸው ባህላዊ ህክምና ብያኔ ሲሰጥ ጤና ነክ ድርጊቶችን ፣ የአቀራረብ መንገዶችን፣ ዕውቀቶችን እና እምነቶችን ፣እፅዋትን ፣ እንስሳትን፣ ማዕድናትን፣ መንፈሳዊቁሶችንና መንፈሳዊ ክዋኔዎችን መሰረት በማድረግ ህመሞችን የማወቅ የመከላከልና የመፈወስ ስርዓት እንደሆነይገልጻል።በዚህ ጥናት ደግሞ ወይባ ከባህላዊ ህክምና አንጻር የሚሰጠውን ፋይዳ መሰረት በማድረግ ህመሞችን የማወቅ የመከላከል የመፈወስ ስርዓት ነው። በመሆኑም ወይባ ከባህላዊ ህክምና አንጻር የሚሰጠውን ፋይዳ መሰረት በማድረግ ቁሱን እና ፈዋሽነቱን በሃገረሰባዊ ልማድነቱ ያለው ማህበራዊ አስተዋጾ የተመረመረበት ጥናት ነው። ባህላዊ ህክምና ማለት በዚህ ጥናት ውስጥ በኬሚሴ ማህበረሰብ ዘንድ  ይገልጻል።*

ከላይ እንደተገለጸው የተለያዩ ማህበረሰቦች ጤንነታቸውን ለመጠበቅና ጠንካራ ለመሆን በባህላዊ ዘዴ የእንፋሎት ሙቀት የመታጠን ልማድ እንዳላቸው ያመላክታል፡፡ በተጨማሪም ፈዋሽነት ያላቸው እጸዋቶችን መታጠን የጤንነት መጠበቂያዎች አንዱ ልማድ መሆኑን ያሳያል ፡፡

ሶስት አይነት የተርሚናሊያ ዝርያ ለመድሃኒት ይውላል፡፡ ለመድሃኒት ከሚውሉት የተርሚናሊያ ዝርያዎች ተርሚናሊያ አርጁና (arjuna) ፣ተርሚናሊያ ባለሪካ (bellerica) ፣ ተርሚናሊያ ቻቡላ (chebula) ይጠቀሳሉ፡፡ በህንድ ተርሚናሊያ አሩጃ ቅርፊትን ከ3000 ዓመታ በላይ ለልብ መፍትሄ ፣ ለልብና የደም ስር በሽታ ፣ለልብ ድካም ፣ለደም ግፊት፣ ለስብ ክምችት (cholesterol)፣ ለጆሮ ህመም ፣ ለተቅማጥ በሽታ፣ ለአባለዘር በሽታ (STDs)፣ ለሽንት ቱቦ ፣የወሲብ ፍላጎት (sexual desire ) ለመጨመር ሲጠቀሙበት ይጠቀሙበታል፡፡ ተርሚናሊያ ቤሌሪካ (bellerica) እና ተርሚናሊያ ቼቡላ (chebula) ከፍተኛ የስብ ክምችት፣ ተቅማጥና ሆድ ድርቀት የመሳሰሉትን የምግብ መፈጨት ችግሮች ሲያክም በተጨማሪም በኤች አይቪ ከመያዝ (HIV infection) ይከላከላል ብለው ይጠቀማሉ፡፡ ተረሚናሊያ ቤሌሪካ ደግሞ ጉበትንና የመተንፈሻ አካላትን ለማከም ፣ለታመመ ጉሮሮና ለአይን ለአፍ ማጠቢያና መጉመጥመጫ እና ለሴት ብልት ቁስለት (vaginal infections) ለማከም ይውላል፡፡ Mesfin (2007: 29)፡፡ ይህም የዘርፉ ምሁራን በተለያየ አካባቢ ያለውን ልምድ የገለጹበትን የሚያጠናክር ነው፡፡

Elizabeth (1897:134).የተባሉ ጸኃፊ የሴትን ብልት ማጠን (Vagina Steam) ዉርጃን ለመከላከል በኮሪያና በመካካለኛው አሜሪካ ባህል ውስጥ ለብዙ መቶ አመታት ጥቅም ላይ እንደዋለና አሁንም ድረስ የአውሮፓ ባህል ውስጥ ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ይህ ባህላዊ ህክምና በሃገራችን ልዩ ልዩ ማህበረሰብም ሲጠቀሙበት ይስተዋላል[2]፡፡

የሴት ብልትን የማጠን ስነ-ሥርዓት በአብዛኛው በእንፋሎት እና በጭስ መልክ የሚከናወን ሲሆን፣ ለዚህ አገልግሎት የሚውሉት ተክሎች መልካም መዓዛ ያላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለምለምነት ያላቸው ድርቅን የሚቋቋሙ፣ በቀላሉ የሚራቡ ናቸው፡፡ ለዚህ ነው ወይባን በሌላ አጠራሩ Terminalia ‹‹*the drought resistant species occurs in the high rainfall woodlands, bush lands, and wooded savannah of the arid and semi-arid regions*

[2]የወይባ ጭስም በከሚሴ አካበቢም ለዚሁ ተግባር እንደሚያገለግል በእምነት ይዘውት ይታያሉ።

*but can also be found in the sub-humid areas. It is often found near* rivers inverydry areas.›› Leffers (2003: 299) *በማለት የሚገልጹት፡፡ በመሆኑም* በከሚሴ አካባቢም ከሌሎች መዓዛ ካላቸው እንጨቶች ውስጥ የወይባ እንጨት የተመረጠው በተመሳሳይ ምክንያት እንደሆነ ተጠቃሚዎቹ ይናገራሉ፡፡

### 2.2.2. **ክዋኔ**

ክዋኔ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ዋና ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ክዋኔ ማንኛው የፎክሎር ገጽታ በቃልና በድርጊት የሚቀርብበት ወይም የሚንጸባረቅበት ቅጥ (mode) ነው፡፡ ሊያ (2008፡16) ክዋኔ ባህልን ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ ስርአትና እሴቶችን በማህበረሰቡ ዘንድ ለማስረጽ ሚያስችል ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ የአንድ ማህበረሰብ ሙሉ ትውፊት የሚገለጸው በክዋኔ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ማህበረሰብ ወይባ ጭስ ለመሞቅ ክዋኔው ከእፁ ዝግጅት ሚጀምር ሲሆን የምትሞቀው ሴት፤ለእጥነት የሚውሉ ምግብና መጠጦችን እንዲሁም ለእጥነት የሚውሉ ልብሶችና ቅባቶችን በማሰናዳት የሚከወነው የወይባ እጥነት ስርአት እንዲሁም ከእጥነት በኋላ የሰውነት መታጠብና የአመጋገብ ክዋኔዎች የማህበረሰቡን ባህልና ወግ የጠበቁ ናቸው፡፡  ይህን አስመልክቶ  Bauman ስለ ክዋኔ ምንነት የሚከተለውን ሃሳብ ሰንዝረዋል፡፡

> ክዋኔ ማለት በዋናነት እንደ ተግባቦት ባህሪና ዓይነት የሚወሰድ፣ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን የሚፈጸሙ ኪናዊ ጉዳዮችን በሙሉ የሚያጠቃልል ጉዳይ ነው፡፡ ክዋኔ በራሱ መንገድ ተቀምሮ ለታዳሚ የሚደርስና የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ የሚታወቅበት እንዲሁም ሰዎች በተግባቦት ሂደታቸው ውስጥ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮቻቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነው፡፡ Bauman (1992፡3)፡፡

Kapchan (1995፡ 479) የክዋኔን ጽንሰ ሃሳብ ሲገልጹ የአንድን ማህበረሰብ ጸባይ አጠቃሎ የያዘ የአነጋገር ዘየ የሚገለጽበት የተለያዩ ማህበረሰቦች የባህል ስርአት የሚስተዋልበት የአንድን ግለሰብ ሆነ ቡድን ፣ማንነት ገልጾ የሚያሳይ ውበት ያለው የሚያስደስትና የሚያዝናና ልማድ ነው ብለዋል ፡፡

በሌላ በኩል ክዋኔ አንድ የባህል ስምምነት ውጤት የሚቀርብበት መንገድ ነው በማለት የሚገልጹት Ben- Amos (1993፡218) ናቸው፡፡ የባህሉ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ አቅሙን የሚያሳይበት ድርጊት፣ እውቀትና እውቀቱን የሚገልጽበት መንገድ፣ እምነትናእምነቱን የሚያከብርበትን ስርዓተ ክዋኔ ሁሉ ከግምት ውስጥ ማስገባትተገቢ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ

በንግግር፣ በሙዚቃ፣ በዳንስና በድራማ ውስጥ የሚታዩ ክንውኖችን ሁሉ እንደሚያጠቃልል ገልጸዋል፡፡

Sims and Stephen(2005፡175) ክዋኔ ለአንድ የፎክሎር አጥኚ ጠቃሚ መሆኑን ለመግለጽ "Analyzing performance enables folklorist to see how and why groups shape and share their traditional forms of expression" በማለት የፎክሎር ተመራማሪ ለክዋኔ ትኩረት ሰጥቶ የሚያጠናውን ፎክሎር ከመረመረ ተጠኝዎቹ እንዴትና ለምን ባህላዊ ጉዳዮቻቸውን እንደሚቀምሩና እንደሚግባቡ ማስተዋል እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

የወይባ ጭስ የመሞቅ ክዋኔ በሚተገበርባቸው በአራስቤት ፤በጫጉላና በአዘቦት አውዶች ላይ ነው፡፡ በወይባ ጭስ አሟሟቅ ስርአት የሚከወኑ ጥበባዊ ድርጊቶችን ለማጥናት የክዋኔ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም፣ ክዋኔ የፎክሎርን ፅንሰ ሃሳብ የሚመራ ውበት ያለው ጥበባዊ ድርጊት ነው፡፡

Kapchan (1995, 479) በበኩላቸው ‹‹ክዋኔ ውበታዊ የሆነ የድርጊት ባህሪ፣ የንግግር ዘዴ፣ በአካል የሚከወን፣ በጊዜና በቦታ የተገደበ፣ በታወቀ መዋቅር በከዋኞች የሚቀርብ ከመሆኑም በተጨማሪ በተደጋጋሚ የሚፈፀም፣ በግልና በቡድን የሚዋቀር የማንነት ማሳያ ነው፡፡ በኬሚሴ ማህበረሰብም ከዋኞቹ ጾታዊ ግንኙነት የጀመሩ የአዘቦት ተጠቃሚ ሴቶችና አካላዊም ሆነ ስነ-ልቦናዊ ፈውስ ማግኘትን ያለሙ አግባተው ጫጉላቤት የገቡ ሴቶች እና የወለዱ አራሶች ናቸው፡፡ ይኸውም የፎክሎር ጥበባዊ ድርጊት ከዋኝ፣ ቦታ፣ ተመልካች እና የክዋኔውን ሁኔታ የሚይዝ ነው›› ይላሉ፡፡ ክዋኔ አንድ ፎክሎር ምን እንደሆነ መቼ ?፣የት ?፣ በማን?፣ እንዴት? እንደሚከወንና ከዋኞችን ምን የጋራ ጉዳይ እንዳሰባሰባቸው በመካከላቸው ያለው ተግባቦት ምንድን ነው? ፎክሎሩ የሚከወንበት ሁኔታ ምን ይመስላል? ታዳሚዎች እነማን ናቸው? የሚሉ ጉዳዮች ይታዩበታል፡፡

በመሆኑም፣ ሴቶች በአራስነት፣ በሙሽርነትና በአዘቦት ጊዜቸው የሚከውኑት ሲሆን፣ በወይባ እጥነት ከዋኞች አራሶችና አራስ ያልሆኑ ሴቶች ስለሚያገኙት ስነ ልቦናዊ፣ ሆነ አካላዊ ፈውስ ተብሎ የሚከውኑት ነው፡፡ ወይባ በከሚሴ ማህበረሰብ የሚከወነው በአብዛኛው ምሽት ላይ ነው፡፡ ወይባ በተገኘው ቦታ ሁሉ የሚታጠኑት ሳይሆን፣ ለዚሁ ተግባር ተከልሎና ለአቀማመጥ አመቺ በሆነ ቦታ የሚከናወን ነው፡፡ ወይባ በሚታጠኑበት ጊዜ ራሱን የቻለና ለዚሁ ተግባር

ብቻ ተብሎ በተዘጋጀ ከሌ ወይም ብርድ ልብስ የሚሸፈን በመሆኑ kapchan ስለ ክዋኔ የሰጠውን ገለጻ ተገቢ ያደርገዋል፡፡

ይህም የሚያሳየው አንድ የፎክሎር ተመራማሪ ለሚያጠናው ፎክሎራዊ ጥናት ክዋኔው ላይ በማተኮር የሚያጠናውን ርዕሰ ጉዳይ ማህበረሰቦቹ በባህሉ ምን ሊሉ እንደፈለጉ፤እንዴትና ለምን ባህላዊ ጉዳዮቻቸውን እንደሚያስኬዱ ያላቸውን ጥበባዊ ተግባቦት በማስተዋል መግለጽ እንዳለበት ያስረዳል፡፡

ክዋኔ በአንድ በተወሰነ አውድ ወይም ቡድን የሚቀርብን ጥበባዊ ገለጻ ለማጥናት ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው፡፡ ክዋኔ የፎክሎርን ጽንሰ ሀሳብ የሚመራ ውበት ያለው ጥበባዊ ድርጊት በመሆኑ በኬሚሴ ከተማ የሚከወነውን የወይባ ጭስ የመታጠን ልማድ ከአዘገጃቱ ጀምሮ እስከ እጥነቱ ባለው ስርአተ ክዋኔ ላይ የሚፈፀሙ ድርጊቶችን ፤ ጭስ ሲገባ የሚጠቀሙባቸውን ቁሶች በአሟሟቅ ስርአቱ የሚታዩትን ሁነቶች ለመመልከቻነት ተጠቅሜበታለሁ፡፡

## 2.2.3. አውድ

አውድ የክዋኔ ገፅታ ወይም ድባብ ነው፡፡ የክዋኔውን መቼት፣ በክዋኔ ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሶችን፣ አጠቃላይ የክዋኔውን ሁኔታ እንዲሁም የከዋኙንና የታዳሚውን ግንኙነት የሚያጠቃልል ነው፡፡ Dan- BenAmos (1993, 210) የአንድ ፎክሎር ክዋኔ ሲነሳ ትኩረት ሊቸረው የሚገባው ዐብይ ጉዳይ አውድ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ የአንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ /text/ መልእክት ለመረዳት አውድን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ፎክሎሩን በምልዓት ለመተርጐም የሚችለው አውዱን በሚገባ ሲረዳ ብቻ ነው፡፡ የአውዱን አጠቃላይ ድባብ ሳይረዱ የፎክሎሩን መልዕክት ማወቅና መተርጎም ያስቸግራል፡፡ የወይባ አስተጣጠን አውድ እጥነቱ የሚካሄድበትን ምሽት፣ ዕጥነቱን ለማድረግ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀውን ከለላ ታዛ፣ ጉድጓድና ጭሱን አለባበሱን ሁሉ ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሂደቶች ባላተሟሉበት ሁኔታ ታጣኟም ሆነች መታጠኗን የሚያስብ አጣኝም ሆነ ተመልካች የወይባ እጥነት እተከወነ ነው ብሎ ሊወስድ አይችልም፡፡

የአንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ክዋኔ ምንነት ለመረዳት የሚከወንበትን አጠቃላይ ገጽታ ወይም ማህበራዊ አውድ መረዳት ተገቢ እንደሆነ ቤን አሞስ ያስረዳሉ፡፡ በወይባ እጥነትም ማህበራዊ አውዱ እጥነቱ የተፈቀደው ጾታዊ ግንኙነት የጀመሩ ሴቶች ብቻ መሆኑ ሲሆን፣ ባህላዊ አውዱ ደግሞ ማህበረሰቡ ያበጀውና ለመታጠን የተመረጠው ወይባ /እንጨት/ ጭስ ለመታጠኛ የተመረጠው ቦታና መጠቀሚያ እቃዎች ወዘተ አድርገን ማየት ግድ ይለናል፡፡ ማህበራዊና

ባህላዊ አውዱንም ጥሩ ትንታኔ ለመስጠት የሚቀርብበትን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ሁኔታዊ አውድ ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው። ለዚህም ነው ማህበራዊና ባህላዊ አውድ ተደጋግመው የሚከወኑ ወይም በተለያዩ ሰዎች ቢከወኑም ማህበረሰቡ አንድ አይነት ፍቺ ማግኘት መሰረት ያደረገ ትንተና ለመማካሄድ ይረዳል :: Dan- BenAmos (2007፡ 210-211)።

ከዚህም በተጨማሪ Bascom (1954፡ 334) እንደገለጹት ማህበራዊ አውድ በውስጡ የሚከተሉትን ነጥቦች ይይዛል። የፎክሎሩ ዓይነት የሚቀርብበት ጊዜና ቦታ፣ የከዋኙ ማንነት፣ የታዳሚው ወይም የአድማጩ የመፍጠር ብቃት፣ በከዋኙና በሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ መካከል ያለው ግንኙነት፣ የክዋኔው ኪናዊነት፣ የማህበረሰቡ ልማዳዊ የቡድን አመሰራረት ስልት እንዲሁም ማህበረሰቡ ለቡድኑ ያለውን አመለካከት በፎክሎሩአማካኝነት ለመረዳት የሚተኮርባቸው ነጥቦች ናቸው። በተጨማሪም፣ ሰዎች በንግግራቸውና በእንቅስቃሴያቸው ሁሉ አስተሳሰባቸውን፣ የህይወት ልምዳቸውን እንዲሁም ባህላዊ ተምሳሌቶቻቸውን የሚገልጹባቸው ሁኔታዎች በሙሉ በማህበራዊ አውድ ውስጥ የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው።

አውድ አንድ ጉዳይ ሲከወን የሚኖር፣ የሚያስፈልግ፣ የሚቆጣጠር ማንኛውም ነገር ሲሆን የሚከወነውን ፎክሎራዊ ጉዳይና የሚከወንበትን አጠቃላይ ገጽታ ያስተሳስራል። ይህም ሲባል ከዋናው ክንውን በፊትም ሆነ በኋላ (ቅድመ ክዋኔ፣ ክዋኔ እና ድህረ ክዋኔ) የሚፈጸሙ ስነ-ስርዓቶችን በሙሉ ያጠቃልላል። ፎክሎሩ ነፍስና ስጋ የሚኖረውም በዚህ መንገድ ከተጠና ነው። በመሆኑም የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ የተሟላ ፍቺ ይኖረው ዘንድ በሚቀርብበት ማህበረ-ባህላዊ አውድ ውስጥ መተንተን አለበት።

አንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ በሚከወንበት አውድ ውስጥ ስናጠና ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ስድስት ነጥቦችን መመልከት ተገቢ እንደሆነ Bauman (1983፡ 367) ጠቁመዋል። እነሱም ፍቻዊ አውድ፣ ተቋማዊ አውድ፣ የማህበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ፣ ማህበራዊ መሰረት፣ ግለሰባዊ አውድ፣ እና ሁኔታዊ አውድ ናቸው። ምንነታቸውን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ማህበረሰቡ ስለሚከውናቸው ልምዶችና እውቀቶች ምን ግንዛቤ እንዳለው፣ እንዴት እንደሚረዳው፣ የትኛውን የህይወት ገጽታ እንደሚያይ እና ለመከወን ያነሳሳው ጉዳይ ምን እንደሆነ ለመገንዘብ የሚያስችል ነው። ይህም ጉዳዩ በተለያዩ ሰዎች ምን ትርጓሜ እንዳለው

ከማሳወቁም ባሻገር ከብዙው የተለየ ፍች ሊያስገኝ ስለሚችል በጥንቃቄ መታየት አለበት። በመሆኑም የኬሚሴ ከተማ ማህበረሰብ ስለ ወይባ ጭስ ምን ግንዛቤ እንዳለው የእጥነት አጋጣሚዎቹምንምን እንደሆኑና እንዴት እንደሚረዷቸው፣ እጥነቱን ለመከወን ምን እንዳሚያነሳሳቸው ያስገነዝባል ።

**ተቋማዊ አውድ** ሁለተኛው በአውድ ተኮር ጥናት የሚተኮርበት ሲሆን የወይባ ዕጥነቱ የት ቦታ ይከወናል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው። ጉዳዩ የሚከወንበት ተቋም መኖሪያ ቤት/ትዳር ማህበራዊ ወይስ ሃይማኖታዊ መሆናቸውን ከመመርመር ባሻገር ምን ዓይነት ተቋማዊ ፋይዳ ያበረክታሉ የሚለውንም ያመላክታል። ማህበረሰቡ የወይባ ጭስ እጥነትን ስርዓተ ክዋኔ የሚከወነው የት እንደሆነ ከማስገንዘቡም በላይ መከወኑ የሚያስገኘውን ተቋማዊ ፋይዳ / ለቤተሰቡ ወይም ትዳሩን ለመመርመር አስችሏል።

**የተግባቦት ሂደት አውድ** ሶስተኛው አውድ ነው። ትኩረቱም የወይባ አስተጣተን ከሌላ የፎክሎር ቅርጽ ጋር እንዴት ይዛመዳል? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው። ማለትም የሚጠናውን ጉዳይ አንዱን ከሌላው ለመለየት ማህበረሰቡ የሚጠቀምበት ሀገርኛ ስያሜ ምን እንደሆነና የወይባ አስተጣጠን ከማህበረሰቡ አመጋገብ፣አለባበስ ወዘተ ጋር ያለውን ዝምድና፣ የሚያሳይ ነው። የእያንዳንዱ ዘውግ ይዘት፣ ፍቺ እና ቅርጽ ምን መሆን እንዳለበት ይወስናል፤ የእያንዳንዱን ዘውግ አገልግሎትና አጠቃቀም ይወስናል፤ የእያንዳንዱ ዘውግ ተገቢነትና ጥበባዊ ዋጋ የሚመዘንባቸውን መስፈርቶች ይገልጣል።

ማህበራዊ መሰረት በማህበረሰቡን እጥነቱ የሚከወነው በየትኛው የማህበረሰብ ክፍል እንደሆነ፣ ምን ዓይነት ማህበራዊ ደረጃ እንደሚያሳይ ፣ በክዋኔው የሌላው ማህበረሰብ ተሳትፎ ምን እንደሆነ በመረዳት የተሻለ አውዳዊ ትንታኔ መስጠት ይቻላል። እንዲሁም በአንድማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በጾታ፣ በእድሜ፣ በሙያ/በሥራ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በእምነት/ በሀይማኖት፣ በልዩ ልዩ ቡድኖች (ማህበራዊ አደረጃጀት መርሆች) ይከፈላሉ። እነዚህ ለአንድ ህብረተሰብ መለያየትና መከፋፈል መነሻ የሆኑ መሰረታዊ ጉዳዮችና ቡድኖች ለፎክሎራዊ ጉዳዩ መለያየትም ምክንያቶች ናቸው። በመሆኑም የወይባ ጭስ መታጠን የሚከወንበትን የማህበረሰብ ክፍልና ማህበራዊ መሰረት በመረዳት የተሸለ አውዳዊ ትንታኔ እንዲሰጥ አስችሎኛል ።

ግለሰባዊ አውድ ስንመለከትም ዕጥነቱ ከግለሰቧ ኑሮ፣ ሀሳብና ስሜት ጋር እንዴት ይሄዳሉ? የሚለው ጥያቄ ላይ ያነጣጥራል፡፡ በመሆኑም የግለሰብን ስሜት የመግለጽ አቅማቸውን እና ፎክሎራዊ ቅርጹ ለግለሰቦች የሚሰጠውን ቦታ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

**ሁኔታዊ አውድ** ማህበረሰቡ እጥነቱን የሚከውነው በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ነው? የሚለውን የሚመልስ ነው፡፡ ለአንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ መፈጠር ምክንያት የሚሆን ማህበረሰባዊና ግለሰባዊ አጋጣሚ ነው፡፡ ሁኔታዊ አውድ በባህሉ የተወሰነ የአንድ ባህሪ ወይም ገጠመኝ መግለጫ አንድ ትርጉም ያለው ድርጊት/ተግባር የሚከናወንበት አውድ ማለት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ አካላዊ መቼቱ፣ የተሳታፊዎቹ ማንነትና በክዋኔው ውስጥ የሚኖራቸው ሚና፣ ክዋኔውን የሚገዙባቸው የተለያዩ ህግጋት፣ በየደረጃው የሚከናወኑ ድርጊቶችና ተግባራት፣ ቅደም ተከተል ይካተታሉ፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ለምን በዚያ አጋጣሚ እንደተከወነ በተከወነበት ሁኔታ ምን ትርጉም እንዳለው የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም የወይባ ጭስ የሚከወንባቸውን አጋጣሚዎች በመለየት አጋጣሚዎቹና ከጭሱ ያላቸውን ተያያዥነት ያሳየናል፡፡

Dan- BenAmos ከላይ የተዘረዘሩትን ስድስት የአውድ ዓይነቶች በአንድ ላይ በማጠቃለል “ባህላዊ አውድ” እና “ሁኔታዊ አውድ” በማለት በሁለት ከፍለው ያስቀምጧቸዋል፡፡ በወይባ እጥነት ባህላዊ አውዱ ትውፊታዊ ጉዳይ ሲሆን ክዋኔው የሚወክላቸውን ነገሮች፣ የሚከወነው ጉዳይ፣ የሚመራበት ማህበራዊ ደንብ፣ የተሳታፊዎች የእምነት ስርዓት፣ የቋንቋ አጠቃቀምና የንግግር ስልት፣ የከዋኙ ለትወፊቱ ያለው እውቀት እና የስነ-ምግባር ህጎችን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ሁኔታዊ አውድ ማለት ደግሞ የወይባ እጥነቱ የሚቀርብበትን ማህበራዊ ሁኔታ የሚመለከት ነው ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ዘዴ

*ይህ ጥናት ዓይነታዊ* /*qualitative*/ *ምርምር ነው።* (best፡1981) "qualitative method can describe events and persons scientificaly without the use of numerical data" (*ዓይነታዊ የምርምር አይነት ያለምንም አሃዛዊ መረጃ ሁነቶችንና ሰዎችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሊገልጽ ይችላል*) ። *በመሆኑም ጥናቱ የወይባ ጭስን አዘገጃጀት አጠቃቀምና የጤና ፋይዳ መርምሮ ማሳየት በመሆኑ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት አገልግሏል።*

## 3.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

*ይህን ጥናት ለማካሄድ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከቀዳማይና ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች ነው።*

*በቀዳማይ የመረጃ ማሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥናቱ መስክ ወጥቶ መረጃ መሰብሰብን ስለሚጠይቅ በተፈጥሮአዊ መቸት የወይባ ጭስ አሟሟቅ ክዋኔን በመመልከት፤ የወይባ ጭስ አዘገጃጀት አጠቃቀምና የጤና ፋይዳን በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት በመታገዝ ወይባ ጭስን ዘወትር ከሚሞቁ ሴቶች፤ አራስ ሴቶች፣ በጫጉላ ቤት ላይ እጥነት ከጀመሩ ሴቶችና ከጭስ ተጠቃሚ የትዳር አጋሮች፣ ከጭስ አሟቂ የስር ሚዜዎች፣ ለወይባ ጭስ እውቀቱ ያላቸው የእድሜ ባለፀጋዎች ጋር በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይት መረጃዎች ተሰብስበዋል ።*

*በካልአይ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ደግሞ የወሎ ኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ርዕሰ ከተማ ስለሁነችው የኬሚሴ ከተማ ማህበረሰብ እና ከጥናቱ ርዕስ ጋር የሚዛመዱ የምርምር ስራዎች፣ ለጥናቱ ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን ከተለያዩ መዛግብት፣ መፅሄቶች ፣ድህረ-ገጾች መረጃዎች ተሰብስበውበታል። እነዚህን ሦስቱን የፎክሎር የመስክ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መጠቀም ያስፈለገኝ እያንዳንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የራሱ የሆነ ጠንካራ እና ደካማ ጎን ስላለው የአንዱን ድክመት የሌላው ጥንካሬ ስለሞላልኝ በአንዱ መረጃ መሰብሰቢያ ያጣሁትን መረጃ በሌላው እንዳገኘው እረድቶኛል ።በዚህም መሰረት የሚከተሉትን ዘዴዎች ተጠቅሜአለሁ።*

### 3.1.1 ምልከታ

ለዚህ ጥናት በአንደኛ ደረጃነት ተግባር ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ ምልከታ ነው። በምልከታ አማካኝነት የወይባ ጭስ አጠቃቀም ክዋኔ በቀጥታ ከተጠቃሚዎቹ ጋር በመስክ በመገኘት አዘገጃቱን፣ የአሟሟቅ ስርአቱንና ወይባ ጭስ ሲሞቁ የሚከተሏቸውን የመሞቂያ ሰዓት ፣ ቅቤ ሰውነትን መለቅለቅ ያሉ ልማዶችን እና ተግባር ላይ የሚውሉ እንደ ለጋ ቅቤ፣ ከሌ፣ የወይባ እንጨት ፣ ቦለቅያ ያሉ ቁሶችን በመመልከት የጭሱን አጠቃቀም ከነባራዊ ሁኔታው መረጃ ለመሰብሰብ አስችሎኛል ።

Gray (2004፣138) ምልከታ አንድን ጉዳይ የመመልከት እና ማስታወሻ የመውሰድ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የአጥኚውን አምስቱንም የስሜት ህዋሳቶች ማቀናጀትን የሚጠይቅ ስራ ነው በማለት ያስረዳል። አያይዞም ምልከታ የሰዎችን ድርጊት በነቃ መንፈስ የመከታተልን፣ ክዋኔውን በአግባቡ ቀርጾ የማስቀመጥን እና የተጠኚዎችን ባህሪ የመረዳት እውቀት የሚጠይቅ መሆኑን አስፍሯል። በዚህ ጥናትም ምልከታ ያደረኩባቸውን የወይባ ጭስ አሟሟቅ ስርአት፣ ክዋኔ፣ የወይባ ጭስ የሚሆን እንጨት አዘገጃጀትን በትኩረት በመመልከት የተጠኚ ማህበረሰቦችን ባህል በመረዳት የአዘገጃጀትና የአሟሟቅ ክዋኔዎችን የሚያመለክቱ መረጃዎች በመቅረፀ ድምጽ፣ በፍቶ ግራፍ ተሰንደዋል።

ከዚህም በተጨማሪ Goldstein (1964፣ 92) ምልከታ ስናካሂድ በዋናነት ትኩረት ልንሰጥባቸው የሚገቡን ጉዳዮች የክዋኔው ባህላዊ እና ማህበራዊ አውድ፣ ከዋኝ፣ ተደራሲ፣ በሁለቱ መካከል ያለው መስተጋብር፣ ቅርጽ፣ መቼት እና የሚከወንበት አጋጣሚ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ምልከታ በሁለት አይነት መንገድ ሊከናወን እንደሚችል Kothari (2004፣ 96) ያስረዳሉ። ይኸውም ተሳትፎአዊ እና ኢ-ተሳትፎአዊ የሚባሉ ናቸው። በተሳትፏዊ መንገድ መረጃን ለመሰብሰብ አጥኚው የተጠኚው ማህበረሰብ ባህል፣ ደንብ፣ ወግ፣ ልማድ፣ ቋንቋ ማወቅ ይኖርበታል። በዚህ ጊዜ በሚፈጽሟቸው ስርዓተ ክዋኔዎች ሁሉ እየተሳተፈ የሚፈልገውን መረጃ ለመሰብሰብ ያስችለዋል። የሚከውኗቸውን ፎክሎሮች በሙሉም ይሁን በከፊል አብሮ ተሳታፊ ይሆናል። ኢተሳትፎ አዊ ምልከታ የሚባለው ደግሞ ተመራማሪው በሚከውነው ተግባር ላይ ምንም ሚና የሌለው ሲሆን ዳር ቆሞ የሚያየውን በሙሉ የሚመዘግብበትን ሂደት የሚመለከት ነው።

በመሆኑም፣ በዚህ ጥናት የተጠኘውን ማህበረሰብ ባህልና ልማድ በከፊል ስለማውቀው ከአመጋገብ ባህላቸው እስከ አለባበስ ባህላቸው እነሱ የሚከውኑትን በመከወን፣ መረጃዎች የተሰበሰቡት በተሳትፎ አዊ የምልከታ ዓይነት ነው። በመሆኑም፣ በወይባ ጭስ በመታጠን ስርዓተ ክዋኔው ወቅት ጭስ የምትገባው ሴት ሰውነት ቅቤ ከመለቅለቅ ስርአት ጀምሮ ጭስ ተሞቆ እስከ መታጠብ ድረስ ያለውን ክወና በመከታተልና ወይባ እንጨት በማቅረብ፣ ጭስ የምትሞቅ ሴትን አጥሚት በማጠጣት ፣ከሌና ብርድ ልብስ በማልበስ በተሳትፏዊ ምልከታ መረጃ ሰብስቤለሁ። በምልከታዬ ወቅት ትኩረት በመስጠት ለምልከታ መረጃ መሰብሰቢያነት ባዘጋጀኋቸው ፎቶ ካሜራ፣ መቅረጸ ድምጽ፣ ማስታዎሻ፣ ብዕር…የመሳሰሉ ቁሳቁሶች በመጠቀም የምልከታ መረጃዎችን ሰብስቤለሁ።

በመሆኑም፣ በዚህ ጥናት ሁሉም ክዋኔዎች በተፈጥሮአዊ አውዳቸው በተለይም ከፍተኛ መደበኛ አውድ የሚባለው የታዩ ናቸው። ከላይ ምሁራኑ እንደገለፁት፤ በዚህ ጥናት ምልከታ ከየካቲት ወር 2010 ዓ.ም ጀምሮ በሶስት አጋጣሚዎች ማለትም በጫጉላ ቤት፤ በአራስቤት፤ የአዘቦት አጋጣሚዎች ላይ በቦታው በመገኘት የወይባ ጭስን የሚሞቁ ሴቶችን በከፍተኛ መደበኛ (Highly formal ) አውድ በመጠቀም ምልከታየን አካሂጃሁ። በጫጉላ ቤት በመገኘትም አግቢዋ ሙሽራ ወይባ ጭስን እንዴት እንደምትሞቅ ፣ማን እንደሚያሞቃትና ጭስ ስትገባ የተጠቀመቻቸውን ቁሶች ተመልክቻሁ። እንዲሁም በአራስ ቤት በመገኘት የወለደች ሴት ወይባ ጭስን፣ ስትሞቅ የምትከተላቸውን ባህላዊ ስርአቶች በትኩረት በመመልከት መረጃዎችን ሰብስቤለሁ። በዘወትር ተጠቃሚዎች ቤት በመገኘት እደዚሁ ተጠቃሚዎቹ ወይባ ጭስን የሚጠቀሙበትን ሁነት አስተውያለሁ።

በእነዚህ በከፍኛ መደበኛ አውዶች ሙሉ በሙሉ የወይባ ጭስ አሟሟቅ ስርአተ ክዋኔውን በመመልከት ጭስ ሲገቡ የሚለብሱትን ልብስ ፣ የሚመገቡትን ምግብ ዓይነት፣ የሚሞቁት ወይባ እንጨት ባህሪ በምልከታየ ወቅት የተቃኙ ናቸው። በምልከታ ሰዓትም ወይባ ጭስ የምትሞቅ ሴትን ቅቤ በመቀባት፣ ወይባ እንጨት በማቅረብ፣ ከሌና ብርድ ልብስ በማልበስ የምትጠጣውን ሾርባ በማቀበል ከፊል ተሳትፎአዊ በሆነ የምልከታ ዘዴ መረጃዎችን ሰብስቤለሁ።

### 3.1.2 ቃለ መጠይቅ

በዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ከዋሉ ዘዴዎች አንዱ ቃለ መጠይቅ ነው። በምልከታ ወቅት ያገኘኋቸውን መረጃዎች ይበልጥ ግልጽ ለማድረግና ለማዳበር እንዲሁም ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ እና የወይባ ጭስ ማህበረሰቡ ለምን ይጠቅመኛል ብሎ እንደሚከውን ለማወቅ በምልከታ ወቅት ያየኋቸውን እና ማህበረሰቡ እንዲመልስልኝ የምፈልጋቸውን ጥያቄዎች በመጠየቅ መረጃዎችን ለመሰብስብ ተጠቅሜበታለሁ። ጥናቴ ከቃለ መጠይቅ አይነቶች አንጻር በጥልቅ (*in-depth*) ቃለ መጠይቅ ላይ መሰረት ያደረገ ነው።

የቃለ መጠይቅን አስፈላጊነት Vandaerstoap and Johnston (2009፡224) ሲገልጹ፡- በስርዓት የተዋቀረ ቃለ መጠይቅ የማህበረሰቡን እይታ ፣አመለካከት እና ለኑሮ የሚሰጠውን ፍቺ ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ያስገኛል። እንዲሁም በቃለመጠይቅ የሚገኝ መረጃ የተሳታፊዎች እውቀት፣ እምነት፣ ስሜት፣ ፍላጎት ስራ እንዲሁም ለሚያከናውኗቸው ድርጊቶች የሚሰጧቸውን ምክንያቶች ሁሉ ያጠቃልላል። አጥኚው ቃለ መጠይቅን ተጠቅሞ ለሚጠይቀው ነገር ጥልቅ እውቀት ሊኖረው እንደሚገባ ያሰረዳሉ ።

ስለሆነም፣ በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የጥናቱ አካላይ ከሆኑት ከኬሚሴ ከተማ ማህበረሰብ ውስጥ ወካይ የሚሆኑ በአላማ ንሞና የመረጃ አቀባዩችን በመረጃ ምንጭነት አሳትፌአለሁ። ለዚህ ቃለ መጠይቅ መረጃ አቀበቀዩች ሲመረጡ ፤ የልማዱ ተጠቃሚነት፣ ለባህል ያለቸው ዕውቀት፣ ዖታ፣ እድሜ የመምረጫ መስፈርት ሆነው ገብተዋል። በዚህምመሰረት 16 ሴቶችና 6 ወንዶች በአጠቃላይ 22 መረጃ አቀባዮች ተመርጠው መረጃ እንዲሰጡ ተደርገዋል።

በተጨማሪም በውይይት ወቅት ስለዚህ ጉዳይ ከኔ የተሻለ እከሊት ታውቃለች ።በማለት ማመላከት ስለ ገጠመኝ አንዳንዴ ሰዎችን በአመልካች ናሙና (Snow ball Sampling) ቅብብሎሽ ስሌት በመጠቀም መረጃ እንዲሰጡኝ በማድረግ ተግባር ላይ አውየዋለሁ ።።

የመረጃ አቀባዩችም ጫጉላ ቤት በሙሽርነት ያለች ሴት፣ ከነባለቤቷ፣ ሙሽራዋን በስር ሚዜነት ተረክቦ ወይባ የሚያሞቀው የሙሽራው ቅርብ ጓደኛ፣ ወልዳ አራስ ቤት ያለች ሴት ከነ ባለቤቷ፣ የአዘቦት ተጠቃሚ የሆነች ሴት ከነባለቤቷ ፣ ስለ ወይባ እውቀቱ አላቸው የሚባሉ የአካባቢው እድሜ ባለፀጋዎችን ከተጠኚው ማህበረሰብ ተመርጠዋል።

እነዚህን የተመረጡ መረጃ አቀባዩች እንደየ ባህሪያቸው ሊመልሷቸው የሚችሏቸውን ጥያቄዎች በማዘጋጀት መረጃዎቸን ሰብስቤለሁ። ከነዚህም ጫጉላ ቤት በሙሽርነት ላይ ላለች ሴት በሙሽርነት ጊዜዋ ወይባ ጭስን ለመጀመሪያ ጊዜ መሞቅ የምትጀምርበት ወቅት በመሆኑ፣ ምን አይነት ስሜት እንደተሰማት፣ ካሁን በፊት ለምን መሞቅ እንዳልቻለች ፣ ወይባ ጭስ የምትሞቀው ምን አይነት ፋዳ ስላለው እንደሆነ ፣ ወይባ ከመሞቋ በፊትና መሞቅ ከጀመረች ወዲህ በአካሏም ሆነ በመንፈሷ ላይ ምን አይነት ለውጥ እንዳየች የሚያመላክቱ መረጃዎች፣ በቃለ መጠይቅ በጥልቀት ተዳሰዋል ።

እንዲሁም፣ የሙሽራዋ ባል ባለቤቱ በጫጉላ ቤት እያለች ወይባ ጭስ መሞቅ መጀመርዋ በእርሷም ሁነ በእርሱ ላይ ያለውን ጠቀሜታ፣ ወይባ በመሞቅ ስርአቱ የእርሱ ድርሻ አለው ወይስ የለውም፣ ወይባ ባትሞቅ እርሱ ምን እንደሚሰማው ፣በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ናቸው። በተጨማሪም፣ የሙሽራው ስር ሚዜ ሙሽሪትን በበላይነት ወይባ የማሞቅ ስራ የሚሰጠው በመሆኑ ወይባ የሚያሞቃት ምን ታገኛለች ተብሎ እንደሆነ ፣ ከጫጉላ ቤት በፊት ለምን መሞቅ እንዳልጀመረች የሚያሳዩ መረጃዎች ተዳሰዋል። ሌላው አጋጣሚ አራስ ቤት ሲሆን በአራስቤት ያለች ሴት በቃለ መጠቅ የምትሳተፍባቸው ጥያቄዎች በአራስነት ወይባ ጭስ መሞቅዋ ምን ፋዳ እንዳለው ፣በአራስነት ወይባ ካልሞቀች ሴት እርሷ በምን እንደምትለይ ፣ ወይባ መሞቅ የምትጀምረው በወለደች በስንት ቀኗ እንደሆነ ፣ እስከ ስንት ጊዜ እንደምትሞቅ፣ እና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በተጨማሪም የትዳር አጋሩ በአራስ ቤት ወይባ በመሞቅዋ ምን እንደሚሰማው ፣ ወይባ በመሞቅ ስርአቱ እርሱ ድርሻ ምን እንደሆነ ፣ የሚያመላክቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በአዘቦት የወይባ ጭስ ተጠቃሚ ሴት ለምን የወይባ ጭስ እንደምትሞቅ ፣ መቸ እንደምትሞቅ ፣እንዴት እንደምትሞቅ ፣ ወይባ ከማይጠቀሙ ሴቶች እርሷ በምን እደምትለይ ፣ በቃለ መጠይቁ በትኩረት ተሰብስበዋል ።

እድሜ ጠገብ ከሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ደግሞ ወይባ የመሞቅ ልማድ መቸ፣ እንዴትና ለምን እንደተጀመረ ፣ የወይባ እንጨት ምን አይነት ባህሪ እንዳለው፣ የወይባ ጭስ እና የኬሚሴ ማህበረሰብ ያለው ትስስር እንዴት እንደሆነ፣ ወይባ ጭስን የተመረጡ ሴቶች ብቻ የሚሞቁበት ምክንያት ምን እንደሆነ ይህ ጭስ የመሞቅ ልማድ በማን እንደተጀመረ፣ ወ.ዘ.ተ.... በጥልቀት ቃለመጠይቆች ተካሂደው መረጃዎች ተሰብስበዋል።

### 3.1.3 ተተኳሪ ቡድን ውይይት

የተሰበሰበውን መረጃ የበለጠ አስተማማኝ ለማድረግ ከላይ ከቀረቡት ዘዴዎች በተጨማሪ የተተኳሪ ቡድን ውይይቶች ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፣ በቃለ መጠይቅም ሆነ በምልከታ ያልተሟሉ፣ ግልፅ ያልሆኑ፣ ማብራሪያ የሚፈልጉ መረጃዎችን "ስለ ወይባ ጭስ " የሚጠቀሙና የሚያውቁ ሰዎች ጋር በሚደረግ ውይይት እርግጠኛ የሆነ መረጃ ለማግኘት፤ በቃለ መጠይቅና በምልከታ ያልተመለሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ እና አጠራጣሪ የሆኑ መረጃዎችን ለማረጋገጥ ስለሚያስችለኝ በሶስተኛ ደረጃ መረጃ መሰብሰቢያነት ተገልግየበታለሁ።

የቡድን ተሳታፊዎች የተነሳ የተሳታፊዎችን ቁጥር Vandaerstoap and Johnston (2009፡235) ሲገልጹ ‹‹በቡድን ውይይት ወቅት ውይይቱን የሚያካሂዱ ሰዎች ቁጥር ከ6-10 ወይም ከ5-15 ያህል ሰዎች መካከል የሚደረግ የጥያቄና መልስ ሂደት ነው›› ይላሉ። ስለሆነም በዚህ የወይባ ጭስ አዘገጃጀት፣ አጠቃቀምንና ፋይዳ የሚመለከቱ መረጃዎችን እንዲሰጡኝ የጥናቱ አካባይ ከሆኑት የኬሚሴ ከተማ ማህበረሰብ ውስጥ በጥናቴ ቢካተቱ የዳበረ መረጃ ይሰጡኛል ያልኳቸውን መረጃ አቀባዩች ስለ ባህሉ እውቀት ያላቸውና ባህሉን መተርጎም የሚችሉ ሰዎች በአላማ ናሙና በመምረጥ አሳትፌለሁ። በዚህም መሰረት በዚህ ጥናት ተተኳሪ የቡድን ውይይት የተደረገው መረጃ ሰጪዎችን ወይባ ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶችን በአንድ ቡድን የወይባ ተጠቃሚ ሴቶች ባሎችን ሁለተኛ ቡድን እንዲደራጁ በማድረግ ሲሆን የመጀመሪያው ቡድን 6 ሴቶችን የያዘ ሲሆን ሁለተኛው ቡድን 6 ወንዶችን የያዘ ነው። በአጠቃላይ 12 ተወያዮችን ያሳተፈ ሲሆን በተመሳሳይ ቀንና ቦታ የተደረገ ነው።

## 3.2. የመረጃ አቀባዩች አመላመል

ያለው (1998፡ 132) እንደ ገለጸው በአላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመራማሪው የጥናቱን ተሳታፊዎች የሚመርጠው ከጥናቱ ዓላማ አንፃርነው። እነማን ብመርጥ የምፈልገው መረጃ ኖሯቸው ሊሰጡኝ ይችላሉ ?የትኞቹ የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ቢሳተፉ አስፈላጊውን መረጃ ላገኝባቸው እችላለሁ? የሚሉትን ቅድመ ሆኔታዎች በማሰብ የሚመረጥ እንደሆነ ይገልፃል ።

በመሆኑም፣ በዚህ ጥናት የጥናቱ አካላይ ከሆኑት ከኬሚሴ ከተማ ማህበረሰብ መካከል በጥናቴ ቢካተቱ የአካላዩ ወካይ በመሆን የዳበረ መረጃ ይሰጡኛል ያልኳቸውን መረጃ አቀባዩች በአላማ ናሙና (Purposive Sampling) በመጠቀም የተመረጡ ሲሆን አልፎ አልፎ በቅብብል

ናሙና (Snow ball Sampling) መረጃ ሰጭዎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ በኬሚሴ ከተማ ከሚገኙ 7 ቀበሌዎች መካከል ለዚህ ጥናት የተመረጡት ሶስት ቀበሌዎች ናቸው፡፡ እነሱም ቀበሌ ሶስት ቀበሌ ስድስት እና ቀበሌ ሰባት ናቸው፡፡ ምክንያቱም ለዚህ ጥናት መረጃ መገኘት አመቺ በመሆናቸው ነው፡፡ ቀበሌ ሰባት የገጠር ቀበሌ ከመሆኑ የተነሳ ዋናውን መረጃ (Originality) ለማግኘት ምቹ በመሆኑ እና ቀበሌ ስድስትና ሶስት ደግሞ ነባር የወይባ ጭስ ተጠቃሚዎች በብዛት የሚኖሩባቸው በመሆናቸው ነው፡፡

## 3.3. የመረጃ መቀንበቢያና መተንተኛ ዘዴ

ያገኘኋቸውን መረጃዎች በመልክ በመልክ አደራጅቼ ተንትኜ ለማቅረብ ሞክሬአለሁ፡፡ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ተገቢ ሊሆን ይችላል ብዬ ያሰብኩት የመረጃዬ መቀንበቢያ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (functional Theory ) በመመራት ገላጭ (Descriptive) የመተንተኛ ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ እነዚህን ዘዴዎች የመረጥኩበት ምክንያት በተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ የወይባ ጭስ መሞቅ የሚያስገኘውን ፋይዳ ለማሳየት ከወይባ ጭስ ጠቀሜታ የሚነሳ በመሆኑ በተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ተተንትኗል ፡፡ ተግባራዊ ቲዮሪ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ማንኛውም ነገር ያለውን ተግባርና አገልግሎት ለመመርመር ይረዳል Okpewho (1992:173):: በመሆኑም የወይባ ጭስ መታጠን ስርዓተ ክዋኔውን ለመተንተን ግልጋሎት ላይ የሚውለው በመታጠን ክዋኔው ውስጥ በየደረጃው የሚከወኑ ተግባራት ፋይዳ፤ እንዲሁም አጠቃላይ መታጠኑ ለምን ዓላማ እንደሚጠቀሙት በኬሚሴ ከተማ ማህበረሰብ አስተሳሰብ መሰረት በማድረግ ገላጭ የመተንተኛ ዘዴን በመጠቀም የወይባን አዘገጃጀትና አጠቃጠም ክዋኔ ከአውዱ ያገኘኋቸውን መረጃዎች ለመተንተን ተጠቅሜበታለሁ፡፡ እንዲሁም የይዘት ትንተና ስልትን አጣምሬ መጠቀምን የወደድኩት ወይባ ለምትታጠን ሴትና ለማትታጠን ሴት የሚገጠሙ አባባሎችን ይዘት መተንተን እንዲያስችለኝ ነው፡፡

ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ ባህሉ ለባለቤቶቹ ያለውን አላማ ማግኘት፣ ማህበረሰቡ በወይባ ጭስ መታጠን የሚያገኘውን ፋይዳ መተንተን ስለሚጠይቅ ከላይ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የጠቀስኳቸው ዘዴዎችን ተግባር ላይ የዋሉ ሲሆን ጭስ መታጠን የሚያስገኘውን ፋይዳ በስርዓተ ክዋኔው መሰረት በማሳየት የክዋኔውን ሂደት በመመርመር፣ ትዕምርት ያላቸውን ቁሶች በመተርጎምና በመተንተን በማህበረሰቡ አስተሳሰብ መሰረት ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ትንተና በማድርግበት ወቅት መረጃዎችን ያደራጀሁት ማህበረሰቡ ለዘመናት ሲጠቀምበት

በኖረው የጭስ መታጠን ልማድ የጫጉላ ቤት ጭስ መታጠን ፣ የአራስ ቤት ጭስ መታጠን፣ የአዘቦት ቀን ጭስ መታጠን አውድ ተኮር ክዋኔ ተመርቼ እንዲሁም ለአንዳንድ ስርዓቶቹ የሚሰጣቸውን ባህላዊ መጠሪያዎች ላይ ተመርኩዤ ነው።

## 3.4. የመስክ ተሞክሮ ዘገባ

ይህን ጥናት ለማጥናት የመስክ ተግባሬን የጀመርኩት በርዕሰ ጉዳዩ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውንና ይበጁኛል ያልኳቸውን ጥናቶች እንዲሁም ስለጥናቴ አካባቢ የሚያትቱ ጽሁፎችን በማሰባሰብ ነው። በሆኑም አሰሳየን ከምማርበት ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ቤተ-መጸሀፍት የጀመርኩ ሲሆን ጥቂት መረጃዎችን ባገኝም አጥጋቢ ባለመሆኑ የትብብር ደብዳቤ በትምህርት ክፍሉ አጽፌ ከጨረስኩ በኋላ ነሃሴ 27 /2009 ዓ.ም ከደሴ ከተማ በመነሳት ጉዞየን ወደ አዲስ አበባ አድርጌ አመሻሽ ላይ አዲስ አበባ ደርሼ ከዘመድ ቤት አደርኩ። በማግስቱ ጠዋት ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ካምፓስ በመሄድ ከትምህርት ክፍሌ የተጻፈልኝን የትብብር ደብዳቤ በማሳየት በአዲስ አበባ ምርምር ተቋም እና በኬኔዲ ቤተ-መጸሀፍቶች እስከ ጳጉሜ 4 ድረስ አሰሳየን በማድረግ በእኔ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ አጥጋቢ ጥናት ባይኖርም የሚቀራረቡ ሁለት ጥናቶችን በማግኘቴ ከነዚያ መረጃዎችን ይዤ በጳጉሜ 5/2009 ዓ.ም ወደ ደሴ ተመልስኩ። ጥናቴ ባተኮረበት ከተማ የሚኖሩ በስራምክንያት የማውቃቸውን ጓደኞቸን ስልክ በመደወል ባህላቸው በሆነው የወይባ ጭስ እጥነት ላይ ጥናት ልሰራ መሆኑን በመንገር አንዳንድ አስፈላጊ መረጃዎችን ጠይቄ በቀጣይ እንደምመጣ በመነጋገር ቅድመ መስክ ተግባሬን ጀመርኩ።

ከዚያም እንደ መቅረጸ ድምጽ ፣ ፎቶ ካሜራ የመሳሰሉትን የመስክ ቁሳቁሶች ፣በመዋስ ማስታዎሻ ፣እስኪርቢቶ በመግዛት፣ የማህበረሰቡን አለባበስ ለመከተል እችል ዘንድ ድሪያና ቢጃማ በመግዛ ቅድመ መስክ ተግባሬን ጀመርኩ። ከዚያም ጥር 30/05/2010 ዓ.ም ከጠዋቱ በሁለት ሰዓት በደሴ ከተማ መናኸሪያ በመግባት የኬሚሴ ሚኒባስ መፈለግ ጀመርኩ።ወዲያው መኪና በማግኘቴ በ2፡30 የደሴ ከተማ መናኸሪያን ለቀን ወጣን። ከዚያም የሃረጎ ጠመዝማዛ መንገድ በማቋረጥ ሶስት ሰዓት ላይ የኢንዱስትሪ መዲና ከሆነችው ኮምቦልቻ ደረስን ከዚያም መኪናችን የሚወርዱትን አውርዶ ሌላ ተሳፋሪ በመጨመር ጉዞ ጀመርን ኬሚሴ ለመድረስ 10 ኪሎሜትር ሲቀረን መኪናችን ትርፍ ሰው በመያዙ በትራፊክ በመያዙ ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኋላ 5፡30 ላይ ኬሚሴ መናኸሪያ ደረስን። ከዚያም ጓደኛየ ወ/ሮ ሽቱ ነጋ ተቀብላኝ ወደ ቤቷ አመራን ። ከልጆቿ ከዘመድ አብዱሮህማን እና ተስፋየ ጌታቸው እንዲሁም ከልጅልጇ ካሌብ

ሃብተ፡ጋር አስተዋውቃኝ ምሳበልተን ቡና ከጠጣን በኋላ 8፡00 ሰዓት ላይ ወደ ዞን ባህል ቱሪዝም ይዛኝ ሄደች።

እዚያም ሃላፊው በስብሰባ ምክንያት ስለሌሉ ባለሙያዎችን አናግሬ ወደ ኬሚሴ ከተማ ባህል ቱሪዝም ሄድኩኝ። ከዚያም ስንደርስ እንደዚሁ ስብሰባ ናቸው የሉም በመባሌ ስብሰባውም ለ6 ቀናት የሚቀጥል መሆኑን ስሰማ ከጓደኛየ ወ/ሮ ሽቱ ነጋ ጋር ተመልሰን ወደ ኬሚሴ ከተማ ሴቶች ህፃናት ቢሮ ሄድን እዚያም ተመሳሳይ መልስ ስላጋጠመኝ በከተማ ደረጃ ያለው አመራር ስብሰባውን እስከሚጨርስ ለሁለት አመት ያህል ሳስተምርበት የነበረው በዚያ አካባቢ በመሆኑ ለሃገሩ እንግዳ ባልሆንም ከተማዋ ከደረሰችበት የቆዳ ስፋት አንጻር የማውቃቸው መስሪያ ቤቶች የትእንዳሉ ዕውቅት ስላልነበረኝ ከጓደኛየ ሽቶ ነጋ ጋር በመሆን አምስት ቀን ያህል አካባቢውን ሳጠና እና ጓደኛየ የከተማው የሴቶች ፌደሬሽን አመራር በመሆኗ ከሴቶች፡ጋር የመገናኘት እድል ስላላት በእሷ በኩል ለመረጃ ሰጭ የሚሆኑ ሴቶችን የማፈላለግና የመተዋወቅ ስራ እየሰራሁ ሰነበትኩ።

በ05/06/2010 ዓ.ም በዞኑ አስተዳደር ጽ/ቤት ገብቸ የያዝኩትን የትብብር ደብዳቤ በማሳየት የመጣሁበትን አላማ አሳወኩ። ከዚያም ርዕሰ ጉዳየ ወደ ሚያገናኛቸው የዞን ባህል ቱሪዝምና የኬሚሴ ከተማ ባህል ቱሪዝም ስልክ በመደወል በአግባቡ ተቀብለው እንዲያስተናግዱኝ መልዕክት በመንገር ከአንድ ባለሙያ ጋር ወደ ኬሚሴ ከተማ ባህል ቱሪዚም ቢሮ አቀናሁ። ከባህል ስራሂደት ባለሙያ ጋር በመገናኘት የትብብር ደብዳቤ ሰጥቸ የጥናቴን ርዕስ ጉዳይ በማስተዋወቅ ከነሱ የሚጠበቀውን ትብብር እንደሚያደርጉልኝ መልካም ፈቃዳቸውን አግኝቼ ለምሳ ተለያየን ። ከምሳ በኋላ ከሃላፊው ጋር በመገናኘት ባህሉን በጥልቀት ሊያውቁ የሚችሉ መረጃ አቀባዩች እንዲያዘጋጁልንና ጥናቱ በግል በጀት የሚሰራና የእነሱን ባህል ለማስተዋወቅም ድርሻ ስላለው የቻሉትን በእነሱ ሊያግዙኝ እንዲችሉ ሃሳብ አቀረብኩ። በጥናቱ ዙሪያ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች የጽህፈት መሳሪያዎች እና ባህሉን የሚያውቁ መረጃ አቀባዩች እንደሚያዘጋጁልኝ ገልጸው ስለ ወይባ ጭስ አንዳንድ መረጃዎች የያዙ መጽሂቶችን ከሰጡኝ በኋላ በበጀት በኩል ግን እጥረት እንዳለባቸው ገለጹልኝ ።ከዚያም መረጃ አቀባዩች፡ጋር የሚያገናኙኝ ኬሚሴ ባህል ቡድን ውስጥ የምትሰራ አይናለም የምትባል ልጅ እና የወጣት ማህበር ሰብሳቢ ከድር ጋር አገናኝተውኝ ካሜራና አስፈላጊ ማቴሪያሎችን እንዲያሟሉ ና ቁልፍ መረጃ አቀባዩችን ለይተው እንዲድሩ ተግባር ተሰጥተው ለጠዋት ቀጠሮ ይዘን ተለያየን።

በ06/06/2010ዓ.ም ጠዋት በቀጠሮየ መሰረት ኬሚሴ ከተማ ባህል ቱሪዝም ቢሮ ሄድኩኝ ነገር ግን የተቀጣጠርኳቸው ሰራተኞች በሌላ ስራ ምክንያት ባለመምጣታቸው ሌሎች መረጃዎችን ለመፈለግ ወደ ኬሚሴ ከተማ ገንዘብና ኢኮኖሚ የበጀት ስራሂደት በመሄድ የኬሚሴ ከተማ አካባቢዊ ዳራን የሚያመላክቱ መረጃዎችን እንዲሰጡኝ ጠየኩኝ። ከዚያም አቶ ግሩም የሚባል ሰው ከባልደረቦቹ ጋር በሶፍት ኮፒ ያዘጋጃቸውን የተለያዩ ጽሁፎችን በማፈላለግ በጋራ መርጠን ተቀበልኩ። ቀሪ አካባቢያዊ መረጃዎች ከዞኑ ባህል ቱሪዝምና ኮሚኒኬሽን ቢሮ እንደሚገኙ ተጠቁሜ የሚነደለኝን መረጃ በፈለኩት ቀን መጠየቅ እንደምችል ቃል ገብተውልኝ ለምሳ ተለያየን። ከምሳ በኋላ ከልጃቹጋር በኬሚሴ ከተማ ወጣት መአከል ተገናኝተን ቃጩር ወደ ምትባለው የኬሚሴ ከተማ ገጠር ቀበሌ ጫጉላ የገቡ ሙሽሮች በመኖራቸው በባህሉ መሰረት ለጫጉላቤት የሚሰጥ አርቲ፣ አደስ፣ ሽንኮራ አገዳ ፣ለስላሳ በማያዝ በኮንትራት ባጃጅ ሄድን።

ከጫጉላ ቤት ስንደርስ የያዝነውን ስጦታ ለሙሽሪት ሰጥተን ትንሽ ከተቀመጥን በኋላ የመጣንበትን ጉዳይ መንገድ የምትመራኝ አይናለም በኦሮምኛ ቋንቋ ገለጸችላቸው። በተጨማሪ እኔ ለምን መረጃው እንደሚሰበሰብ በአግባቡ አስረድቼ የነሱን መልካም ፈቃድ ካገኝሁ በኋላ ወይባ ጭስ የሚገባው ጠዋት ወይም ማታ በመሆኑ ጭስ የምትሞቅበት ሰአት ምሽት ሰለሆነና አብረውኝ የሄዱት እስከዚያ ሰአት ሰለማይጠብቁኝ ክዋኔውን ሳልጠብቅ ሙሽሪትን ፣ ባለቤትዋን ና የሙሽሪትን ጭስ አሟቂ ባሪያውን ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃ ሰብስቤ ተለያየን ።

በ07/06/2010 ዓ.ም ጠዋት ዞን ባህል ቱሪዝም በመሄድ የተለያዩ ጽሁፋዊ መረጃዎችን በሶፍትኮፒ ተቀብዩ ከአንድ ቁልፍ መረጃ አቀባይ በቃለ መጠይቅ መረጃ ሰብስቤ ወደምሳ ሄድኩኝ ። ከምሳ በኋላ የወለደች አራስ ቤት መጠየቂያ በመያዝ ሄድን ፡፤ ከዚም ጭስ ለመግባት << ሰዓቱ ጠራራ[3] ነው አሁን ጭስ አይገባም እሳቱ ልብ ያደክማል ወጣም ለሚል ሰውም ያማታል[4] >> በማለታቸው ለጠዋት ተቃጥረን መረጃ በቃለ መጠይቅ ሰብስቤ ተለያየን ።

በ08/06/210ዓ.ም ጠዋት በቀጠሯችን መሰረት የጭስ መግባት ስርአት ክዋኔውን እስከ 6፡00 ሰዓት ለማየት ችያለሁ። ከምሳ በኋላ ወደ ሌሎች መረጃ አቀባዩቸ ለመሄድ ልብስ እየቀየርኩ እያለ በቴሌቭዥርን የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ ከሃላፊነት መልቀቅ

[3]<<ጠራራ>> ማለት እኩለ ቀን ፣ ጸሃይ የሚበረታበት ሰዓት ማት ሲሆን የወይባ ጭስ በዚህ ሰዓት አይሞቅም ምክንያቱም ጭሱ ከሙቀቱጋ ተዳምሮ ልብን ሊደክም ስለሚችልና በዚያሰአት ጭስተሞቆ ውጭ ቢወጣ ያማ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡

[44]<< ያማታል >>፤ ማለት ወይባ በጸሃይ ከተሞቀ ሽታ ስላለው ወደ ውጭ ቢወጡ ያማል ለማለት ነው፡፡

ጥያቄ ሲያቀርቡ ስሰማ ልጀን ደሴ ጥያት ስለ ሄድኩ ደሴም ሆነ እኔ ካለሁበት ኬሚሴ ችግር ቢፈጠር ብየ ስለፈራሁ ማታ ወደ ደሴ ከተማ ተመለስኩ። ሁኔታውን እስከ ማይና አንዳንድ ማመቻቸት ያለብኝን ነገሮች እያመቻቸሁ እስከ11/06/2010 ድረስ ይዣቸው የሄድኳቸውን መረጃዎች በየፈርጃቸው ሳደራጅ ቆይቻለሁ።

ሁለተኛውን የመስክ ጉዞየን በ12/06/2010 ዓ.ም በድጋሜ ወደ ኬሚሴ ሄጀ በመንገድ ላይ በተከሰተብኝ አደጋ በመደናገጤ ለ7ቀናት ያለምንም ስራ ጸበል በመጸበል እንዳሳልፍ ተገድጃለሁ። ከዚያም19/06/2010 በመጀመሪያ ጉዞየ በስም ተጠቁሜ የነበሩ መረጃ አቀባዩችን የመተዋወቅ እና ፕሮግራም የመያዝ ስራ ስሰራ ዋልኩ ። በ20/06/2010 ዓ.ም ከተዋወኳቸው ሰዎች አንዱ ወደ ሆኑት ወደ ወ/ሮ ሶፍያ ትዕዛዙ ቤት አቀናሁ። ቤቱ የባህል አልባሳትና ጌጣጌጥ መሸጫ በመሆኑ እስከሚከፈት ድረስ እስከ ሶስት ሰዓት ጠብቄ በየመካከሉ ቁጭ ብድግ ባለበት ሁኔታ ለሶስት ሰዓት ያህል መረጃ በቃለ መጠይቅ ሰበሰብኩ። በመጨረሻም እኒህ መረጃ ሰጪዩ ከሳቸው በተሻለ በዚህ ዙሪያ እውቀቱ ያላቸው እናታቸው ወ/ሮ አሚናት እንደሆኑና ስለጉዳዩም እንደ ሚነግሩልኝ ጠቁመውኝ የቤት አድራሻቸውን በምልክት ተቀብየ ከሳቸው ጋር ለመገናኘት ለጠዋት ቀጠሮ ይዥ ለምሳ ተለያየን።

በቀጠሮዩ መሰረት በ21/06 2010 ጠዋት ከወ/ሮ አሚናት ቤት መንገድ መሪየን ሽቱ ነጋን በመያዝ አቀናሁ። ስንደርስ ሽቶ ወ/ሮ አሚናትን ስለምታውቃቸው አለምንም ችግር ወደቤት ዘለቅን ወ/ሮ አሚናት ታመው እንደተኙ በአንድ ወንድ ልጅ ተነገረን እቤት ገብተን ወ/ሮ አሚናትን እግዚአብሄር ይማርሁ በማለት ትንሽ እንደቆየን እኔን በማስተዋወቅ የመጣንበትን ጉዳይ ወ/ሮ ሽቶ ገለጸች ። ከዚያም እኔ ከዕርስዎ የምፈልገውን ጉዳይ አስረዳሁ። በወቅቱ ወ/ሮ አሚናት ከኔ ጋር ቆይታ ለማድረግ እንደማችሉና በማግስቱ ለ7ቀን ጸበል ሊሄዱ እንደሆነ ነግረውኝ በ28/06/2010 እንድመጣ ቀጠሮ ሰጥተውኝ ተለያየን። በ22/06/2010 ዓ.ም ጀምሮ አስከ ቀን 8/07/06 ዓ.ም ድረስ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ሰፊ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ አካላት ተብለው በተለያዩ ሰዎች የተጠቀሱልኝን ሰዎች በማግኘትና በገበያ ላይ የወይባ ና ወይባ ለመታጠን የሚውሉ ቁሳቁሶች ገበያን ምልከታ ሳደርግ እና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን ሰከውን ሰነበትኩ።

ለቡድን ውይይት ከተመረጡ ቁልፍ መረጃ አቀባዩቸ ጋር ምቹ ቀናትን ሰጠብቅ ሰለነበር 09/7/2010/ ዓ.ም ከርዳሜ እየተባለ ሚጠራው ቀበሌ የህዝብ ስብሰባ እንዳለ እና ሁሉም በዚያ ቦታ እንደሚገኙ ስለነገሩኝ ሁለቱንም የተተኳሪ የቡድን ውይይቱን በተመሳሳይ ቦታና

ቀን ለመከወን ቻልኩ ። ከዚያም ለሶስት ቀናት ያህል መረጃዎቹን በመመልከት የጎደሉ ነገሮች ካሉ ለማተካከል ሳሰናዳ ሰንብቻለሁ። በአጠቃላይ በ13/7/2010/ዓ.ም በሁለት ዙር የመስክ ጉዞ እና 33 ቀን ቆይታ በኋላ ወደ ደሴ ተመልሸ በድምጽ የተቀረጹ ቃለ መጠይቆችንና የተተኳሪ ቡድን ውይይቶችን ወደ ጽሁፍ ቀይሬያለሁ፤ ፍቶ ግራፍችንም አሳትሜያለሁ። በማስታወሻ እና በድምጽ የተሰበሰቡ መረጃዎችንም በማናበብ ጽፉያቸዋለሁ።

## 3.5. ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው

በመስክ ቆይታዬ ወቅት ያጋጠሙኝ ችግሮች ቀላል የሚባሉ አይደሉም። ከነዚህም መካከል በመጀመሪያ ደረጃ የሚቀመጠው ለጥናቴ የሚሆን ገንዘብ የሚሸፈነው በግል ወጭ በመሆኑ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቢሮዎች እና ስፖንስር ያደርጉኛል ብየ ያናገርኳቸው አካላት መልካም ምላሽ ያለማግኘቴ ለጥናቴ የሚያሰፈልገኝን ወጭ ሁሉ እንዳላሟላ አድርጎኛል።


ሁለተኛው ለጥናቴ መረጃ  ሊሰጡ ይችላሉ ብዬ የመረጥኳቸውን መረጃ ሰጪዎች በቀላሉ ማግኘት አለመቻሌ ነው። በመሆኑም አንድ ሰው ለማናገር ከአራት ጊዜ በላይ በተደጋጋሚ እንድሄድ አስገድዶኛል። ሶስተኛ የአካባቢው ማህበረሰብ የእስልምና እምነት ተከታይ በመሆኑ መረጃ ሰጭዎቸ  ቪዲዩና ፎቶ ግራፍ ማንሳት ሃራም ነው እምነታችን አይፈቅድም በማለት ቨዲዩ ሙሉበሙሉ መቅረጽ አለመቻሌ እና አብዘሃኞቹ መረጃ አቀባዩቸን  ፎቶ ግራፍ ማንሳት አለመቻሌ ትልቅ ችግር ሆኖብኛል። ሌላውና አሳዛኙ በሁለተኛ ጉዞየ ወቅት ወደ ኬሚሴ ስሄድ የተሳፈርኩበት መኪና ሃርቡ ላይ በመጋጨቱ እኔ ጉዳት ባይደርስብኝም ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ማየቴና መኪናው ሲወድቅ በመደንገጤ እስከምረጋጋ ለ7 ቀናት ያህል ምንም ስራ ሳልሰራ ከተማው ውስጥ እንድቀመጥ ተገድጃለሁ።

ምንም እንኳን በጊዜው ያጋጠሙኝ ችግሮች ቀላል የሚባሉ ባይሆኑም ለጥናቴ የሚሆን መጠነኛ ገንዘብ ከአማራ ብድር ቁጠባ ተቋም በመበደር እንደልብ ለሁሉም ለመረጃ ሰጭዎቸ መክፈል ባልችልም በተወሰነ መልኩ ችግሬን መሸፈን ችያለሁ። የአካባቢው ማህበረሰብ አብዘሃኛው በንግድስራ የተሰማራ በመሆኑ የተመረጡ መረጃ ሰጭዎችን በተደጋጋሚ ከቤታቸው እና ከስራ ቦታቸው በመሄድ የሚመቻችላቸውን ጊዜ በመጠበቅ ተገቢ መረጃ ማግኝት ችያለሁ ። በቀረጻ በኩል የገጠመኝን ችግር ፈቀደኛ የሆኑልኝን ሰዎች በመቅረጽና ፎቶ በማንሳት  ሰርቻለሁ። ሌላው ለ5 ቀናት ጸበል በመጠመቅ የደረሰብኝን ድንጋጤ እንድረሳና እንድረጋጋ ሆኛለሁ።


# ምዕራፍ አራት

## የኬሚሴ ማህበረሰብ አካባቢያዊ ገጽታና ማህበረ -ባህላዊ ዳራ

### አማራ ክልል የወሎ ኦሮሞ ዞን ካርታ




የኬሚሴ ከተማ ካርታ



## 4.1. የኬሚሴ ከተማ አጠቃላይ ገጽታ

ከሚሴ ከተማ በኦሮሞብሄረሰብ አስተዳደር ዉስጥ ካሉት 5 ወረዳዎችና 2 ከተማ አስተዳደሮች እና በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙ 2ኛ ደረጃ ከተሞች አንዷ ናት። ከተማዋ በምስራቅ የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በምእራብ የሰሜን ሸዋና የደቡብ ወሎ ዞን ፣በደቡብ ከአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፣በሰሜን ከደቡብ ወሎ ዞን ጋር የምትዋሰን ሲትሆን፣ የብሄረሰብ ዞኑ ርእሰ ከተማና የዳዋ ጨፋ ወረዳ መቀመጫ ናት። ( የ2009 የክልሉ ፕላን ኮሚሽን ትንበያ)።

የኬሚሴ ከተማ የተመሰረተችው በ1935 ዓ.ም ሲሆን፣ ቆርቋሪዋም ከአዲስ አበባ እስከ አስመራ የሚሰራውን የአስፓልት መንገድ ለመስራት የመጣው አብደላ ሙሃመድ ሳልሃዲን የተባለው ሱዳናዊ ነው። ‹‹ኬሚሴ›› የሚለውን ስያሜ ያገኘችው ከኦሮምኛ ቃል ሲሆን በከተማዋ ሃሙስ ቀን ከሚውለው ገበያ የተወሰደ ነው። ሃሙስ በኦሮምኛ ኬሚስ በመሆኑ ልዩ መጠሪያዋንም ከዚሁ አግኝታለች ይላሉ። ኬሚሴ ከተማ ከአዲስ አበባ በ 325 ኪሎ ሜትር ከባህር ዳር ደግሞ 565 ኪሎ ሜትር ትርቃለች። የቆዳ ስፋቷ 10.666 ሄክታር ሲሆን 6 የከተማ ቀበሌዎች እና 1 የገጠር ቀበሌ እንዲሁም በ47 ጎጥ የተዋቀረች ናት (አርሂቡ መጽሄት ፤ልዩ እትም ፤2006 ። የ2008 ዓ.ም በጀት ዓመት ስታስቲካዊ የመረጃ መፅሄት)::

ኬሚሴ ከባህር ጠለል በላይ 1450 ሜትር ከፍታ በ25.03.730 ላቲቲዩድ 13.23.8416 ሎንግቲዩድ ላይ ትገኛለች። የኬሚሴ የመሬት አቀማመጥ ዙሪያ ገባዋን በተያያዙ ተራሮች የተከበበችና የጨፋ ስምጥ ሸለቆ አጎራባች ናት። መካከሏ ሜዳማ ስትሆን በግራና ቀኝ የማይደርቁ ወርቄ ፤ቦርካናና ዶሉ የተባሉ ወንዞች ይገኙባታል። የአየር ንብረት ሽፋኗ 85% ቆላማ ሲሆን 15% ወይናደጋ ነው ። በጥቅሉ የኬሚሴ ከተማ አየር ንብረት የሚያመዝነው ሞቃታማ ሲሆን፣ 984 ሚሊ ሊትር የዝናብ መጠን ሽፋን አላት ።

የቀን የሙቀት መጠኗ በከፍተኛ 30 ሴንት ግሬድ ሲያስመዘግብ ዝቅተኛ ደግሞ 25 ዲግር ሴንት ግሬድ እንደሆነ ይገመታል። (የ2008 ዓ.ም በጀት ዓመት ስታትስቲካዊ የመረጃ መፅሄት። ኬ.ከ.ገ.ኢ..ል.ጽ/ቤት የተዘጋጀ ሰነድ 2007፡12)።የኬሚሴ ከተማ ጠቅላላ የህዝብ ብዛት 19,420 ሲሆን ወንድ 9,782 ሴት 9,638 (CSA፡2007)

ከኬሚሴ ማህበረሰብ ውስጥ 95% የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ሲሆን 3% ያህሉ የኦርቶዶክስ ክርስትና ኃይማኖት አማኝ፣ 2 % ደግሞ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች

ናቸው። በከተማዋ 11 መስጅድ፣ 2 የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ሃይማኖት ቤተክርሲቲያን፣5 የፕሮቴስታንት ክርስትና እምነት የአምልኮ ቦታ ይገኝባታል። ኬ.ከ.ገ.ኢ.ል. ጽ/ቤት የተዘጋጀ ሰነድ (2007፡12)።

ኬሚሴ በአማራ ክልል የኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ርዕሰ ከተማ እንደመሆኗ የማህበረሰቡ የስራ ቋንቋ ኦሮምኛ ነው። በመሆኑም 75 %የሚሆነው የማህበረሰቡ ክፍል የአፍ መፍቻ ቋንቋ ኦሮምኛ ሲሆን፣ 22% የአፍ መፍቻ ቋንቋ አማርኛ 3 %የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አርጎብኛ፣ አፋርኛ፣ ትግሬኛ ተናጋሪ የሆኑ ማህበረሰቦች መኖሪያ ናት። በመሆኑም ሁሉም ቋንቋ ተናጋሪዎች በሚገናኙበት በገበያና የተለያዩ ቦታዎች ሁሉንም በማግባባት አማርኛ ቋንቋ ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል(Central Statistical Agency of Ethiopia CSA፡2007 ፣ የኬ. ከ.ባ.ቱ ዳሰሳ ጥናት 2007፡24)

አብዘሃኛው የኬሚሴ ማህበረሰብ የሚኖረው በከተማ እንደመሆኑ የማህበረሰቡ ዋና የኢኮኖሚ መሰረት የሆነው ንግድ ነው። በተወሰነ መልኩ በገጠር የተከለለችው አንድ ቀበሌ ማህበረሰብ ደግሞ በእርሻ ስራ ላይ የተሰማሩና ቅይጥ ግብርናን የሚጠቀሙ ሲሆኑ። ቀሪዎቹ ደግሞ በተለያዩ የመንግስት ስራዎች ላይ ተሰመርተው የሚሰሩ ናቸው። ኬሚሴ ከምትታወቅባቸው ምርቶች ውስጥ ማሽላ ፣ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ሽንኩርትና ማሾ ተጠቃሽ ናቸው። (በኬ.ከ.ን.ኢ.ል.ጽ/ቤት የ2009 ዓ.ም ዳሰሳ ጥናት)::

## 4.2. የጋብቻ ሥነ-ስርዓት

አንድ ህዝብ በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ስርዓቶች ውስጥ የራሱ የሆኑ የባህል እሴቶች አሉት። ከነዚህ እሴቶች መካከል አንዱ የጋብቻ ሥነ-ስርዓት ነው።ጋብቻ የቤተሰብ መመስረቻ አንድ ትልቅ ተቋም እንደ መሆኑ ከአካባቢ አካባቢ ከባህል ባህል የተለየ አከዋወን አለው። ኬሚሴ ውስጥ ሁለት አይነት የጋብቻ ስርአቶች አሉ። እነዚህም አንደኛው የእርፎ መረባ የቆቲ /አርኪፋና የቆቲ ማስደገፍ ሲሆን ሁለተኛው የቅቤ ቀቢ ስርአት /በከተማ የቀለበት ስነ ስርአት/ የሚባለው ነው።(ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች 2009 ፡ 281)

የቆቲ የጋብቻ ስነ ስርአት የወንድ ልጅ አባት ዱብርቲዎችን(አዋቂ ሴቶችን)ይዞ ልጁ ወደ ወደዳት ሴት ቤት እርፎዎችን ቆቲ /ዘንግ / በመያዝ ። የወደዳትን ሴት በቤተሰብ በመለመን የሚከወን ጋብቻ ነው። ይህ ጋብቻ ዱብርቲዎች ቆቲ /ዘንግ በመያዝ ወደ ሴት ቤት በጠዋት ተነስተው ይሄዳሉ። በዚያም በመገኘት እበራፍ ላይ ቆመው ዝምድናችሁን ፈልገናል አላህ

የሰጣችሁን ልጅ አላህ ለሰጠን ልጃችን ትሰጡን ዘንድ ብለን ቆመናል በማለት ልመናቸውን ያሰማሉ ሴት ቤተሰብም ጋብቻውን ካላመነበት እንማከር ብለው ይሰዳሉ ካመኑበት አሸታቸውን ገልጸው ለሌላቀን ተቃጥረው ይለያያሉ ከዚያም በቀጠሮአቸው መሰረት የልጁ አባት ከጓደኞቹ ጋር በመሆን የራስ ወለባ አምባርና ልብስ በመያዝ ሄደው የቀለበት ስርአት ይደረጋል በዚያም ቤት ያፈራን ተጋብዘው የሰርግ ቀን ተቆርጦ ይለያያሉ። ሴት ልጅ አግብታ ስትሞሽርም ወይባ ጭስን መሞቅ የምትጀምርበት ወቅት ይሆናል። በማለት የቆቲ /ዘንግ /የዱበርቲ ጋብቻን ስነ ስርአትን ያሳያል ።

ሁለተኛው የጋብቻ ስነ ስርአት የቅቤ ቀቢ ስነ ስርአት ነው ። በከተማ የቀለበት ስነ ስርአት የሚባለው ዓይነት ሲሆን በዚህ የጋብቻ ስነ ስርአት ወደ ሴት ቤት ለጥየቃ የሚሄደው በመጀመሪያ የወንድ ልጅ አባት ብቻውን ሲሆን ልጃችሁን ለልጀ ፈልጌያታለሁ ይላል። በዚህ ዕለት ወዲያው ምላሽ አያገኝም። እንምከርበት ይባላል። ካልተሳካ ከዚያው ከቤቱ ይላክበታል ። ከተሳካ መልስ አያሰፈልገውም ። በዚህ መሰረት ቀጣይ መቸ ምልክት እናድርግ ተብሎ ቀጠሮ ይያዛል። በዚያም ቀን የወንዱ አባት ሽማግሌዎች እና የሙሽራው እናት ሆነው ቅቤ በመያዝ ከሴት ቤት በመገኘት የወንዱ እናት ሙሽራዋ ከነሚዜዎቿ ቅቤ የመቀባት ስነ ስርአት በማከናወን የስርግ ቀን ቆርጠው ይለያያሉ። (ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች 2009። አቶ አብዱ ሰይድ፣ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት7/2010 ዓ.ም) ይገልጻሉ።

## 4.3. ባህላዊ የአለባበስና አጊያጊያጥ ስርአት

የኬሚሴ ማህበረሰብ የአካባቢያቸውን ባህል የሚያሳውቁበት ከአካባቢው አየር ንብረት ጋር ተስማሚ አለባበስና አጊያጊያጥ አላቸው። እነዚህ አለባበሶች ኮበሌ /ወጣት ወንድ ፣የአዋቂ ወንድ፣ያገባች ሴት፣ የዱበርቲ/ የአዋቂ ሴት/ የታጨች /ያልታጨች ተብለው በመመደብ የሽመና ውጤትና የእደጥበብ ውጤቶችን እያመረቱ የማህበራዊ ደረጃ መለያ በመሆን ያገለግላል ፡ (ሰይድ ይማም (2002) ፣ ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች (2009 ፡ 244)

ያገቡ ሴቶች ከጥጥ የሚሰሩ ጎንደቤና ጋኖ እንዲሁም መቀነት በመታጠቅ ይታወቃሉ። በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ያገባች ሴት መቀነት ትታጠቃለች። ከብርና ከነሃስ የተሰራ <<ጎሃ>> የተሰኘ የአንገት ጌጥ <<ላላ>> ከብር የተሰራ ክብ ቅርጽጌጥ ፣ ጭልጭል፤ የጆሮ ጌጥ ፣ አልቦና ዝርግፍ በመባል የሚታወቁ የእግርላይ ጌጦች መለያቸው ናቸው።ይህን ባህላዊ አለባበስ የለበሰችና የወይባ ጭስ ታጥና የሰውነቷጠረን የሚማርክ ሴት ያገባች ወይም ጾታዊ ግንኙነት

የጀመረች መሆኗ ትታወቃለች። በተጨማሪም ያልታጨች ልጃገረድ መላያ የሆነው ክብ የሆነ ሁለት ብር ብስ አንገቷ ላይ በማተብ ታስራለች ።ጎንደቤና ጃኖ በቶርቢ/ ነጭ ቀበቶ /ታደርጋለች ቶርቢ የተባለበት ምክንያት ከቆዳ የተሰራ ሆኖ እንደ ሳንቲም ወደ ታች ሰባት ነጠብጣብ ያለው ነው።

የወጣት ወንዶችና የአዋቂ ወንዶችእንደዚሁም የሴት ህጻናትና የወንድ ህጻናት  አለባበስን በተመለከተ( ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች( 2009፡ 244)፣ ሰይድ ይማም ( 2002 ) እንደሚከተላው ይገልጸዋል። ወጣት ወንዶች በአለባበስ እረገድ መሰነፍ ከጥጥ በሸመና የሚሰራ ጎንደቤ  ከጥጥ የሚሰራና ከግማሽ በላይ ጥለት ያለው ከላይ የሚለበስ ፣ጥለት ያለው ሚዶ ጸጉራቸው ላይ ይሰካ  በአንገታቸውም ባሩድ ፣ ከሙስበሃ የሚሰራ ብልጭልጭ ጌጥ ብርጨማ እንደትራስ  የምታገለግል ፣ጊሌ የወጣት ወንዶች መለያ ሲሆኑ አዋቂ ወንዶች በአለባበስ አንድ አይነት ሆነው የሚለያቸው  ጸጉራቸውን ጎፈሬ አለማበጠራቸውና ሚዶ አለመሰካታቸው ነው። ከ15 አመት በታች የሆኑ ሴት ህጻናት ከጥጥ የተሰሩ ወጥ ባህላዊ ልብሶችንና በጆሯቸው ጭልጭል ጌጥ በአንገታቸው አንድድ ብርብስ ሲያደርጉ ህጻናት ወንዶች ደግሞ አነስተኛ ሸርጥ ከላይ በሸመና የተሰራ ሸሚዝ መሰል ልብስ ሲለብሱ ጌጥግን አይጠቀሙም ።ሰይድ ይማም (2002 ) ፣ ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች( 2009 ፡ 244)  በማለት የኬሚሴ ማህበረሰብ የአለባበስና አጊያጊያጥ ባህልን ያሳያሉ ።

## 4.4. ባህላዊ ምግቦች

በአማራ ክልል የኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን መዲና በሆነችው በኬሚሴ ከተማ ያሉ የኦሮሞ ህዝቦች እንደ ሌሎች አካባቢዎች ሁሉ የራሳቸው ባህላዊ ምግቦች አሏቸው። ይህን እመልከቶ ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች (2009 ፡ 303) እንደሚከተለው ይገልጻል በአካባቢው የሚታውቁ  ባህላዊ ምግቦችን በሶስት ከፍሎ ማየት የሚቻል ሲሆን ቡርቁምሳ ፣ ጨጨብሳ ፣ገንፎ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው ።በተጨማሪም ሚጁ/ ወተት ፣ደራራ/ የማሽላ ንፍሮ / ይጠቀሳሉ ።እነዚህ ምግቦችም የራሳቸው የአዘገጃጀት ስርአት ያላቸው ሲሆን ለምግብነት የሚቀርቡበትም ወሳኝ የሆኑ ጊዜያት አሏቸው ።በጠጨማሪም ምግቦቹ ከወይባ እጥነት ጋር አብረው የሚቀርቡ በመሆናቸው አንድ በአንድ ተዳሰዋል ።

**/ቆሎ/ ብርቁምሳ**

ከገብስ የሚሰራ ሲሆን የተመረጠ ገብስ ተፈትጎና ተቆልቶ በቅቤ፣ ማርና ቅመማቅመም በማሸት ለምግብነት የሚውል ሲሆን በቀለበት ስነ ስርአት ጊዜለሚመጡ ሽማግሌዎች ከቡናጋር የሚቀርብ ነው። ይህን ባህላዊ ምግብ በአዘቦትና በጫጉላ ቤት የወይባ ጭስ የምትሞቅ ሴት ከጭስ ከወረደች በኋላ ተጣጥባ አረፍ ባለችበት ሰዓት የምትቆረጥመው ነው። ይህ ምግብ በቅቤና ማር የታሸ በመሆኑ በወይባ ጭስ እጥነት ላብ የፈሰሳት ሴትን ሃይል የሚተካ ተደርጎ ይወሰዳል ።

**ጨጨብሳ**

ጨጨብሳ ከቂጣና ቅቤ የሚዘጋጅ ሲሆን አብዘሃኛውን ጊዜ ለክብር እንግዳ የሚቀርብ ምግብ ነው። (አቶ አብዱ ፣ሰይድ፣ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት7/2010 ዓ.ም) ዓ.ም << ጨጨብሳ እንደ ክብር እንግዳው ዓይነት አሰራሩም የተለየ ነው ። የክብር እንግዳው ቀለል ያለ ከሆነ ቂጣው ተጋግሮ በቅቤ ተለቅልቆ ከወተት ጋር ሲቀርብ እንግዳው ከበድ ያለ ከሆነ ቂጣው በቅቤና በርበሬ እየተነከረ ተፈትፍቶ ከወተት ጋር ይቀርባል ። ጨጨብሳ ብዙ ጊዜ የሚሰራው ለአባወራ ሲሆን ለልጆች የሚዘጋጅ አይደለም >> በማለት ጨጨብሳ የክብር ምግብ እንደሆነ ያሰረዳሉ። በተጨማሪም ጨጨብሳ ጫጉላ ቤት ያለች ሙሽራ ወይባ ጭስ ለመሞቅ ስትገባና ስትውጣ ትኩሱን እየተዘጋጀ እንድትመገብ የሚቀርብ ምግብ ነው

**ገንፎ**

ገንፎ ከገብስ የሚሰራ ሲሆን የጋብቻ ጥያቄ ሲመጣ ፣ በወዳጃ ጊዜ ፣ በቀለበት ስነ ስርዓት ወቅት፣እንዳሰፈላጊነቱ ጠዋት ጠዋት፣ የጋራ ጉዳይ ሲኖርና ብዙሰው በሚሰበሰብበት ጊዜ የሚቀርብ ምግብ ሲሆን ገንፎ አንድነትን ይፈጥራል፣ ጉዳይን የጋራ ያደርጋል ተብሎ ይወሰዳል። በዚህ ማህበረሰብ ግንፎ የወይባ ጭስ ለመሞቅ የምትገባ ሴት የምትመገበው ምግብ ሲሆን በተለይ በአራስ ቤት ለሚከወነው የወይባ ጭስ እጥነት በቀዳሚነት የሚወሰድ ምግብ ነው። አራስ ሴት ወይባ ጭስ ስትገባም ሆነ ስትወጣ ትኩስ ገንፎ እንድትመገብ ይደረጋል።

**ወተት /ሚጁ/**

ወተት በማህበረሰቡ ሚጁ በመባል ይጠራል ። ሚጁ በተለያየ ስርዓትና ወቅት ላይ የሚቀርብ ነው። ለምሳሌ በወዳጃ ስርአት ጊዜ፣ በቀለበት በጋብቻ ስነስርአት ወቅት ጮጮ በተባለች ቅል የሚቀርብ ሲሆን መልካም ኑሮን የመመኘት ጣፋጭና ያማረ ይህይወት እንዲኖራቸው የመልካም ምኞትመግለጫ በመሆን ያገለግላል ። በአተቃላይ እነዚህ የባህል ምግቦች በኬሚሴ ማህበረሰብ የክብር ምግብ ከመሆናቸው ባሻገር ከጫጉላ ቤት ጀምሮ ወይባ ለምትሞቅ ሴት ሰውነቷ እንዲጠገን ተዘጋጅተው የሚሰጡ ምግቦች ናቸው ። ጨጨብሳ እና ገንፎ ወይባ ጭስ ከመግባት በፊትና በኋላ የሚበሉ ምግቦች ሲሆኑ ደራራ ከወይባ ከወረደች በኋላ የሚበላ ምግብ ነው። ደራራ ከማሽላ የሚሰራ ንፍሮ ሲሆን በጣም ሳይበስል በማውጣት ወይባ ታጥና የወጣች አራስ ሴት ትኩስ ትኩሱን የምትመገበው ነው።(አቶ አብዱሰይድ፣የቡድን ውይይት፣መጋቢት 9/2010ዓ.ም)።

# ምዕራፍ አምስት

# የመረጃ ትንተና

በዚህ ርዕስ ስር የጥናቱ አብይ ጉዳይ የሆነው በኬሚሴ ከተማ የወይባ ጭስ አዘገጃጀት አጠቃቀምና የጤና ፋይዳ ጭስ ከመሞቂያ  አውዶች አንፃር ተተንትኖ ይቀርባል፡፡ ከቃለ-መጠይቅ፣ ከምልከታ እና  ከተተኳሪ ቡድን ውይይት የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ሲሆን፣ እነዚህ መረጃዎች በመልክ በመልካቸው ተደራጅተው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 5.1. የወይባ ጭስ ምንነት

ወይባ የሚለው ቃል ስያሜ አንዳንድ የሃይማኖት አባቶች የግዕዝ ቃል እንደሆነና ‹ወየበ› ከሚል የግስ ቃል የተመሰረተ ሲሆን፣ ትርጉሙም መልኩን ቀየረ፣ ተለወጠ፣ ቢጫ ሆነ ማለት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ እንደ መረጃ አቀባዩቼ ገለጻ እና እኔም በምልከታዩ ወቅት እንዳየሁት ወይባ በሚል ሰያሜ የሚጠራው የዛፍ አይነት እንደ ስያሜው ከቅርፊቱ ጀምሮ እስከ ፍልጡ ድረስ ቢጫ ቀለም ያለው ነው፡፡ ወይባ እንጨት በሳይንሳዊ ስሙ terminalia brownie fresen ሲባል በአርጎብኛ "መልሆ" በመባል ይጠራል፡፡ የወይባ እንጨትን ባህሪና በኬሚሴ ማህበረሰብ ያለውን ተግባር በተመለከተ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

የወይባ ዛፍ በቆላማና ደረቅ የአየር ንብረት ባለበት አካባቢ የሚበቅል ረጅም ጊዜ ይቆያሉ ከሚባሉ ትልልቅ ዛፎች ተርታ የሚመደብ ሲሆን፤ ከአመት እስከ አመት ከላዩ ላይ ቅጠል የማያጣ፣ ድርቅን የማይፈራ ቅርንጫፈ ብዙ ዛፍ ነው፡፡ የወይባ እንጨት በውስጡ የሚይዘው እርጥበት ከፍተኛ ወዝ ያለው በመሆኑ ተደራራቢው የውስጠኛው የግንድ ክፍል የማጣበቅ ባህሪ ያለው ነው፡፡ ከእንጨቱ የሚወጣው ጭስም ከሌሎች እንጨቶች በተለየ ጥሩ ሽታ ያለውና በሰውነት ላይ ሲያርፍ መልክን ወደ ቢጫነት የመቀየር ሃይል ያለው ተክል ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ ሁሴን ኢብራሂም፣የቡድን ውይይት፣መጋቢት 9/ 2010 ዓ.ም) ሲገልፁ፡-

‹‹የመልሆ ዛፍ እንደ ዋርካ ነው፡፡ ቅርንጫፉ አገሩን ነው የሚያለብሰው ከጥላው ሽምግልና እንውልበታለን እረኞች ያርፉበታል፡፡ ደግሞ ስንቆርጠው እንጨቱ እራሱ ወዝ አለው፡፡ ወዙ እጃችን ላይ ነው የሚቀረው፡፡ ውስጡ ታዲያ ህርድ[5] ነው የሚመስለው፡፡›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

[5] ‹‹ህርድ›› እንደመረጃ አባዩ አገላለጽ ( እርድ) ማለት ስሆን ቢጫቀለም ያለው ለተለያዩ ምግቦች ሲሰሩ የመልክ መቀየሪያነት የሚያገለግል ነው፡፡



ፎቶ 3 የወይባ ዛፍ በወ/ሮ ፋጡማ ይማም ግቢ (ፎቶ በአጥኚዋ)

እጾች እንደ ባህሪያቸው ከሃገረሰባዊ መድሃኒት መቀመሚያ እስከ ተለያዩ ቁሶች መስሪያ አገልግሎት ላይ ይውላሉ ። በመሆኑም፣ በኬሚሴ ማህበረሰብ ወይባ እንጨት ዘርፈ ብዙ ተግባሮች ያሉት ተክል ነው። ከተግባራቶቹ ውስጥ ቀዳሚውን ቦታ የሚያዘው የተለያዩ ችግሮቻቸውን ለማቃለል ጭሱን ለእጥነት በመዋል በርካታ በሽታዎችን ፈውስ በመስጠትና ቀድሞ ለመከላከል ይጠቀሙበታል ። ቅጠሉንና ቅርፊቱን በማጨስ እርኩስ መንፈስን ለማራቅ ይረዳል በሚልም ይገለገሉበታል። በተጨማሪም፣ ወይባ ዛፍ እንደሌሎች እንጨቶች ሁሉ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶችን ለመስራትም ያገለግላል።ለምሳሌ ያህል ግንዱን ለበር፣ ለሙቀጫና እጅ መሳሪያዎች መስሪያነት ያገለግላል ። እንጨቱ ከፍተኛ የሆነ እርጥበትን የመያዝ አቅም ያለው በመሆኑ አገልግሎቱም ይህንኑ ባህሪውን ተከትለው ለሚፈለጉ ተግባራት ይውላል።

ይህን አስመልክተው (አቶ ሃሰን ሙሃመድቃሰ መጠይቅ መጋቢት1/2010 ዓ.ም) ‹‹ ወይባ ጠንካራ ነው የቤት መዝጊያ የሆነ እንደሁ ማንም አይነቀንቀውም ። ለሞፈር ፣ ለእርፍ ፣ ለዛቢያ ፣ ለሙቀጫ ፣ለደንጎራ ይሆናል። በሬ ስለሚጎዳ ለቀንበር ግን አይሆንም። ደርቆም ስለማይቀል ቀንበር አናደርግም።›› በማለት የገለጹት ሃሳብ የሚያሳየን ማህበረሰብ ወይባ ክብር የሚሰጠው ዛፍ ከመሆኑ የተነሳ ለአልባሌ[6] ነገር አይቀረጥም። በመሆኑም በዚህ ጥናት ትኩረት

[6] ‹‹አልባሌ›› በወሳኝነት የማያስፈልግ ማለት ነው። ከጥንት ጀምሮ በኬሚሴ ማህበረሰብ የወይባ ዛፍ እንደማንኛውም ዛፍ ወሳኝ ላልሆነ ጉዳይ ቅድሚያ ለማይሰጠው ተግባር ምሳሌ ለማገዶና ለአጥር፣ አይቀረጥም ። ምክንያቱም የወይባ እንጨት ከዚህ በላይ ቅድሚያ የሚሰጡ የተለያዩ በሽታዎችን በመፈወስ የጤናቸውን

ተሰጥቶ በሚዳሰሰው የወይባ ጭስ እጥነት እናጭሱን ለመሞቅ የሚያስፈልጉ ቁሶች ያለቸው ዝምድና እንደሚከተለው ተቃኝቷል፡፡

## 5.2. የማጠኛ ቁሳቁሶችና ውክልናቸው

የወይባ ጭስ እጥነት ሲከወን በቀዳሚነት የሚያስፈልጉና የማይለያዩ የአንዱ መጥፋት ለእጥነቱ አለመከወን ምክንያት የሚሆኑ እርስ በእርስ የተቆራኙ አራት ቁሶች ያስፈልጋሉ፡፡ ቁሶቹ በማህበረሰቡ አኗኗር ልማድ ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው በመሆናቸው የሚታወቁበት ተምሳሌታዊ ውክልና አላቸው፡፡ እነዚህም ቁሶች ወይባ እንጨት ፣ ለጋ ቅቤ ፣ ከሌ ወይም ብርድ ልብስ፣ ቦለቅያ ወይም ድስት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህን ቁሶች ማህበረሰቡ ባህሉን ጠብቆ በቤቱ የሚያዘጋጃቸውና ከገበያ የሚገዛቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም፣ ቁሶቹ ከመታጠን ጋር ያላቸውን ዝምድና ከዚህ በመቀጠል አንድ በአንድ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 5.2.1.የወይባ እንጨት በእጥነት ውስጥ

ወይባ እንጨት ጭስ ለመታጠን ከሚያስፈልጉ ቁሶች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሰ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ለእጥነት የተመረጠበት ዋናው ምክንያቱም ከእንጨቱ ባህሪ የተወሰደ ነው፡፡ የወይባ እንጨት እርጥበታማና ወዛም ከመሆኑ የተነሳ በማህበረሰቡ እሳቤ የማለምለም፣ የማራባት/ማብዛት/ ተምሳሌት አለው፡፡ ከቅጠሉ እስከ እንጨቱ ያለው የእርጥብነት ፣ቅጠል ያለማርገፍና የወዛምነቱ ጋር ተያይዞ ሴቶችን እንደገና የማደስ፣ የማንጻት፣ ዘርን የመተካት ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህን አስመልክቶ (አቶ ሁሴን ኢብራሂም፣የቡድን ውይይት፣መጋቢት 9/ 2010 ዓ.ም) ሲገልፁ፡- ‹‹ዛፉ ምን በጋ ቢሆን ቅጠል አያረግፍም ጥላው የተለየ ነው፡፡ ጸሀይ አይፈራም ወዛማ ነው፡፡ ሴቶች ሲሞቁት እንደ ዛፉ ወዝ ይተፋባቸዋል፡፡ አይነጡም፡፡ ሰውነታቸው ይታደሳል፡፡›› በማለት የገለጹት ሃሳብ የሚያሳየን የወይባ እንጨት ለእጥነት እንዲያገለግል ተደርጎ ሲወሰድ አብረው የሚነሱት ለእንጨቱ መገለጫዎች የተሰጠው ባህሪ ከጭሱ ጋር እንዲቆራኝ አድርጎታል፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ ከወይባ ላይ ያለው እምነትና ቁርኝት የጠበቀ መሆኑን ያሳየናል፡፡

---

የሚጠብቁበት ነው ፡፡ በአሁኑ ሰአት በተለያዩ አካባቢዎች እንጨቱ ተፈላጊ ከመሆኑ የተነሳ ገበያ በማውጣት ገቢ የሚያገኙበት በመሆኑ ትላልቅ የወይባ ዛፎች ጭምር እየተቆረጡ በመጥፋት ላይ ናቸው፡፡

### 5.2.2. ቦለቅያ በእጥነት ውስጥ

ወይባ ጭስን ለመታጠን ከሚያስፈልጉት ቁሶች አንዱ ቦለቅያ ነው፡፡ ቦለቅያ የሚለው የኦሮምኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ‹‹ቦለ›› ማለት ጉድጓድ ሲሆን ‹‹ቀያ›› ማለት የወይባ እንጨት ጪስ ማለት ነው፡፡ ቦለቅያ ለጭስ መሞቂያነት የተዘጋጀ ክብ ጉድጓድ ነው፡፡ ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች ( 2009 )፡፡ ቦለቅያ የአርጎባ ብሄረሰብ ያገቡ ሴቶች ውበታቸውን ለመጠበቅ የሚጠቀሙበት የጭስ መሞቂያ ጉድጓድ ሲሆን ጭሱ ‹‹ወይባ ጭስ›› በመባል ይታወቃል ፡፡ ወይባ ጭስ የተባለበትም ምክንያት ሴቶቹ የሚሞቁት ‹‹ወይባ›› የተባለ የእንጨት ፍላጭ በመሆኑ ነው (አብዩ አስማማው፣ 2000)፡፡

በኬሚሴ ከተማ ወይባና ቦለቅያ የማይነጣጠሉ በገቡበት ቤት ሁሉ የሚያገኙት ባህላዊ ቁስ ነው፡፡ (ወ/ሮ አስማ ሙሀመድ፣ቃለ መጠይቅ፣ የካቲት23/ 2010 ዓ.ም) እንደሚሉት ‹‹ሴት ከቤቷ ቦለቅያ ከሌለ ምኑን ሴት ሆነች ልጅ፤ ቦለቅያ እንደ አንድ የማጀት መጠቀሚያዋ በመሆኑ ሆን ብላ የምታሟላው እቃ ነው፡፡›› በማለት ቦለቅያ በአብዛኛው ቤት የምናገኘው ቁስ መሆኑን ያሳዩናል፡፡ ቦለቅያ የወይባ ጭስ በሚሞቅበት ጊዜ ጭሱን አፍኖ በመያዝ ለረጅም ሰዓት እሳቱ ሳይጠፋ ወይም በጣም ሳይነድ እየጨሰ ለማቆየት ያገለግላል ፡፡

ጭሱ በቦለቅያው ግርግዳ ታፍኖ ስለሚያዝ ታጣኟ በእሳት ሳትለበለብ ጭሱ በቀጥታ ወደ ሰውነቷ እንዲወጣና እንዲያጥናት የሚገለግል ነው፡፡ በምልከታዩ ወቅት እንዳየሁት ቦለቅያ አሰራር እንደየተጠቃሚው ፍላጎት የተለያየ ነው፡፡ ንፋስና ጸሃይ በማይደርስበት የቤት ግድግዳን ተደግፎ ከአፉ ጠበብ ያለ ክብ ጉድጓድ በታጣኟ ሴት ሰውነት ልክ ይቆፈራል፡፡ ከዚያም ከጫፉ ላይ ለእግር ማሳረፊያ የሚሆን እንጨቶች ይጋደማሉ፡፡ ከጉድጓዱ ጫፍ ላይ ለመቀመጫ የሚሆኑ እንጨቶች ይረበረባሉ ፡፡

ከዚያም ዙሪያውን በጭቃና በጭድ ይመረጋል ፡፡ ለጭስ መከለያነት የሚሰራው ግድግዳ እንደየቤቱ የተለያየ ሲሆን አንዳንዱ ተጠቃሚዋ ተቀምጣ እሰከ አገጪ ድረስ የተገነባ ሲሆን ይህን በአገሬው አጠራር የቁም ቦለቅያ በማለት ይጠሩታል ፡፡ ይህ የሚያገለግለውም ጭስ የምትሞቀው ሴት በእሳቱ ላይ ለረጅም ሰዓት ያለምንም መሰላቸት ስትፈልግ ወደኋላዋ ስትፈልግ ወደ ፊቷ እየተደገፈች እንድትቆይ የሚያደርግ ነው፡፡ ሁለተኛው እስከጉልበት ድረስ ብቻ ጭሱን ለመከለል የሚገነባ ሲሆን በአብዛኞቹ ሴቶች ቤት የሚገኘውም በዚህ ዓይነት አሰራር የተገነባው ቦለቅያ ነው፡፡

መቀመጫ





ፎቶ  የቦለቅያ አይነቶች ( ፎቶ በአጥኝዋ)

(ወ/ሮ አስማ ሙሃመድ ቃለመጠይቅ፣ የካቲት23/2010 ዓ.ም) ስለ ቦለቅያ አሰራር እንደሚከተላው ይገልጻሉ፡-

> *አዘገጃጀቱ መጀመሪያ ጉድጓድ ይቆፈራል፡፡ ይህ ይበቃል ተብሎ ልኩ ይገመታል፡፡ ከዚያም ጭቃ ተቦክቶ በጭድ ይመረጋል፡፡ በመቀመጫ ልክ ዘናብሎ እንዲያስቀምጥ ሆኖ ተቆፍሮ ይሰራል፡፡ የቁም ቦለቅያ የሚባልም አለ፡፡ የቁም ይባል እንጅ ተቀምጠን ነው፡፡ ቁጭ ብለን አገጫችን ድረስ ሶስት እንጨት ይቆምና እንደ ጌጥ ተሸልሞ ይዘጋጃል፡፡ በእንጨቱ ልክ በመስመሩ ወደ ላይ በጭቃ ይዘጋል፡፡ ከስርም እግር እንዳይታይ ይመረጋል፡፡ እቤቷ ቦለቅያ ያላት ልባም ሴት ናት ፡፡ ቦለቅያዋን ምርግ ፣ልቅልቅ ፣ ጥርግርግ አድርጋ ታሰቀምጣለች ይኸ በድስት የሚሞቀው መለብለብ እንጅ መሞቅ አይባልም ፡፡*

በማለት ከአዘገጃጀቱ  በተጨማሪ ማህበረሰቡ ለቦለቅያ ያለውን ክብር ገልጸውታል፡፡ ቦለቅያ በጭቃ ገንብቶ በመስራት በተከታታይ መሞቂያ በማድረግ ጭስ የጠገበ ወይንም ጠንካራ እንዲሆን ይፈለጋል፡፡ ይህ የሚሆነው ማህበረሰቡ እምነት ቦለቅያዋ በጭስ ጠቁሮ ወዝ በመያዝ የሚያብለጨልጭ፣ ጠንካራና በቀላሉ የማይፈነቀል ከሆነ የታጣኗ ሰውነትም እንደ ቦለቅያው የጠነከረ /የደረጃ/ ይሆናል በማለት ሴት በቦለቅያዋ ትመሰልበታለች፡፡ አንድ ሴት ጭስ አዘውትራ ስለመታጠኗ የቦለቅያዋ መልክ ይናገራል፡፡ ይህን አስመልክቶ ወ/ሮ አስማ ሙሃመድ ቃለመጠይቅ፣ የካቲት 23/2010  ‹‹ ቦለቅያዋ በጭስ የጠገበ ሴት ሰውነቷም እንደቦለቅያው የደረጀ ነው፡፡ ጭስ የጠገበ ሰውነት በቦለቅያው ይታወቃል ፣ ቦለቅያዋ ቅቤ እንደጠገበ ቅል የሚያበራ የሆነ እንደሁ አከላቷም እንደዚያው ነው፡፡›› በመሆኑም ይህ ባህሪውና ከቦለቅያ

አሰራር ጋር አያይዘው የሚሰጡት ተምሳሌት ቦለቅያ ለወይባ ጭስ መታጠኛ የሚውል የተመረጠ ቁስ እንዲሆን አስችሎታል ።

በቤታቸው ቦለቅያ የሌላቸው በተለይ በስራ ምክንያት ከሌላ ቦታ የመጡ ሴቶችና ኮንዶሚኒየም የሚኖሩ ሴቶች የቦለቂያ መስሪያ ቦታ ችግር የተነሳ የሚጠቀሙበት በማህበረሰቡ አጠራር የቦለቅያ መሞቂያ ድስት እየተባለ የሚጠራ ሸክላ ድስት ነው። ይህ ቁስ ከገበያ ላይ የሚገዛ ሲሆን አሰራሩ እንደማንኛውም ድስት ክዳን ያለው ሆኖ ዙሪያው የጭስ መውጫ የሚሆን ሽንቁር ያለው ሲሆን የቦለቅያን አገልግሎት ተክቶ ሲጠቀሙበት ይስተዋላል።

### 5.2.3. ለጋ ቅቤ በእጥነት ውስጥ

ለጋቅቤ ወተት ተንጦ[7] የሚወጣው ትኩስ ቅቤ ነው። ለጋ[8] ቅቤ ወይባጭስ ለመሞቅ ከሚያስፈልጉ ነገሮች ውስጥ አንዱ ሲሆን በአደስቅጠል በመለወስ ማህበረሰቡ ዘወትር እንደቅባት ይጠቀሙበታል። ለጋ ቅቤ ወይባ ጭስ ሲሞቅ ከእራስ ጸጉር ጀምሮ እስከ እግር ጥፍር ድረስ የሚለቀለቅ / የሚቀባ / ነው። ጭስ የምትገባው ሴት እሳቱ እንዳይጎዳት ከእጥነት በፊት በመለቅለቅ የሰውተቷን ሙቀት ምትቆጣጠርበት ሲሆን ከእጥነት በኋላ ደግሞ የሰውነት ሙቀቷን ለማብረድና በላይዋ ላይ የተቀብቶ የነበረውን የቅቤ ወዝ እና ላብ ለማውረድ ስውነትን በውሃ መታጠብ የሚከናወን ይሆናል ። በተጨማሪም ለጋ ቅቤ የምትለቀለቀው እሳቱ እንዳይጎዳትና ገላዋ እንዳይንደበደብ ሲሆን በእጥነት ላይ እያለች ከምትጠጣው ትኩስ ፈሳሽ ጋር ተዳምሮ ቅቤው እየቀለጠ ከጭሱ ጋር በመዋሃድ በሰውነቷ ላይ ባሉ ቀዳዳዎች በመግባት ውስጣዊ አካሏን በማራስ ቆዳዋ እንዲዘና እና እንዲለሰልስ ያደርገዋል።

ቅቤው ሰውነቷን በማፍታታት ጭሱን እንዲቀበል ያመቻችላታል። በመሆኑም ማህበረሰቡ ለለጋ ቅቤ ያለው አመለካከት የጠበቀ ነው። ለጋነት በማህበረሰብ የአዲስነት፣ የልጅነት፣ ንጹህነት፣ ተምሳሌት ያሳያል ። በመሆኑም ለጋ ቅቤን ከሌሎች ቅባቶች ለይቶ ለወይባ ጭስ እጥነት እንዲውል ይመርጡታል። ጭስ የምትገባው ሴት በለጋው ቅቤ መታሸት አዲስነቷን ፣ ንጽሃትዋን ፣ ያመላክታል ። ታጣኟ እንደ ቅቤው አዲስ ያማረችና የለመለመች ትሆናለች ተብሎ ይታሰባል ። በመሆኑም በዚህ ማህበረሰብ ለጋ ቅቤን ጭስ ሲሞቅ በሰውነት ላይ መቀባትና ማሸት የተለመደ ነው። ይህም ጡንቻን ለማፍታታት የደም ስሮች እንዲዘና የደም

[7] ‹‹ ተንጦ›› ማለት ወተቱ ተገፍቶ፣ቅቤ እንዲወጣው ተነቅንቆ፣ ተወዝውዞ ማት ነው።

[8] ‹‹ ለጋ›› ማለት በዚህ ጥናት ማህበረሰብ አዲስነት ፣ልጅነት፣ ንጽሃን ያመላታል ።

ዝውውሩ ጤናማ እንዲሆን ለማድረግ እንዲረዳ ታስቦ ይመስላል ። ይህን አስመልክቶ (ወ/ሮ ፋጡማ ይማም፣ ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት 4/ 2010ዓ.ም) እንዲህ ይገልጹታል

> *ወይባ የምትታጠን ሴት ከቤቷ ቅቤ አታጠፋም እቤት ከታለበ ማሻ አላሁ[9] ነው። ካልሆነ ከገባየ ግዝት አድርጋ እንዳይበላሽ /እንዳይበስል / በጮጮዋ ታስቀምጣለች ታዲያ ለሳምንት ቀድር( ለአንድ ሳምንት ያህልማለት ነው ) የሚሆናትን ነው ከዚያ ካለፈ ይበስላል ለመቀባት አይሆንም ያማታል[10]። ጅስሟ[11] በለጋው ቅቤ እሽት ሲደረግ እንደ አዲስ ይለመልማል።*

ይህ የሚያሳየን በጭስ እጥነት ወቅት ለጋ ቅቤው ከጭሱ ጋር የሚፈጥሩት ውህደትና ጠቀሜታ አለው። በጭሱና በሙቀቱ የላላውን ገላ የተለየ መጥፎ ጠረን በሌለውና በአፍላ፣በለጋና በወጣትነት በተመሰለው ለጋ ቅቤ ከመታጠን በኋላ መታሸቷ ለታጣኟ ከፍተኛ ስነ- ልቦናዊና ፋይዳ ያለው ከመሆኑም በላይ በመታጠን ምክንያት የተፈጠረውን ከፍተኛ ሙቀት ለማመጣጠንና ጡንቻዎችንና የደም ስሮችን ለማፍታት ታስቦ የሚከወን ነው። በዚህም ወይባ እጥነት ያለ ለጋ ቅቤ የሚሞከር ባለመሆኑ እንዳይለያዩ ሆነው የተገናኙ ናቸው ።

---

[9] ‹‹ማሻአላህ›› ማለት አረብኛ ቃል፣ ሲሆን በጣም ጥሩነው ማለት ነው።

[10] ‹‹ያማታል ›› ማለት በጸሃይ ሲወጡ ያማል ማለት ነው።

[11] ጅስም ፣ ማለት ቃሉ አረብኛ ሲሆን ሰውነት ማለት ነው ። የሴት ልጅ ሰውነት በለጋ ቅቤ ከታሸች ወዘነዋ ያማረ ለስላሳ ቆዳ ያላት እንድትሆን ያደርጋ ል።





**ፎቶ-6 የለጋ ቅቤ ማያዣ ጮጮ እና የለጋ ቅቤ ገበያ በኬሚሴ (ፎቶ በአጥኝዋ)**

## 5.2.4. ጀንዲ (ከሌ) በእጥነት ውስጥ

ከሌ ለእርድ ከቀረቡ የከብቶች ቆዳ የሚገኝ ሲሆን፣ ከብቶች ከታረዱ በኋላ በአግባቡ በባለሙያ ተወጥሮና ተለስልሶ የሚዘጋጅ ነው፡፡ እንደ ጨርቅ የለሰለሰ ጀንዲ (ከሌ ) እቤት ካለ ከቤት ካልሆነም ከገበያ በመግዛት እንደአስፈላጊነቱ ለአገልግሎት እንዲውል ይደረጋል፡፡ ተጠኝ ማህበረሰቦች እንደሚገልጹት በጥንት ጊዜ በአብዛኛው አገልግሎቱ ለመተኛ /ለምንጣፍ /እና ወይባን የሚሞቁ ሴቶች ለመጀቦኛ የሚያገለግል ዋና ቁስ ነው፡፡ ከሌ በማህበረሰቡ የጥንካሬና የዘላቂነት ተምሳሌት ያለው ነው በመሆኑም፣ ሴት ልጅ ተድራ ስትሄድ ከቤተሰቧ ቤት በስጦታነት ተበርክቶ የሚሄድ ሲሆን በዚያ ላይ ሙሽሮች አብረው የሚተኙበት ይሆናል፡፡ በዚያም ከሌ ሙሽሪት ወይባ ጭስን ተጀቡና ትሞቅበታለች፡፡ ለወይባ እጥነት የተመረጠበት ምክንያት ወይባ ጭሰ በከሌ ተጀቡና የምትሞቅ ሴት ጭሱን ወደ ውስጥ ይዞ በማፈንና ከፍተኛ ሙቀት በመፍጠር ሰውነቷ በላብ እንዲዘፈቅና ጭስ በአግባቡ እንዲጠግብ ያደርጋል ፡፡

በዚህም የተነሳ ሰውነቷ እንደ ከሌው የለሰለሰ ይሆናል በማለት ከሌሎች መሸፈኛዎች ተለይቶ እንዲመረጥ አድርጎታል ፡፡ በመሆኑም፣ በእጥነት ስርአቱ ውስጥ የከሌ አገልግሎት ከቦለቅያ የሚወጣውን ጭስ ዙሪያውን አፍኖ በመያዝ ወደ ሌላ አቅጣጫ ሳይበተን በቀጥታ በታጣኟ ብልትና ሰውነቷ ላይ ባሉ ቀዳዳዎች እንዲገባ በማድረግና ከፍተኛ ሙቀት በመፍጠር ሰውነቷ ላብ እንዲያመጣ ያደርጋል፡፡ የወይባ ጭስ በከሌ የምትሞቅ ሴት ነፋስ ሳያገኛትና ከላይዋ ላይ ተጣብቆ ሳያቃጥላት ዘንታ እንድትሞቅ ያስችላታል፡፡ ወ/ሮ ሃዋ ሙሃመድ ቃለመጠይቅ ፣ መጋቢት 8/2010 ዓ.ም እንደሚሉት፡-

*ዛሬ ብቻ ሳይሆን በአባቶቻችን ጊዜ ከሴ የወግ እቃነው ። በክብር ቅባት እየተቀባ ወዝ እንዲያነሳ እየተደረገ ተሰቅሎ ይቀመጣል። ሙሽራ ስትዳር አንድ ሆነው የሚተኙበት ከቤተሰቧ ቤት ተይዞ ይኬዳል በዛ ላይ ይተኛሉ ፍቅራቸውም የዘለቀይሆናል። እንደ አሁኑ የተግለበለበ አይሆንም። በሱ ተጀቡነሽ[12] መልሆ ስትሞቂም እላይሽላይ ተጣብቆ ሳያንገበግብሽ ላብ ዝፍቅ እያደረገ ከሴው አብሮሽ ይወረዛል ያንችም ጅስም እንደ ከሴው ልስልስ ይላል።*

ይህ የሚያሳየን ከሴ ለወይባ እጥነት ከሌሎች መጀቦኛዎች የበለጠ ጭስን እና የታጣኘን ሰውነት በማዋሃድ ማህበረሰቡ የሚሻውን የወይባ ጭስ እጥነት የሚከውንበት ወሳኝ ቁስ መሆኑን ነው።

## 5.3. የወይባ ጭስ አዘገጃጀት

ወይባ ጭስ መታጠን በኬሚሴ በትኩረት የሚከወን ልማድ ነው። ይህ ልማድ መቸና በማን እንደተጀመረ የሚታወቅ መረጃ ባይገኝም የተግባሩ መነሻ ከጥንት ጀምሮ ሴቶች ማታ ግብር ውሃ ወጥተው ሲመለሱ ወደመኝታ ከመሄዳቸው በፊት በትንሽ ማጨሻ ላይ ጥሩ ሽታ ያላቸው እጽዋቶችን ይሞቁ እንደነበር ይነገራል። ይህ ልማድ እያደገ መጥቶ ጾታዊ ግንኙነት የጀመሩ ሴቶች በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚከውኑት ልማድ እንደሆነ መረጃ አቀባዩች ይናገራሉ። የወይባ እንጨት ጭስን ለመከወን የወይባ እንጨትን ለእጥነት ተግባር እንዲውል አድርጎ ማዘጋጀትን ይጠይቃል። የወይባ ጭስ አዘገጃጀትን አስመልክቶ ወ/ሮ ፋጡማ ይማም፣ቃለ መጠይቅ ፣መጋቢት4/2010 ዓ.ም ሲገልጹ ፤

*ወይባ ለመሞቅ መጀመሪያ ወይባሽን ማሳ ካለሽ ከማሳሽ ማሳ ከሌለሽ ከገበያ ቆንጆውን ትል[13] ያሎጋውን ገዝተሽ ትመጫለሽ ከዚያ በቦለቂያሽ[14] ልክ ይከረከርና ይፈለጣል። ከዚያ ቦለቅያሽላይ እሳትሽን አድርገሽ ተዘጋጅተሽ መግባት ነው። የሚተርፈው ወይባ እርጥበቱን እንደያዘ እንዲሰነብት በኬሻ ጥቅልል ተደርጎ ይቀመጣል ያልተፈለጠ ከሆነ ደግሞ መሬት ቆፈርቆፈር ተደርጎ አፈር ለበስ ተደርጎ ይቀመጥና ሲፈለግ ወጥቶ ይፈለጣል።*

---

[12] ‹‹መጀቦን ›› ማለት አንድን ነገር ዙሪያውን መሸፈን ሲሆን ወይባ የምትሞቅ ሴት ጭሱ ላይ ስትቀመጥ ጭሱ ወደውጭ እንዳይወጣ ና ሙሉበሙሉ ሰውነቷ ውስጥ እንዲቀር በከሴ ሙሉ ሰውነቷን ትጠቀለላለች።

[13]‹‹ ትል›› ማለት ጥቃቅን ነፍሳት ስትሆን ለወይባ እጥነት የሚውል ወይባ ትል ያልወጋው መሆን አለበት ።

[14] ‹‹ቦለቅያ››ማለት የወይባ ጭስ መሞቂያ ጉድጓድ ሲሆን ቦለቅያሽን ማለት የጭስ መሞቂያ ጉድጓድሽን ማለት ነው።

በማለት ለእጥነት የሚያስፈልገው የወይባ እንጨት የተመረጠ፣ ተለክቶ የሚቆረጥና የሚፈለጥ ሲሆን ለእጥነት የሚሆነው ወይባ ኬሮ የሌሌው (ትል ያልወጋው ወይም ሙጫ ያልወጣበት) መሆን አለበት፡፡ እንደዚህ አይነት ወይባ ለእጥነት ከዋለ የሴትየዋን ገላ የማሳከክ ፣ማንደብደብና እሳት ስትገባ የመለብለብ ስሜት የሚያመጣ በመሆኑ በጥንቃቄ ተፈትሾና ታይቶ መዘጋጀት አለበት ፡፡ ወ/ሮ አስማ ሙሃመድ ቃለ መጠይቅ፣የካቲት 23/2010 ዓ.ም ደግሞ የወይባ ጭስ አዘገጃጀትን እንዲህ ይገልጹታል፡፡

> *መልሆ ኬሮ የሌለውን ቢሻው ገዝተሽ ቢሻው ቆርጠሽ ታመጫለሽ ኬሮ ያለው አይሆንም ያሳክካል ፣ሰውነትሽ ግልብጥብጥ ይላል፡፡ እንደሰው ገላ የለሰለሰው እርጥቡ መልሆ ነው የሚሆነው፡፡ ከዚያ ቦለቅያሽ ልክ አስከርክመሽ ቦለቅያሽ ውስጥ መጀመሪያ ትንሽ አመድ ይደረጋል አፈር አፈር እንዳይሸት ከዚያ ፍምሽን አድርገሽ ማጨስ ነው፡፡ታዲያ መልሆው ደረቅ መሆን የለበትም እየተግለበለበ ይለበልባል እርጥቡ የሆነ እንደሁ ቀስብሎ እየጨሰ የልብሽ እስኪደርስ ትሞቂዋለሽ፡፡*



*ከወ/ሮ አስማ ሙሃመድ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ( ፎቶ በአጥኝዋ)*

በማለት የወይባ ጭስን አዘገጃጀት እስከ ወይባው አይነትና ባህሪ ድረስ ያስረዳሉ፡፡ ለጭስነት የሚውለው እንጨት የሚገኘው በሁለት መንገድ ሲሆን አንደኛው በማሳቸው ላይ በመትከል የሚጠቀሙና ለገበያም የሚያወጡ ሲኖሩ በማሳቸው የሌላቸው ደግሞ በወይባ ገበያ ከደመቀው የኬሚሴ ገበያ በመግዛት ይጠቀማሉ፡፡ በምልከታዬ እንዳየሁት እንጨቱ በገበያ ላይ የተፈለጠ ያልተፈለጠ ቀጭን ወፍራም ግንድ በማለት በምድብ ከሃያ ብር ጀምሮ እስከ መቶ ብር ድረስ

ዋጋ ወጥቶላቸው ይሸጣሉ፡፡ በኬሚሴ ገበያ እንደ ደሴና ኮምቦልቻ ያሉ አጎራባች ከተሞች ወይባ እንጨት ለንግድ ጅምላ የሚገዙበት የገበያ ቦታ በመሆኑ ሰፊና የደመቀ የወይባ ተራ ያለው ነው፡፡





ፎቶ 2 የወይባ እንጨት ገበያ በኬሚሴ (ፎቶ በአጥኝዋ)

## 5.4. የወይባ ጭስ እጥነት የሚከወንባቸው አጋጣሚዎች

ወይባ ጭስ መሞቅ የራሱ ባህላዊ ስርአቶች አሉት፡፡ ተጠቃሚዎቹ የወይባ ጭስን የሚሞቁበት ማህበራዊና ባህላዊ አጋጣሚዎችን ሰበብ ያደረገ ነው፡፡ በኬሚሴ ከተማ በማንኛውም እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ያገቡ ሴቶች ወይባ ጭስን በሶስት አጋጣሚዎች ይሞቁታል፡፡ መታጠኑ የሚጀመርበት አጋጣሚ ጫጉላ ቤት ሲሆን ቀሪዎቹ የአራስ ቤት እና ለአዘቦት የመከወኛ አጋጣሚዎች ናቸው፡፡ እነዚህን አጋጣሚዎች ከዚህ እንደሚከተለው ይተነተናሉ፡፡

### 5.4.1. የወይባ ጭስ እጥነት በጫጉላ ቤት

ጫጉላ ቤት ሙሽሮች ከሰርጋቸው ማግስት ጀምሮ እስከ አስራ አምስት ቀን እና ወር ድረስ በተዘጋጀላቸው የማረፊያ ቦታ ከሚዜዎቻቸው ጋር የሚያደርጉት የእረፍት፣ የመዝናናትና ሙሽሪትን የማላማመጃ ወቅት ነው፡



ፎቶ 9 ቃጬር ቀበሌ ከሙሽሪት አንሻ ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ (ፎቶ በአጥኝዋ)

በዚህ ወቅት ከሚከወኑ ተግባራት አንዱ ሙሽሪት የወይባ ጭስ ለመጀመሪያ ጊዜ መሞቅ እንድትጀምር ማድረግ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ባህልና ወግ መሰረት ልጃገረድ ወይባ እንዳትሞቅ በሁለት ምክንያቶች ክልከላ አለባት፡፡ አንደኛ ወይባ ሰውነት ስለሚያጠብቅ ልጃገረድ ወይባ ከሞቀች ሰውነቷ ይጠብቃል፣ብልቷ ይጠነክራል፣ከወንድ ጋር ግንኙነት ለማድረግ ያስቸግራል፣ የወንድ ብልት ወደ ውስጥ መግባት አይችልም ተብሎ እንደሚታመን መረጃ አቀባዩቸ ገልጸውልኛል ፡፡ ሁለተኛው የክልከላ ምክንያት የወይባ ጭስ ሽታ በጣም የሚስብና ለረጅም ጊዜ ከሰውነት ላይ የማይጠፋ፣ የሞቀችው ሴት ባለችበት አካባቢ ሁሉ ሽታው የሚማርክ በመሆኑ ወንዶችን በማማለል ያለዕድሜ ለሚደረግ ጾታዊ ግንነኙነት ይዳርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ሴት ልጅ አግብታ ያታዊ ግንኙነት ጀምራ ህን እስከሚገሰስ ወይባ ጭስ መሞቅ አትጀምርም፡፡

ሰርግ ተሰርጎ ካገባች በሶስተኛው ቀን ሶስቶሽ ይባላል፡፡ በዚያም የሙሽሪት ሚዜና ጓደኞች ወደ ወንድ ቤት ይዘውት ከሚሄዱት የተለያዩ መጠየቂያዎች አንዱ ወይባ እንጨት ነው፡፡ ከዚያም ከቤተሰቦቿ የመጣው ወይባ እንጨትና በሙሽራው ሚዜዎች የተገዛው ወይባ እንጨት ተዘጋጅቶ ከሶስተኛ ቀኗ ጀምሮ ጭስ ትገባለች፡፡ይህን አስመልክቶ ወ/ሮ ሃዋ ሙሃመድ፣ቃለመጠይቅ ፣የካቲት 29/2010ዓ.ም

*በኢያት ቅድመ ኢያታችን በወረስነው ደንብ ቆንጆ[15] ወይባ አትሞቅም አግብታ ህን ሲወጣ ነው፡፡ አሁን አንዳንድ ጊዜ ባልየው አቅም ያንሰውና ህንን መውሰድ አይችልም በዚያ ሰአት*

15 ‹‹ቆንጆ››በማህበረሰቡ አባባል ቆንጆ ማለት ያላገባች ልጃገረድ ማለት ነው፡፡

*ጫጉላ ቤት ናት ተብሎ ወይባ አይጀመርም፡፡ ይጠበቃል፡፡ የጫጉላ ቀኑ ይራዘማል ፣ ሀን ከወጣበት ቀን ጀምሮ አንድ ተብሎ ይቆጠራል፡፡ ቶሎ ሳታገባ ትልቅ ብትሆንም ወይባ አትሞቅም እንዴት ቆንጆ ወይባ ይሞቃል ተብላ ትነወራለች፡፡*

በጫጉላ ቤት ወይባ ለመጀመር ጾታዊ ግንኙነት መጀመር ዋናው ቀዳሚ ጉዳይ ሲሆን የሙሽራዋን ወይባ በመፍለጥ ቦለቅያ ቆፍሮ ማዘጋጀትና የማሞቅ ድርሻ የሙሽራው አንደኛ ሚዜ በማህበረሰቡ አጠራር ‹‹የባሪያው›› ነው፡፡ በዚህ ወቅት ጭሱ ለሙሽራዋ እንግዳ በመሆኑ እሳቱን መዳፈር ትቸገራለች፡፡ ባሪያው ይህን አይቶና ከጭሱ ላይ እንዲያነሳት መማጸኗ አሳዝኖት በአግባቡ ሳያሞቃት ብትቀር ሙሽራው ባሪያውን ይከሰዋል፡፡ ባለቤቴን በአግባቡ አላሞቀልኝም ምክንያቱም ጠረኗ አልተቀየረም፣ ሰውነቷ አልጠነከረም በማለት በግንኙነት ጊዜ የምታሰማውን የስቃይ ስሜት በማስታወስ አቤቱታውን በጫጉላ ቤት በተሸሙ ጊዚያዊ ዳኞች ያቀርባል፡፡

በዚህም ባሪያው ቅጣት ይደርስበታል፡፡ ይህን ችግር ላለመቀበልና ሙሽራዋ አለምንም ችግር ፆታዊ ግንኙነትን ተላምዳ፣ ሰውነቷ ጠንክሮና ንጽህናዋ ተጠብቆ ጤነኛ ሆና እንድትታይ በማድረግ በሙሽራውም ሆነ በቤተሰቡ ባሪያ ማለት ይኸነው ተብሎ ለመወደስ በትኩረት ወይባ ፈልጦና አዘጋጅቶ በየቀኑ ሙሽሪትን ያሞቃል፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ ሁሴን ኢብራሂም፣ ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት 3/ 2010 ዓ.ም እንደሚከተለው ገልጸውልኛል፡-

> *ጫጉላ ቤት አግቢው ሹም ነው፡፡ ባሪያ የምንለው አንደኛ ሚዜው እየፈለጠ የሚያሞቅና የሚንከባከብ፣ ጭስ ስትገባና ስትወጣ የምትመገባቸውን እንደ ገንፎና ጨጨብሳ ያሉ የተለዩ ምግቦችን እያሰራ ተከታትሎ መመገብ የእሱ ስራ ነው፡፡ ጭስ ስትገባ አዲስ ስለሆነች ለበለበኝ ብላ ብትነሳ በጉማሬ እያለ ያሞቃታል አዝኖ ቢያወጣት እሱ ይገረፋል፡፡ ከዚያ ፍልቅልቅ ብላ ቁልፎ[16] ጨርሰው አጥበው ሲወጡ እንደብርቅ ትታያለች ጢስ ጠግባለች የምትባለው እንደዚህ ነው፡፡ጅስሟ ካልጠነከረና ከልጁጋ እንደልቧ ካልተኛች ቀድሞ የሚነወረው[17] ባሪያው ነው ፡፡*

---

[16]‹‹ቁልፎ›› ማለት በማህበረሰቡ አዲስ ተጋቢዎች ከሚዜዎቻው ጋር እየበሉ ፣እየጠጡና እየተጫወቱ ለአስራምስትቀን ወይም ለወር በአንድ ቤት ተሰባስበው የሚያሳልፉት ጊዜ ነው፡፡

[17] ‹‹ መነወር ›› ማለት መሰደብ፣ መናቅ ማለት ነው፡፡ ባሪያው በአግባቡ ሙሽራዋን ጭስ ከላሞቀና በሚፈለገው ደረጃ ሆና ካልወጣች በማህበረሰቡ ይሰደባል ፣ትችት ይደርስበታል ፡፡

በማለት በጫጉላ ቤት የወይባ ማሞቅ ስርአት ሙሽሪትን የልጅነት ሰውነቷ ጠንክሮ ወደ ሳዱላነት በመሸጋገር ከጫጉላ በኋላ በአማቶቿ ፊት ጠንክራና አምራ እንድትታይ ባሪያው ትልቅ ሃላፊነት አለበት፡፡ሙሽሪት እሳቱ አዲስ ሆኖባት ብትቸገርም ጭስገብታና ሳትገባ ያደረገችውን ጾታዊ ግንኙነት ልዩነቱን በማየት ከተወሰኑ ቀንት በኋላ ሳትገደድ ወደጭሱ መግባት ትጀምራለች ፡፡ጭሱ በመጀመሪያ ቀን ግንኙነት የቆሰለ አካሏን በማከም ወሲብን ቀስ እያለች እንድትለምድ ያደርጋታል፡፡ ቁስሉንም በማድረቅ ቶሎ እንዲሻላት ያገግዛታል፡፡ ሙሽሪት ማን ጠግቦሽ የካቲት6/2010፤ቃለመጠይቅ ፡፡ ይህን አስመልክቶ የገጠማቸውን እንዲህ ይገልጹታል፡-

> *መጀመሪያ ያቃጥለኛል ብየ ፈራሁ አፌን እፍን አድርጌ ትንሽ ስሞቅ አንቀጠቀጠኝ ባሪውን ለምኜ ተደብቄ ወጣሁ፡፡ ያው ከሱ ጋር አብረን አይደል የምናድረው (ከባሏ ጋር ማለቷ ነው) በመጀመሪያው ዕለት ያመመኝ በዚያ ቀን ማታ አልተሰማኝም ወገቤን ሁሉ ለቀቀኝ በሁለተኛ ቀን ጭሱን ስደግም ህመም የለኝም ከሱ ስተኛም ሳልቸገር ቀረሁ ጥቅሙን ሳየው በፈቃዴ እየገባሁ መሞቅ ጀመርኩ ሁሉንም ለመድኩት፡፡*

በሁለተኛነት በጫጉላ ቤት የሙሽራዋን ሰውነት ቅቤ የመለቅለቅ የማለባበስና የማጠብ ስራ ደግሞ ለሙሽሪት ተንከባካቢ የተመረጠችው አግብታ ያልፈታች ሴት በማህበረሰቡ አጠራር አያንቴ ናት፡፡ አያንቴ የሙሽሪትን ቦለቅያ የመምረግ ስራም የእርሷ ነው ፡፡ ይህ የሚደረገው አያንቴ አግብታ ያልፈታች በአንድ የዘለቀች ሴት በመሆኗ የሙሽሪትን ቦለቅያ ከመረገች ፍቅራቸው እስከ መጨረሻ ይዘልቃል፡፡ የእርሷ እጣ ይገጥማታል ተብሎ ይታመናል ፡፡ በመሆኑም ሙሽሪትን በጫጉላ ቤት በቅርበት በመከታተልና በመንከባከብ ከባሪያውጋር በመወያየት ከወይባ ጭስ በማሞቅ ጤንነቷን ከመጠበቅና የተመረጡ ምግቦችን አዘጋጅቶ እስከ መመገብ ያሉትን የጫጉላ ቤት ስርአቶችን የመከወን ድርሻቸውን ይወጣሉ፡፡ በዚህም ከጫጉላ ቤት በወይባ ጭስ አካልን አጠንክሮ፣ ከትዳር አጋሯ ጋር አላምዶ በማውጣት ሙሻራ ማለት ይችናት ማስባል የማህበረሰቡ ባህል ሆኖ ይታያል፡፡

### 5.4.2. የወይባ ጭስ እጥነት በአራስ ቤት

አንድ ሴት ከወለደችበት ቀን ጀምሮ እስከ አርባ ወይም ሰማንያ ቀን ድረስ ያሉት ጊዜያቶች አራስ ቤት ይባላሉ፡፡ በዚህ ጥናት ማህበረሰብ አራስ ቤት የወይባ ጭስ እጥነት የሚከወንበት አንዱ አጋጣሚ ነው፡፡ በወሊድ ምክንያት የተከፈተውን ሰውነቷን ለማጥበቅ፣ማህጸኗ እንዲሰበሰብ ለማድረግ፣ ፈውስን ይሰጣሉ ተብሎ የሚታመንባቸው ከወይባ ተጨማሪ እንደ ወይራ ፣ ምስርች ፣አጋም ስር ፣የአባሎ ስር ተጨምረው ይሞቃሉ፡፡ ከወይባ ውጭ ያሉት ስራስሮች በመጀመሪያዎቹ ሳምንታት ከወይባ ጋር እየተጨመሩ የሚሞቁ ናቸው፡፡ ከአስራ አምስት ቀን በኂላ ከወይባ ውጭ ያሉት ፈውስ ቢኖራቸውም ሰውነትን ያጠቁራሉ ስለሚባል እንዲቋረጡ ይደረጋል፡፡ ከዚያም ወይባ ብቻውን እስከ አርባ ቀን ድረስ ይሞቃል፡፡ (ወ/ሮ አክየ አህመድ፣ ቃለ መጠይቅ ፣የካቲት 29/2010 ዓ.ም) እንደሚሉት

> *ለአራስ ጭስ ማቀጠያዋ[18] ነው፡፡ እኔ ወልጀ ከተኛሁ ከሳምንቴ ጀምሮ እየሞኩ ነው ጭስ ገብቶና ሳልገባ የምተኛው እንቅልፍ አንድ አይደለም፡፡ ጭስ ሰገባ ሰውነቴ ይዘናል ፣ ያልበኛል ምግብ ይከፍትልኛል ገንፎየን ብልት አድርጌ ትኝት ስል የወደኩበትን አላውቀም ፡፡ በሆነ ችግር ሳልሞቅ ከቀረሁ ተኝቸም ምቾት የለኝ ፡፡ እንኳን ለኔ ለህጻኑ ወገቡ እንዲጠነክር ጭሷ ብን… ስትል ትንሽ ወገቡን አስመታዋለሁ ጭስ ዋና ነገር ነው ፡፡*



ፎቶ10 ከ ወ/ሮ ሀዋ አህመድ ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ በአራስ ቤት (ፎቶ በአጥኝዋ)

---

[18] ‹‹ ማቀጠያዋ›› ማለት በእርግዝናና በወሊድ ጊዜ የተጎዳ አከሏን መመለሻ ነው፡፡

በአራስ ቤት ወይባ በትኩረት በቀን ሁለት ጊዜ ጠዋትና ማታ ይሞቃል፡፡ጭስ ያልጠገበ የአራስ ወገብ ችሎም አይነሳ ሰውነቷ እንደተከፋፈተ ይቀራልተብሎ ስለሚታመንለመታረሻ የተዘጋጁ እንደ ገንፎ፣ ሾርባ፣ ጨጨብሳ፣ አጥሚት ናፍትፍት፣ ሳቱ[19] የመሳሰሉ ባህላዊ ምግቦችን በትኩስነታቸው እንድትመገብ እየተደረገ ጭስ እየሞቀች እንድትታረስ ይደረጋል፡፡ በአራስ ቤት የሚሞቅ ወይባ የአራሷን ሰውነት ከማጠንከር በተጨማሪ በእርግዝናና በወሊድ ሰአት ያሳለፈችውን የሴትነት ጣጣዋን ከማህጸኗ ጠራርጎ በማስወገድ አዲስ ሴትነት ለመጀመር የምትሽጋገርበት ወቅት ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ አብዱ ሙሄ፣ቃለ መጠይቅ የካቲት 24/2010ዓ.ም፡፡ እንዲህ ይገልጹታል

> *ወይባ ለአራስ እራሱን የቻለ አንድ ምግብ ነው ታላት ጥሩ በልታ ተሌላት ያላትን እየጎረሰች ጭሷ ከገባች ነገ ያላት ኑሮ ያማረ ይሆናል፡፡ ታለዛ ነገ እንኳን ለባሏ ልትሆን ለራሷም ሰው አትሆን ፡፡ ሴት ባራስነቷ ጭስ ካልመታት ወንድ ከጭኗ ገብቶ ሲነሳ አ....አ.. ወገቤ ትላለች፡፡ ይኸን ስለሚያውቅ ባሏም ከስር ከስር እየፈለጠ ማቅረብ የሱ ስራ ነው፡፡*



ፎቶ11 ወ/ሮ መዲና ሙሃመድ የአራስ ቤት ወይባ በመሞቅ ላይ ፎቶ (በአጥኝዋ)

[19]‹‹ ሳቱ›› ከማሽላ የሚዘጋጅ ንፍሮ ሲሆን ንፍሮው በጣም ሳይበስል ለጥርስ ትንሽ ያዝያዝ ሲያደርግ ወጥቶ በማር እየታሸ ከጭስ እንደወረደች ትበላላች፡፡ ይህ ሰውለቷን ለመጠገኝና ጡቷም ወተት እንዲያግት ይረዳል ተብሎ ይታመናል፡፡

ይህ የሚያሳየን በአራስ ቤት ላይ የሚከወን የወይባ እጥነት ሴቷ ያለፈቻቸው እርግዝናና ወሊድ የመሳሰሉ የሴትነት ጣጣዎች እምትሸኝበት በመሆኑ ከምግቡ ጀምሮ እስከ መሞቂያ ጊዜው ድረስ በአጽንኦት ሚከወን ነው ። በመሆኑም የአራሷ ባለቤት ጭምር  አስፈላጊ ቁሶችን በማቅረብና ሰአቱን ጠብቃ ጭስ እንድትገባ በማበረታታት ይታትራል ። በመሆኑም አራሷ ከምትሻቸው  አካላዊ ለውጦች በዘላላ ከትዳር አጋሯጋር የነገ አብሮነትን ያማረ ለማድረግ በዚህ አጋጣሚ የሚከወነው የወይባ ጭስ እጥነት  ሚናው ከፍያለ ነው፡፡

## 5.4.3. የወይባ ጭስ እጥነት በአዘቦት

አንድን ነገር ለመከወን አጋጣሚ ወይም ሰበብ ሳይጠይቅ የሚፈጸም የእለት ተዕለት እንቅስቃሴ በዚህ ጥናት ማህበረሰቡ አጠራር አዘቦት ይባላል፡፡ ፆታዊ ግንኙነት የጀመረች ሴት ቦለቅያ ከማጀት እቃዎቿ መካከል አንዱ ነው፤ በመሆኑም፣ ወይባ መሞቅ የዕለት ተግባሯ ነው፡፡ አብዛኞቹ ያገቡ ሴቶች በቀን ሁለት ጊዜ ቦለቅያ ይገባሉ፤ አንዱ ጠዋት ጠዋት ቁርስ በልተው ቦለቅያቸው ላይ መቀመጥ ቀዳሚ የእለት ተግባራቸው ሲሆን ሁለተኛው ማታ ወደ መኝታቸው ከመሄዳቸው በፊት እራት በልተው የወይ ባጭስ ይሞቃሉ፡፡ ቀድሞ እንደተገለጸው ማህበረሰቡ ለወይባ ጭስ ያለው አመለካት ጥልቅ እንደመሆኑ ወይባ ለሚሞቁና ለማይሞቁ ሴቶች ያለው አመለካከት በእጅጉ የተለያየ ነው፡፡ ቦለቅያ የምትገባ ሴት በአወንታ የምትነሳ ሲሆን ቦለቅያ የማትገባ ሴት ደግሞ በአሉታ ትነሳለች፡፡ በመሆኑም ጾታዊ ግንኙነት የጀመሩ ሴቶች ያልተመቻቸ ሁኔታ ገጥሟቸው የጠዋቱ ቢያልፍ ማታ ቦለቅያ መግባት የእለት ስራ ማጠናቀቂያ ተግባራቸው ነው፡፡



ወ/ሮ12 ፋጡማ ይማም የአዘቦት ወይባ ጭስ በመሞቅ ላይ(ፎቶ በአጥኝዋ)

ይህንአስመልክቶ (ወ/ሮ ፋጡ ማይማም፣ቃለመጠይቅ፣መጋቢት4/2010ዓ.ም) እንደሚከተለው ይገልጹታል ፡፡

> *በእኛ ባህል ሴት ጎጆ ከያዘች ቢሞላላት በቀን ሶስት ሁለት ጊዜ ካልሞላላት ግን ማታማታ በለቅያ ሳትገባ አታድርም እኔ ጠዋት እንዳየሽኝ በቀን ሁለት ጊዜ ነው የምሞቀው ጠዋት ሞቅ ብየ ትጥብጥብ እልና ፈርሃኝ[20] ሆኘ እውላለሁ፡፡ ማታ ደግሞ ግብት ብዬ ሞቅ አድርጌ ተጣጥቤ ወደመኝታዬ እሄዳለሁ፡፡ ሰውነቴ እንግዲህ እንደምታይው ነው፡፡ ወይባ የሚሞቅ ሰው ምን እድሜው ቢገፋ ቆዳው አይሸበሸብም ፣በሽታ አይደፍረውም ፣ አያስረጅም እከሌ እኮ አታረጅም ወይባ ትሞቃለች ነው የሚባለው፡፡ አባዋራዋም ወይባ ለመግዛትና ለመፍለጥ አይቦዝንም በማህበረሰቡም እሷ ተከብራ ባሏን ታስከብራለች፡፡*

በዚህ ጥናት ማህበረሰብ በአዘቦት ጭስ ለምትገባ ሴት ከፍተኛ ፍቅር አለው፡፡ ጭስ የምትገባ ሴት ከእርሷ አልፋ ባለቤቷን ታስመሰግናለች ፡፡ ሚስት ማለት እንደ እከሌ ነው ሂናዋ ከእጇ ጭሷ ከእግሯ አይጠራም ፣ሴቷን እሱ ይዟታል ንጹኅ፣ ሽቅርቅር እኮ ናት ካለ ወይባ አትወጣም እየተባለ እንደምትወደስ መረጃ አቀባዩቸ ይናገራሉ፡፡ ወ/ሮ ፎዚያ ኡመር በአዘቦት

[20]ፈርሃን የአረብኛ ቃል ሲሆን ደስተኛ ማለት ነው፡፡ ወይባ የሞቀች ሴት ደስተኛ ሆና እየሳቀችና እየተጫወተች ዘንታ እንደምትውል ያሳዩበታል ፡፡

‹‹ወይባ የምትገባ ሴት እንዝርት[21] ናት፡፡ ከጠረኗ አልፈሽ በአረማመዷ ታውቂያታለሽ፡፡ ጭሷ ስትገባ ሰፈሯ ይታወዳል››፡፡ ሴት ልጅ ትዳር ከያዘች በመታጠን ጤንነቷንና ንጽህናዋን ጠብቃ መገኘት ግዴታ ነው፡፡ የእከሌ ሚስት ጭስ አትገባም፣ መባል ትልቅ ውርደት ነው፡፡ ከትዳር ያፈናቅላል፡፡ በመሆኑም አዘውትራ ጭስ ለምትገባ ሴት የሚሰጠው ደረጃው ከፍተኛ ነው፡፡ ሴት በቦለቅያ አሰራሯ፣ ጭስ ገብታ ንጽህናዋን በመጠበቋ፣ የሚሰጣት ማህበራዊ ደረጃ አለ ‹‹ባለሙያ›› እየተባለች ትወደሳለች፡፡ሴቷም ከሚሰጣት ትኩረት የተነሳ በራስ የመተማመን ስሜቷ ከፍተኛ ነው፡፡ እራሷን ለመጠበቅና አዘውትራ ጭስ ለመግባት አትቦዝንም በማህበረሰቡም ሆነ በትዳሯ ተቀባይነቷ የጠነከረ ነው፡፡ (አቶ ሁሴን ኢብራሂም ቡድን ውይይት መጋቢት 9/2010 ዓ.ም )

*ከታጠነች ሴት ጋር የተኛ እራሱ እንደታጠነ ነው፡፡ ካልጣጠነች ሴት ጋር የተኛ ጠዋት ችሎም አይነሳ፡፡ ህመም አያጣውም በእኛ ባህል ይህ ነው፡፡ አባዋራ የሚባለውም ቅቤና ወይባ የሚያሟላ ሲሆን ነው፡፡ ጠብ የሚመጣው ቅቤ አልገዛልኝም ወይባ አልፈለጠልኝም በሚል ነው፡፡ ልጅነት እንኳ ይዞት ችላ ቢል ጎጆ እስኪለዩ እናቱ ተከታትላ ታሟላለች በአማቶቹም ጥሩ ኑሮ ይዛለች የሚባለው በዚህ የሚያንከባክብ ባል ከሆነ ነው፡፡ ያ የሚቀናበት ቤት ይሆናል፡፡*



ፎቶ14 ከእድሜ ባለጸጋ አባቶችና ለጭስ ተጠቃሚ ሴት ባሎች ጋር የተደረገ የቡድን ውይይት (ፎቶ በአጥኝዋ)

[21]<<እንዝርት›› በባህላችን ለጥጥ መፍተያነት የሚያገለግል ከቀርቀሃ የከሚሰራ ቁስ ነው፡፡ በእንዝርት ጥጥሲፈተልእንዝርቱን በማሽከርከርና በማሾር ጥጡ እንዲከር የሚያደርግ ፈጣን እንቅስቃሴ ያለው ቁስ በመሆኑ ወይባ የምትሞቅ ሴትን ከእንዝርት ጋ በማነጻጸር ቅልጥፍናዋን ተገልጾበታለል ፡፡

በአዘቦት በለቅያ የማትገባ ሴት በማህበረሰቡ የሚደርስባት ነቀፌታ ከፍተኛ ነው፡፡ ከንጽህናዋ ጀምሮ እስከ ጤንነቷ ድረስ እራሷን የማትጠብቅ ሰነፍና የማትረባ ሴት ተደርጋ ትወሰዳለች፡፡ አግብታ በቤቷ በለቅያ የሌላት ሴት ሙያ የሌላት ተብላ እንደምትንቋሽሽ መረጃ አቀባዮቸ አጫውተውኛል፡፡ (አቶ ኑራን የቡድን ውይይት መጋቢት 9/2010 ዓ.ም) ‹‹ሴትና የወተት ቅል ጢስ ካልነካው ዋጋ የለውም አይጣፍጥም፡፡ ጣዕሙ ከወተቱ ሳይሆን ከማጥንቱ ነው፡፡ ሴቷንም በዚያ እይው ጭስ ያልገባች ሴት ኦና[22] ቤት ማለት ነው፡፡›› በማለት ይገልጹታል ፡፡ ሴት ልጅ ኑሮዋን ለማቃናት ከምታትርባቸው ተግባራት አንዱ ጭስ መግባት ነው፡፡ ጭስ የማትገባ ሴት ከመናቋም በላይ ትዳሯ የጸና አይሆንም፡፡ ይህን አስመልክቶ ( አቶአብዱ ሰይድ ቡድን ውይይትመጋቢት 9/2010 ዓ.ም)

> ጓደኛ የባለቤቱ ኮብልላ ልንሽመግል ተቀምጠን ችግራችሁን አውጡ ስንል እሱ ይናገር እሷ ትናገር ሆነ ሁለቱም ሲያስቸግሩን ተከፋሁ ያልሽው አንች በመሆንሽ አቅርቢ አልን ‹ ሲበላ እንደ አንበሳ ሲተኛ እንደሬሳ ይኸው ሶስት ሳምንቴ ጭኔ ከተነሳ› በማለት የኮበለለችበትን ምክንያት ወቀሳ አቀረበች እሱም በምላሹ ‹ እንኳን ሶስት ሳምንት ቢሆናት ሰላሳ ምነው በሷ ጭን ጭስ አይጨስም እሳ ኦና ቤት ገብቸ ቢጓሰመኝ እሳ› ብሎ መለሰ››

ይህ አባባል የሚሳየን አመጋገቡ ሆዱ እስኪሞላ ተመችቶት እያለ ከትዳር ጓደኛው ጋር ለፍቅር ጨዋታ የቦዘነው ጭስ የማትገባ ሴት እንደ ባዶ ቤት የምትቆጠር መሆኑንና ወንዶች ለፍቅር መኘታ እንደማይፈልጓት እናይበታለን፡፡ ማህበረሰቡ ለጭስ መታጠን የሚሰጠው ዋጋ የላቀ በመሆኑ ይህን ተግባር የማትከውን ሴት ሰላማዊ ትዳር የሌላት መሆኑን ያሳየናል፡፡ ጭስ አለመታጠን ትዳርን የሚያፈርስ መሆኑን መረጃ አቀባዩ የገጠማቸውን እንዲህ አጫውተውኛል፡፡

‹‹አንድ አባወራ ሚስቱን ቢላት ቢላት ጭስ አልገባ ስላለችው እሷን ፈትቶ ዘወትር ከቦለቅያ የማትወጣና እንሶስላዋ ያማረ ሴት አገባ፡፡ ይህን ሳታይ ቆጭቷት ወይባዋን ሞቃ በመልካም መዓዛ በአጠገቡ በመሄድ ስታሳየው ‹እኤስ አቅሻለሁ ለማያውቅሽ ታጠኝ አላት› ይባላል››፡፡ (እንደላይኛው )፡፡ ጭስ የማትገባ ሴት ንጽህናዋን የማትጠብቅ፤ የባለቤቷን ፍላጎት የማታሟላ፣ ጥንካሬና ወዝ የማይታይባት ሙያ የሌላት ናት ተብሎ ስለሚታመን ጭስ

[22]‹‹ኦና›› ማት ምንም ነገር የሌለው፣ ሰው የማይኖርበትባዶ ቤት ማለት ነው ፡፡ በኬሚሴ ማህበረሰብ ባህል ጭስ የማትገባ ሴት እንደ ኦና ቤት ትቆጠራለች ፡፡

እንደምትገባ ሴት እኩል ክብር አይሰጣትም ። በመሆኑም በአዘቦት ወይባ የምትሞቅ ሴት በማህበረሰቡ የተለየ የክብር ቦታ ትሳጣለች የሴቶች ምሳሌ ተደርጋ በየቦታው ትነሳለች ተለይታ ትታወቃለች። አይን እንኳን ባያይ ጠረኗ ይቀድማል ። እሷ አልፋ ሄዳም ጠረኗ ይቀራል፡፡ ከፊቷ ላይ ፍልቅ የሚል ወዝ ያላት ጤነኛና ውብ እንደምትሆን መረጃ አቀባዮች አጫውተውኛል ። ወይባ ጭስ በአዘቦት ሴቶች ጾታዊ ግንኙነት ከጀመሩ ጀምሮ እድሜ ሳይገድባቸው በህይወት እስካሉ ይሞቁታል ። (ወ/ሮ አስማ ሙሃመድ፣ ቡድን ውይይት መጋቢት 9/2010ዓ.ም) ‹‹ መልሆ አዘቦት ተከታትላ የሞቀች ሴት እድሜዋ ስድሳ ሰማኒያ ቢሆን ቆዳዋ አይታጠፍም ። በሽታ አይደፍራትም ፣ሙሽ እንዲህ እንደ ዛሬው በጭብጥ መሰለሽ እኛ ስንሞቅ እኮ በቀርቀቦ[23] ሙሉ ነው የምናቀርበው እየሞቅን እንቅልፍ እንተኛ ነበር ለዛሬ ስንቅ የሆነን ያ ነው ።›› ሴት ልጅ ትዳር ይዛ ጎጆ ከመሰረተች የእለት ስራ ማሳረጊያዋ የሚሆነው ወይባ ጭስ በመግባት እራሷን ጤንነት መጠበቅና የትዳር አጋሯን ጾታዊ ፍላጎት ለማሟላት ዋናው ተግባር ጭስ መግባት እንደሆነ ያሳየናል፡፡



ፎቶ 13 የቡድን ውይይት በጭስ ተጠቃሚ ሴቶችፎቶ (በአጥኝዋ)

በዚህ ጥናት ማህበረሰብ አብዛኛው አግብተው የሚኖሩ ሴቶች የአዘቦት የወይባ ጭስ እጥነት ተጠቃሚ ናቸው፡፡ በመሆኑም የኑሮ ደረጃ ሳይወስናቸው ያላቸውን በልተውና ጠጥተው

[23] ‹‹ቀርቀቦ›› በአካባቢው አጠራር ለመስፈሪያነት የሚያገለግል ከስንደዶ ወይም ከአክርማ የሚሰፋ ሲሆን ቁና በመባልም ይታወቃል፡፡

የወይባ እንጨትን እንደ ወርሃዊ የቤት ወጭ በመቁጠርና በማሟላት በየጊዜው ጭስ ይሞቃሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ወይባ እንጨት መግዛትና መፍለጥ የአበዋራው[24] የስራ ድርሻ ነው፡፡

## 5.5. የወይባ ጭስ አሟሟቅ ስርአት

የወይባ ጭስ በሚሞቅበት ጊዜ የሚከወኑ የተለያዩ ስርአቶች አሉት፡፡ እነዚህም ከአመጋገብ እስከ አለባበስ ድረስ ለጭሱ ተብለው የተዘጋጁ ምግብና መጠጦችን በመጠቀም እና ለእጥነቱ ምቹ የሆነ አለባበስን በመከተል ይከወናል፡፡ በመሆኑም፣ የወይባ ጭስ ተጠቃሚ ሴት ወደ ጭስ መሞቅ ስትገባ እሳቱ ልቧን እንዳያደክመው እና በሚወጣት ላብ መተኪያ የሚሆን ትኩስ ምግብ መብላትና  ትኩስ ነገሮችን መጠጣት ይጠበቅባታል፡፡ ምክንያቱም የምግቡ ትኩስነት ከምትሞቀው ጭስ ጋር ሲገናኝ በሰውነቷ ውስጥ የሚፈጠረው ሙቀት ከውጭ ከሚመታት የጭስ ሙቀት ጋር ይስማማል፡፡ የወይባ ጭስ የአሟሟቅ ሂደት የተፈለጠ የወይባ እንጨት ከተዘጋጀ  በኋላ  ጭስ የሌለው የእሳት ፍም በቦለቅያው ውስጥ በማስገባት የተፈለጠውን ወይባ እንጨት በመጨመር የምትሞቀው ሴት ከቦለቅያው ላይ ቁጭ ብላ ለጋ  ቅቤ ከራስ ጸጉሯ እስከ እግር ጥፍሯ ድረስ ትለቀለቃለች፡፡ ከዚያም ከሌ ከአንገቷ በታች ትለብሳለች፡፡ ጭሱ እንዳይወጣ ከላዩ ላይ ብርድ ልብስ ትደርብና ዙሪያዋን ተጠቅልላ ሰውነቷን በጭሱ ሙሉ ለሙሉ ታስመታለች፡፡ ከጭሱ ላይ እያለችም አጥሚት ወይም ሾርባ አጠገቧ ያለ አሟቂ እንዲያጠጣት ይደረጋል ፡፡ ጭሱ ፊቷን  እንዲያገኛት ስትፈልግ ከአንገቷ ከፈት በማድረግ ወይንም ጎንበስ እያለች  ፊቷን ወደ ሰውነቷ በማስገባት በጭሱ ትመታለች፡፡



ፎቶ 7 ወሮ/ ፋጡማም ወይባ ጭስ በመሞቅ ፊቷን ስታስመታ ( ፎቶ በአጥኝዋ)

[24] ‹‹ አባወራ›› የቤተሰብ ሃላፊ ወይም አስተዳዳሪ ማለታ ነው፡፡

ታጣሿ ሴት በዚህ ሁኔታ ከጭሱ ላይ አንድ ወይም ሁለት ሰአት ከቆየች በኋላ እንደተጀቦነች ከጭሱ ያገኘችው ሙቀት ሳይበርድ ከቦለቅያው ጎን በተዘጋጀ ጊዜያዊ ማረፊያ ላይ በሞቀችበት ከሌ ተጠቅልላ ትተኛለች፡፡ በዚያም ሙቀቷ የበለጠ እንዲጨምርና እንዲያልባት ያስችላታል፡፡ ይህን አስመልክቶ ወ/ሮ ፋጡማ

> *ይማም ሲገልጹ ጭሱን እስኪበቃሽ ትሞቂያለሽ ሰውነትሽ በላብ ዝፍቅ ይላል ከዚያ እንዳላበሽ ጎፈፍ ብለሽ ወርደሽ ትኝት ትያለሽ እዚያ እንደገና አንድ ብሎ ያልብሻል ፡እንደ እንቅልፍም ይቃጣሻል ከዚያ ተነስተሽ ሰውነትሽን አብርደሽ ውልቅ አድርገሽ ትታጠቢያለሽ ደግመሽ መግባት ተፈለግሽ ትገቢና ሞቀሽ ስታበቂ አትታጠቢውም ሰውነትሽን አብርደሽ ወደ ስራሽ ትሰመሪያለሽ፡፡*

በማለት የገለጹት ሃሳብ የሚያሳየን የወይባ ጭስ እጥነት ወቅት የሚከወኑ ተግባሮች ለአሚሚቅ ሂደቱ ወሳኝ መሆናቸውን ነው፡፡ እነዚህ ሂደቶችም በየመሞቂያ አጋጣሚዎቹ በአብዛኛው ተመሳሳይነት ያለቸው ሲሆኑ፣ ከእጥነት በፊትና ከእጥነት በኋላ የሚወሰዱ ምግብና መጠጦች በማህበረሰቡ ባህልና ወግ መሰረት በጫጉላ ቤት ያለው የወይባ እጥነትና በአራስቤት ያለው የወይባ እጥነት ትኩረት ተሰጥቶት የሚተገበር ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም በአራስ ቤት የሴቷ ሰውነት በእርግዝናና በወሊድ ወቅት የተጎዳ አካለለዋን እንዲጠግናት ታስቦ የሚሰራ ሲሆን በጫጉላ ቤት ያለው እጥነት ደግሞ ሙሽራዋ በፊት ከነበረው አካለዊ ብቃቷ የተሸለ ቁመና ላይ ደርሳ እንድትገኝ የወይባ ጭስን እጥነትን በተመረጡ ባህላዊ ምግቦች ጋር በማገዝ እክብካቤ ይደረግበታል ፡



ፎቶ8 ወ/ሮ ፋጡማ ይማም ወይባ ጭስ በሞቀችበት ከሌ ተጀቡና እንደተኛች (ፎቶ በአጥኝዋ)

ይህን አስመልክቶ (ወ/ሮ ፋጦ እንድሪስ፣ቃለ መጠይቅ የካቲት7/2010ዓ.ም) ሲገልጹ፡-

*የወይባ ጭስ አሟሟቅ በሁሉም ወቅቶች አንድ ነው፡፡ የምናደርገው የምናቀርበው ሁሉም ያው ነው፡፡ እብዛም ልዩነት የለውም ትንሽ ጥንቃቄ የሚደረገው እህሉ ላይ ነው፡፡ ጫጉላ ቤትና አራስ ቤት ተጠንቅቀን ገንፎ ፣ጨጨብሳ ተበልቶ ሾርባ እየተጠጣ፣ ደራራ እየተበላ ነው አዘቦት ከሆነ ቤት ያፈራውን ሽሮም ሆነ ፍርፍርም ሆነ ትኩሱን ብልት አድርገን ጭሳችን እንገባለን ስንወጣም እንደዚሁ የተገኘውን ትኩስ ትኩሱን እንበላለን፡*

ወይባ ጭስን በመሞቅ ሂደት ውስጥ የሚበሉ ባህላዊ ምግቦች ከጭሱ ጋር ሰውነትን በማሞቅ እና በመጠገን ለእጥነቱ ትልቅ ቦታ አላቸው ጭስ የገባች ሴት ገንፎ፣ ጨጨብሳ፣ ሳቱ፣ ወዘተ…የመሳሰሉ ትኩስ ምግቦችንና እንደ ሾርባና አጥሚት ያሉ ፈሳሽ መጠጦችን መውሰድ አላባት፡፡ እነዚህን ምግቦች በማይገኙበት ወቅት ቤት ያፈራውን[25] ትኩስ ነገር በመብላትና በመጠጣት ጭሱን እንድትሞቅ ያደረጋል፡፡

## 5.6. በወይባ ጭስ የመታከም ፋይዳ

### 5.6.1 የወይባ ጭስ ፈውስ

የወይባ ጭስ እንደየ ማህበረሰቡ አስተሰሰብ አድማስ፣ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ መሰረት የሚሰጠው ፋይዳ የተለያየ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ማህበረሰብ ከተለያዩ በሽታዎች በመፈወስና ቀድሞ በመከላከል ዘርፈ ብዙ የጤና ጠቀሜታዎችን መጎናጸፊያ ልማድ ነው፡፡ ሰዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚከሰቱ የጤና መጓደሎች ይገጥሟቸዋል፡፡ እነዚህን የጤና ችግሮች በማሶገድ ወደ ነበሩበት መልካም ጤንነት ለመመለስና ዳግም እንዳይከሰቱ ለመከላከል በባህላዊ መንገድ የሚወሰዱ እርምጃዎች ውስጥ አንዱ በጭስ እጥነት እራስን ማከም ነው፡፡ በመሆኑም በኬሚሴ ማህበረሰብ ሴቶች ጤናቸውን ለመጠበቅ ከሚጠቀሙበት ባህላዊ ነገሮች መካከል የጭስ እጥነት አንዱ ነው፡፡ ይህ ልማድ በአካላዊ ጥንካሬና በአዕምሮ መዝናኛነት ትልቅ ጥቅም ይሰጣል ፡፡ በዚህ ጥናት ማህበረሰብም የወይባ ጭስ እጥነት ከተለያዩ በሽታዎች ፈውስ ከመሆን አንጻር ያለውን ፋይዳ ከዚህ በመቀጠል አንድ በአንድ ተዳሰዋል ፡፡

---

[25] ‹‹ቤት ያፈራው›› ማለት በቤት ውጥ ተዘጋጅቶ የሚገኘውን ፣ ያለውን ማንኛውንም ምግብ ማለት ነው፡፡

#### 5.6.1.1. ለአካላዊ ፈውስ

ወይባ ጭስ አካላዊ ጥንካሬን በማምጣት ከተለያዩ በሽታዎች የመፈወሻ መንገድ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ወይባ ጭስ በኬሚሴ ማህበረሰብ ዘንድ ለተለያዩ አካላዊ ጠቀሜታዎች ይውላል፡፡ እነርሱም፡- የአካል ጥንካሬና ብርታት መስጠት ፣ ከሰውነት የሚወጡት አላስፈላጊ ፈሳሾችን ማድረቅ ፣ለቆዳ ልስላሴና ከሰውነት የሚወጡ ጠረኖችን በማስወገድ ጤንነትን የመጠበቅ ፋይዳዎች አሉት፡፡

ወይባ (በሌላ አጠራር ተርሚናሊያ) የአፍሪካ ሃገራት ህዝቦች እንደ ባህላዊ መድሃኒት ይገለገሉበታል፡፡ ለምሳሌ እንጨቱን በመዘፍዘፍ የተዘጋጀ መጠጥ /ሻይ/ ለአጣዳፊ ሳል እንደ ማስታገሻ ያገለግላል፡፡ የቅርፊቱ መረቅም ለወፍ በሽታ /ጉበት/ የወባ በሽታ ፣ የሳንባ ነቀርሳ፣ የሚጥል በሽታ፣ የአባለዘር በሽታ/ቂጥኝና ጨብጥ/ በመደሃኒትነት ይጠቅማል፡፡የግንድና ቅርፊቱ በመቀቀል መረቁ የሰውነት እብጠት ይከለከላል፡፡ ቅጠሉም ለጨጓራ ህመም ፣ ለአንጀት ህመምና ተቅማጥ ለዓይን ቁስለትን ያድናል ፡፡ ስሩም በሰውነት ላይ ለሚከሰቱ ያለመቀበል ስሜት ያዳክማል ማለትም የሰዎች ሰውነት ሁሉንም ነገር እንዲቀበል ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በእንስሳት ላይ ለሚከሰቱ ድንገቴ በሽታዎች ፈውስን ያመጣል፡፡ የወይባ ጭስም በከሚሴ ከተማ ማህበረሰብ ጾታዊ ግንኙነት የጀመሩ ሴቶች በሶስት አጋጣሚዎች ላይ ጭሱን በመታጠን ለዚሁ ተግባር እንደሚያገለግል በእምነት ይዘውት ይታያሉ፡፡በመሆኑም የዚህ ጥናት አካል በሆኑት በኬሚሴ ማህበረሰብ ደግሞ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች የሚያበረክት መሆኑን እንመለከትበታለን

##### 5.6.1.1.1 ሰውነትን ከማጠንከር

የኬሚሴ ማህበረሰብ የወይባ ጭስ ተጠቃሚዎች ለአካል ጥንካሬ እና ለሰውነት ጥብቀት ይጠቀሙበታል፡፡ ጾታዊ ግንኙነት የጀመሩ ሴቶች የወይባ ጭስን ከላይ በተጠቀሱት ሶስት አጋጣሚዎች በመሞቅ ጡንቻቸውን ለማፍታታት ፣ በስራ የደከመ አካላቸውን በማዝናናት ጠንካራና ደስተኛ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም የሴት ልጅ ብልትን በማጥበብ ለወሲብ ምቹ ማድረግና ስራ በሚሰሩበት ጊዜ ድካምን መቀነስ፣ በግብረ ስጋ ግንኙነት ጊዜ የሴቷን የአቅም ድክመት እና ስሜት ማጣትን በማስወገድ አካላዊ ደህንነታቸውን ይጠብቁበታል።

የወይባ ጭስ የሴትን ልጅ ሰውነት በማጥበቅ ጠንካራ እንድትሆንና እድሜዋ ሲገፋም የእርጅና ስሜት እንዳይጫናት በማድረግ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ ወይባ ጭስ ሲገቡ በሰውነት ላይ

የሚለቀለቀው ቅቤ በጭሱ እየቀለጠ ወደ ሰውነት ዘልቆ በመግባት በሙቀት ሃይል በስውነት ላይ ያሉ ቀዳዳዎች እንዲከፈቱ በማድረግ አላስፈላጊ ቆሻሻዎችን በላብ መልክ ያሶግዳል፡፡ ገላን በማውዛትና በማለስለስ የሰውነት ቆዳ ጠንካራና የማይሸበሸብ እንዲሆን ያስችላል፡፡

ይህን አስመልክቶ (አስማ ሙሃመድ ፣ቡድን ውይይት ፣9/2010ዓ.ም) ‹‹ ምን ደሃ ብትሆን ያላትን በልታ ጭስ ከገባች ስጋና መረቅ ከሚጋፍፉት[26] እኩል ትደረጃለች ቀዷና ቀድሯ[27] እስካልደረሰ ድረስ ወይባ የሞቀች ሴት አረጃለሁ ብላ አትሰጋም መንገድ ሄዳም አትደክምም፡፡ ›› ይህ አባባል የሚያሳየን የተመጣጠኑ ምግቦችን ተመግበው ከሚያገኙት አካላዊ ጥንካሬ ባልተናነሰ የወይባ ጭስ መታጠን የአካል ጥንካሬን ለማግኘት የሚውል መሆኑን ያመላክታል ፡፡ ይህ የጭስ እጥነት በተጠቃሚዎቹ ዘንድ አቅም እየደከመ ሲሄድ ጉልበት ይሆናል፡፡ አንዴ ወገቤ አንዴ እግሬ እንደማያስብል ይጠቁማሉ፡፡ ሰውነት ሲደክምና ሲዝል ጭስ መግባት ድካሙን በላብ በማሶጣት የሰውነትን ጡቻ በማፍታታት እና በማዝናናት ጠንካራ አካለዊ ብቃት እንዲኖራቸው ይረዳል ፡፡

### 5.6.1.1.2. አለስፈላጊ ፈሳሾችን በማድረቅ በሽታዎችን ማከም

ወይባ ጭስ በሙቀት ሃይል በሰውነት ቆዳ ላይ ያሉ ቀዳዳዎች እንዲከፈቱ ይረዳል፡፡የጭስ እጥነት በላብ መልክ ከውስጥ ያሉ ቆሻሻዎች እንዲወጡ በማድረግ በሽታን በማስወገድ ፈውስን የሚሹበት ልማድ ነው፡፡ ጭሱ በማህጸን በመግባት አላስፈላጊ የሆኑ ፈሳሾችንና ቆሻሻዎችን በማውጣት ባክቴሪያዎች እንዳይፈጠሩ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ወይባ ጭስ የመታጠን ፋይዳ በኬሚሴ ማህበረሰብ ዘንድ በሴት ብልት አካባቢ የሚኖሩ ፈሳሽ ነገሮችን ለማፅዳት፣ የማህፀን መዳከምን ለመቀነስ፣ የወር አበባ ጊዜውን ጠብቆ እንዲመጣ ለማድረግ፣ በውልደት ጊዜ የሚፈስን ፈሳሽ ለማፅጃነት፣ይውላል ፡፡ ንጽህናን በመጠበቅም የሴቶችን የመራቦ አካላት ከተለያዩየ በሽታዎች ይከላከልል፡፡ ይህ የሴትን ብልት ጤንነት የመጠበቂያ ዘዴ ተላላፊ በሽታዎችን ለማከም የፊንላንዲያውን ሃገራትን ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች ግልጋሎት ላይ እንደዋለ እንዳየነው ሁሉ በኬሚሴም ከሴት ብልት የሚወጡ ፈሳሽ ነገሮችን ከማድረቅና በበሽታ አምጭ ተህዋስያን ምክንያት የሚመጡ ህመሞችን በማከም የማህጸንን ጤንነት መጠበቂያ እጽዋት ነው ብለው ይጠቀሙበታል፡፡

---

[26] ‹‹ከሚጋፍፉት›› በብዛት ከሚመገቡት ማለት

[27] ‹‹ቀዷና ቀድር›› ማለት ከአረብኛ የተወሰደ ቃል ሲሆንክፉ አጋጣሚዎች የሚከሰቱበት ፈጣሪ ያዘዘው ቀን ማለት ነው ፡፡

በወይባ ጭስ ጤንነታቸውን የሚጠብቁ ሴቶች ከወይባ እንጨት በተጨማሪ በፈዋሽነታቸው የሚያምኑባቸውን እንደ ቆለዲ ፣አጋምና ምስርች የመሳሰሉ እፆችን አብረው ይታጠናሉ፡፡ በዚህም የብልት አካባቢ ቁስለቶችን ፣በሰውነት ቆዳላይ የሚወጡ ሽፍታዎችን፣ የመገጣጠሚያ ችግሮችን፣ የደም ዝውውር ችግሮችን፣ የምግብ ፍላጎት ማጣትና የተለያዩ ተላላፊ በሽታዎችን ለማሶገድ የጠቀሙበታል፡፡

በጽንሰ  ሃሳባዊ ዳራ ባየነው መሰረት የእንፋሎት እጥነትን  በአሜሪካ ያሉ ፊላንዳውያንና ጃፓኖች  ጾታ እና እድሜ ሳይገድባቸው የሚከውኑት ባህላቸው ሲሆን በዚህ ጥናት ማበረሰብ ባህል ደግሞ እጥነቱ በእድሜና በጾታ የተገደበ ነው፡፡ በመሆኑም ወንድ ልጅ ወይባ ጭስ አይታጠንም፡፡ ምክንያቱም የጭስ እጥነት ከፍተኛ ሙቀትና ላብ የሚፈጠርበት በመሆኑ ወንድከታጠነ የዘርፍሬው ደካማ ይሆናል ፣ፈጥኖ ለወሲብ መነሳሳት ያዳግተዋል( ለስንፈተ ወሲብ ) ይዳረጋል  ተብሎ ይታመናል ፡፡ በመሆኑም ወንዶች ይህን የፈውስ ምንጭ ቱርፋት የሚያገኙት ሴቶች በተለያዩ አጋጣሚዎች በመታጠን የእነሱንም ሆነ የቤተሰባቸውን ጤና ለመጠበቅ  በሚያደርጉት ልማዳዊ ክወና ነው፡፡ ይህም ወይባ ጭስ ከምትታጠነዋ ሴት አልፎ በእሷ ሙቀትና ላብ የመታጠን ክልከላው ያለባቸውን ወንዶች ከተለያዩ  በሽታዎች ምሳሌ እንደ ጉንፋን ፣ወባ ፣ምች ፣ እራስምታት ፣ታይፎይድና ታይፈስ የመሳሰሉ በላብ መልክ ሊወጡ የሚችሉ በሽታዎችን ፈውስ እንዲያገኙ ከታጠኑ ሴቶች ጋር ሙቀታቸው ሳይጠፋና ላባቸው ሳይደርቅ ፈጥኖ አብሮ በመተኛት ፈውስን ያገኙበታል ፡፡ይህ የፈውስ ልማድ ከታጣኟ አልፎ ሌላ ታማሚን መፈወሻ ጭምር የሚያገለግል በመሆኑ ለዘመናት  ከማህበረሰቡ ጋር እጅግ የቀረበና የጠበቀ ቁርኝት አለው፡፡ ይህን አስመልክቶ (አቶ ሃሰን ሙሃመድ ፣ ቡድን ውይይት ፣ 2010) እንደሚከተለው ገልጸውታል፡-

> *መልሆ(ወይባ) እጅግ ስለሚያልብ በሽታ ያወጣል ሴት መልሆውን ቆለዲውን ፣ምስርቹን ፣አድርጋ ቦለቅያ ከገባች እንኳን ለራሷ ጤና ለባሏም ትተርፋለይ[ትተርፋለች] ፡፡ ወባ ሲይዘን እሷ ሞቃ ጭሱ እፍን እንዳለ ከነላቧ  ወንዱን በጉንፏ[28] አስገብታ አቅፋው ስትተኛ አብሮ ላቡ ተንቆርቁሮ ከወባው ይሽራል ፓራስታሞል የምንውጠው እንዲያልበን*

*[28]<< ጉንፍ›› ማለት በተለበሰ ልብስ ስር ወይም በጉያ ማት ሲሆን ወይባ ጭስ የታጠነች ሴት አንድን  የታመመ ወንድ በተጀቦነችበት ከሌ ወይም ብርድ ልብስ ስር አስገብታ ብታቅፈውና ብትተኛ  እሷ የሞቀችው ወይባ ጭስ ሙቀትና የእሷ ሰውነት ግለት እሱን አብሮ በማላብ ከበሽታው እንዲፈወስ ያደርገዋል ተብሎ ይታመናል ፡፡*

*አይደል ከሷ የምናገኘው ሙቀትና ላብ እኛን አብሮ ስለሚያልበን የተቆራኘንን በሽታ ያወጣልናል፡፡* በማለት የወይባ ጭስ እጥነት የሚያስገኘውን ፈውስ ያስረዳሉ፡፡

### 5.6.1.1.3. የሰውነት ጠረንን ለመቀየር

የሰው ልጅ በሰውነቱ ላይ ባሉ ቀዳዳዎች አላስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በላብ መልክ ያስወጣል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚወጡ ፈሳሶች በሽታዎችን ከማስተላለፍ በተጨማሪ ለአፍንጫ ሚከብዱ መመጥፎ ጠረን ያወጣሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ያሉ ሽታዎችን በማሶገድ ንጽህናን ለመጠበቅ ከመታጠብ ጀምሮ በርካታ ጠረን የሚቀይሩ ሽቶዎችንና መሰል ነገሮችን መጠቀም የተለመደነው፡፡ በመሆኑም በኬሚሴ ማህበረሰብ ዘንድ የወይባ ከላይ ከተጠቀሱት ችግሮች መፍትሄን ከማስገኘት ባለፈ ለተለያዩ መጥፎ ጠረን አምጪ ተህዋስያን ለመከላከያነት ይጠቅማል፡፡ በመሆኑም ሴቶች በላብ አማካኝነት በሰውነታቸው ላይ የሚፈጠር መጥፎ ጠረንን የወይባ ጭስ በመታጠን ከሰውነታቸው የሚወጣው ላብ ጥሩ ሽታን እንዲይዝ በማድረግ የመልካም መዓዛ ባለቤት እንዲሆኑ ይረዳል፡፡

በመሆኑም የወይባ ጭስን የሚታጠኑ ሴቶች ከሌሎች ጠቀሜታዎች ባሻገር ለሽታ ማጣጣም ተግባር ይጠቀሙበታል ፡፡ ወይባ ጭስ የአራስን ገላ ከማጠንከር ባለፈ በአራስነት ወቅት ያሉ ጠረኖችን ለመቀየር ይውላል፡፡ የአራስ ክፍል ንፋስ እንዳይገባው በሚል ተጋርዶ አየርና ብርሃን እንደልብ የሌለበት በመሆኑ ህጻኑና እናቲቱ ከሚቀቡት ላጋ ቅቤና ከሚቀርበው የምግብ ሽታ ጋር ተዳምሮ አየሩ የታፈነ ይሆናል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚፈጥረውን መጥፎ የአራስ ቤት ጠረን ወይባ ጭስን በመሞቅ ፣የአራሷንና የህጻኑ(ኗ)ን ልብስ በማጠን ለአፍንጨ የሚከብዱ ሽታዎች እንዲጠፉ ይደረጋል ፡፡ በተጨማሪም ወተትና ቅቤ የሚቀመጥባቸውን እንደ ጮጮ፣ ቅልና ባሊ የመሳሰሉ የቤት ውስጥቁሶች ይታጠኑበታል ፡፡ በዚህም ቁሶቹ ረጅም ጊዜ ወተት ወይም ቅቤ ይዘው ከመቀመጣቸው የተነሳ የሚያመጡትን መጥፎ ጠረን በጥሩ ሽታ በመቀየር ምግቦቹ ለጤና ተስማሚና መልካም ጠረን ያለቸው እንዲሆኑ ያስችላል ፡፡

ወይባ ለአፍንጫ የሚስብ ጠረን የሚያስገኝ በመሆኑ ተቀባይነቱ ከሴቶቹ በላይ በወንዶቹም እንደሚንጸባረቅ ያነጋገርኳቸው ሰዎች አጫውተውኛል ፡፡ አባወራ ማታ እቤቱ ሲገባ ባለቤቱ ጭስ መግባቷን ሚያረጋግጠው ቤቱ ውስጥ በሚቀበለው የወይባ ጭስ ሽታ ነው ፡፡ ይህ ሽታ የተጠቃሚዋን ጠረን ከመቀየር አልፎ በቤት ውስጥ ያሉ መጥፎ ጠረኖችን ለአፍንጫ በሚመች መልኩ በመቀየር ምቹ አካባቢን ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ እንዳይቋረጥ

አባወራው ወይባ በመግዛትና በመፍለጥ እንዲሁም ሚስቱን በማበረታታት ድርሻውን ይወጣል ። ሴቷም አዘውትራ ጭስ በመግባት መልካም መዓዛ እንዲኖራት፣ በትዳሯና በምትኖርበት አካባቢ ከበሬታና ውዴታን ለማትረፍ፣ የተሸለ ማህበራዊ ቦታን ለማግኝት ማህበረሰቡ ሴቶች እንዲሆኑ የሚፈልገውን አሟልታ ለመገኝት ዘወትር ትታትራለች።

ወይባ ጭስ መጥፎ ጠረንን በመቀየር መልካም መዓዛ ባለቤት እንደሚያደርግ (ወ/ሮ አስማ ሙሃመድ ቃለመጠይቅ፣ የካቲት 23/ 2010) እንዲህ ይገልጹታል ።

> *ወይባ ገበና ከታች ነው። ሴት ልጅ ብዙ ጉድ አለባት እንኳን ከወንድ ሄዳ እንዲሁ ጠረኗ የማያስጠጋ አለች ። ትጥብጥብ ብለን ለጋ ቅቤያችንን አበስ አበስ ብለን ባለቅያችን የገባን እንደሁ ውጥት ብለን በሳሙናችን ትጥብ ስንለው ጅስማችን ወለል ነው የሚለው። ጭሱ ባከላታችን ገብቷል እያለፍን ይተንጋል[29]። እንደየ የሞቅነው ሳምንት ብንቆይ ጠረናችን አይለውጥም ኀበዞቹማ የመልሆውን ልጫ ውስጡን ገንፊል አድርገው በዚያ ውሃ ውልቅ አድርገው ይታጠባሉ። ነካ ብታደርጊያቸው ጅስማቸው ያዳልጣል፣ መአዛቸው ከሩቅ ይጣራል።*

*ከላይ የገለጹት ሃሳብ የወይባ ጭስ እጥነት በሴቶች ላይ ለሚፈጠር መጥፎ ጠረን ለማሶገድ እንዲሁም ንጽህናን በመጠበቅ መጥፎ ሽታ የመያመጡ ተህዋስያንን በማጥፋትና የመልካም ጠረን ባቤትነትን በማጎናጸፍ በራስ የመተማመን ስሜት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል አይነተኛ የፈውስ ምንጭ በመሆን እንደሚያገለግም ያሳየናል።*

### 5.6.1.2. ስነ-ልቦናዊ ፈውስ

አዕምሮን የሚያጨናንቁ ከባድ ስራዎች ለአካለዊ ሁኔታ መዛልና መድከም ይዳርጋሉ። በተጨማሪም ድካም/ውጥረት/ በመፍጠር አምሮን ይረብሻሉ። ሰዎች ከነዚህ የአካልና የአምሮ ድካም የሚያርፉባቸው፣ መንፈሳቸውን ለማረጋጋትና አካላቸውን ዘና ለማድረግ የሚጠቀሙባቸው ባህላዊ መንገዶች አሏቸው። ከነዚህም ውስጥ አንዱ በጭስ መታጠን ነው። በመሆኑም በኬሚሴ ማህበሰብ ወይባ ጭስ አዕምሮ ማደሻና እረፍት መውሰጃ ነው። ሴቶች ሲባክኑበት ከሚውሉት ተግባራቸው ሲመለሱ አረፍ ብለው እራሳቸውን የሚያዳምጡበትና ወደ ህሊናቸው የሚመለሱበት ሰአታቸው በመሆኑ የአዕምሮ ማደሻ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህን

[29] ‹‹ ይተንጋል ›› ማለት በጣም ይሸታል ፣ ሽታው በጣም የገነነው ማለት ነው።

አሰመልክቶ (ወ/ሮ ሶፍያ ትዕዛዙ ቃለ መጠይቅ የካቲት 20/2010 ዓ.ም) እንደሚከተለው ገልጸውታል፡-

> በእኛ ባህል ቦለቅያ የሴት ማረፊያ ነው፡፡ ጮራ ሳትፈነጥቅ የተነሳን እንለፋለን ማረፍ የለም እኔን እንደምታይኝ ሱብሂ[30] የተነሳሁ ነኝ ለልጆች ቁርስብየ ምሳ ሰርቸ እዚህ ደግሞ ይህን ስሸጥ እውላለሁ፡፡ የሚሸጡትን ምግብ ማለታቸው ነው እማርፈው ማታ ቦለቅያየ ላይ ሰቀመጥ ነው ቀልብ ይሰበስባል ፡፡ ውስጤን የማዳምጠው በዚያ ሰዓት ነው፡፡ ሰውነት ስለሚያዘና ውስጥሽ ሰላም ያገኛል፡፡ድካም ይለቃል የሰላም እንቅልፍ ይተኛል ፣ መንፈስሽ ይታደሳል ፣ጭስ ካልተገባ አካልሽ ቢተኛም ጭንቅላትሽ አይተኛም፡፡

በማለት የወይባ ጭስ የሚያስገኘውን አዕምሮአዊ እረፍት ያሰረዳሉ፡፡ በተጨማሪም የወይባ ጭስ እጥነት ንጽህናቸውን በመጠበቅና ከተለዩ በሽታዎች ፈውስን ማግኘት የእለት ከእለት ኑሯቸውን እንዲመሩና መልካም ማህበራዊ ግንኑነት እንዲያገኙ በማድረግና በራስ በመተማመን ስሜት በመያዝ ስለልቦናዊ እርካታን የሚጎናጸፈበት ተግባር ነው፡፡

### 5.6.1.3. ውልደትን ማፋጠን

ብልትን በጭስ የማጠን ስርአት ሙቀትን ወደ ማህጸን የማስገባት ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም የተለያዩ እጾችን አንድ ላይ በመጨመርና በመታጠን ከውልደት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ችግሮችን ለማከምና መልሶ ለማዘጋጀት ይውላሉ፡፡ ውልደት በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ከማይቀሩ ሄደቶች አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም የወይባ ዛፍን ተጠቅመው ውልደትን ማፋጠን የሚችሉበትን የማከም ዘዴ በተለያዩ አካባቢዎች ዘንድ ይስተዋላል፡፡ በመሆኑም ጭስ የመታጠን ተግባር የወላድን ሰውነት ለመንከባከብና ፈሳሾችን ለማድረቅ ማህጸንና ብልትን ለማፍታታት /ለማላላት/ እንዲሁም ለዳግም ውልደት በማዘጋጀት ይጠቅማል፡፡ በመሆኑምወይባ ጭስ ከሴቶች አልፎ የወንዶችንም ስነ ልቦና የገዛ በመሆኑ ወይባ እንጨትን ከማሳ ቆርጦ ወይም ገዝቶ ፈልጦ በማቅረብ ባለቤቱ ዘወትር እንድትሞቅና ለፍቅር ጨዋታ ምቹ እንድትሆን በማድረግ እጅግ አስደሳች ፍቅር ጊዜን በማሳለፍ የተለየ እርካታ ያገኙበታል፡፡ መረጃ አቀባዮች እንደገለጹልኝ ወይባ ጭስ የሴቶችን ብልት በማጥበብ ለፍቅር ጨዋታ የተመቹ እንዲሆኑ በማድረግ ለጾታዊ ግንኙነት በማነሳሳት ለወንዶች አዕምሮአዊ እርካታን በመለገስ ውልደት

*[30] ‹‹ ሱብሂ›› የሚለው ቃል ከአረብኛ የተወሰደ ሲሆን ትርጉሙም ማለዳ ፣ በጠዋት ማለት ነው ፡፡*

እንዲፋጠን ያደርጋል፡፡ ወይባ  የምትሞቅ ሴት ጋር ጾታዊ ግንኙነት የሚያደርግ ወንድ ሁል ጊዜ  ከልጃገረድ ጋር የተኛ ያህል ይሰማዋል፡፡

አብዝቶም ለፍቅር ጨዋታ ይነሳሳል፡፡ በኬሚሴ ማህበረሰብ የወይባ ጭስ እጥነት በሴቶች በኩልም በእርግዝና እና በወሊድ ወቅት ያሉ የሴትነት ጣጣዎችን በማስወገድ እንደገና ስሜትን በማነሳሳት ለመራባት የማመቻቸት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ አቶ ኑራን የቡድን ውይይት መጋቢት 9/2010 ዓ.ም)  ‹‹በውሃ ብቻ ታጥባ ግንኙነት የምታደርግ ሴትና ጭስ የሞቀች ሴት አንድ አይደሉም ጭስ የሞቀች ሴት ወላሂ ሁልጊዜ እንደ ቢክራ[31] ናት፡፡ ንጽህናዋን ጅስሟ ይናገራል፡፡  የተወለወለ ቤት የገባና ያልተጠረገ ቤት የገባ እኩል ደስታ አለው እንዴ? እንደዚያ አድርገሽ ያዥው ጭስ ያልገባች ሴትን  አንድ ቀን ብትተኝ ደግመሽ አትተኛትም››፡፡ በማለት ይገልጹታል፡፡

ወይባ ከዚህም አልፎ መረጃ አቀባዮች እንደጠቆሙኝ አንድ ልጃገረድ ለመጀመሪያ ጊዜ ግንኙነት አድርጋ ህን ከተገሰሰ በኂላ ሌላጊዜ ግንኙነት ሳታደርግ በተከታታይ ለአስራ አምስትቀን ጭስ ብትሞቅ የተቀረጠው ስጋው ተገናኝቶ ብልቷ መልሶ ስለሚኮማተርና ስለሚጠብ  መልሳ ህግ እንዳላት ትሆናለች፡፡ ይህን ሁኔታም በእናቶቻቸው ጊዜ ሳይታሰብ  የታጨች ልጅ በሌላ ስትደፈርባቸው ላለመዋረድ ሲጠቀሙበት የቆዩ ልማድ መሆኑን  አጫውተውኛል ፡፡

ወይባ ጭስ ለሴት ልጅ ትዳሯ የጸና  ደስተኛ የፍቅር ህይወት እንዲኖራት ያደርጋል፡፡ ወይባ በባህሪው እንደተገለጸው አመቱን ሙሉ ቅጠሉን የማያረግፍ ፣እንጨቱ ተቆርጦ ለረጅም ጊዜ ቢቀመጥም የማይደርቅ ፣ቅርንጫፈ ብዙ ዛፍ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ዛፍ እንጨት ጭስ በመታጠን የሴት ልጅ  እንደ ዛፉ ትለመልማለች ፣ማህጸኗን ለጾታዊ ግንኙነት ምቹ በማድረግ ውልደትን  ለማፋጠን ድርሻው ሰፊ ነው፡፡

በዚህ ማህበረሰብ  ሴት የሚስትነት ወግ የሚታይባት ወይባ ጭስ የምትሞቅ  ከሆነ ነው፡፡ በለቅያ የምትገባ ሴት ከትዳር አጋሯ ጋር በተለያዩ ምክንያቶች ቢጋጬም ለመለያየት አይደርሱም (ወ/ሮ ፎዚያ ዑመር፣ የቡድን ውይት መጋቢት 9/2010 ዓ.ም) ‹‹  ወይባ በኬሚሴ የትዳራችን መሰረት ነው ፡፡ በኑሯችን ውስጥ ሌላ ነገር ምን ጎደሎ ቢኖረን ጭስ ከገባን እያስተካከለ ይይዘናል እንጅ  ባላችን  አይፈታንም ፡፡ ካልሞቅን ግን ምንተደፍተን እየሰራን ብናበላው ለመጣላት ሰበብ ያበዛል፡፡ ለማባረር አይኑን አያሽም››:: ይህ የሚያሳየን የወይባ ጭስ መታጠን የሴቶችን ብልት ለጾታዊ ግንኙነት የተመቻቸ በማድረግ፣ ወንዶች ለፍቅር መኻታ

[31] ‹‹ቢክራ›› የሚለው ቃል የአረብኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ልጃገረድ ማለት ነው፡ወይባ  የምትታጠን ሴት ሰውነቷ ለባልዋ ሁል ጊዜ እን ደልጃገረድ ሰውነት እንደሚሆንለት ይታመናል ፡፡

እንዲወዱት በማድረግ ና ሴቶችን ለጾታዊ ግንኙነት በማነሳሳት ውልደትን ለማፋጠን እና ለመጨመር እንደሚውል ያሳየናል ፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# ማጠቃለያና ይሁንታ

## 6.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር ውስጥ ካሉት አምስት ወረዳዎች እና ሁለት ከተማ አስተዳደሮች አንዷ በሆነችው ኬሚሴ ከተማ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በኬሚሴ ከተማ የወይባ ጭስ አዘገጃጀት፣ አጠቃቀምና የጤና ፋይዳን መርምሮ ማሳየት ዋና አላማ አድርጎ የተነሳ ሲሆን የወይባ ጭስ የእጥነት ሥርዓት የሚከወንባቸውን አጋጣሚዎች መመርመር ፣ እጥነቱ ለአካል፣ ለመንፈስና ለህሊና የሚሰጠውን ጥቅም ማሳየት፣ የወይባ ጭስን ለመታጠን የሚውሉ ቁሶችን ተምሳሌታዊ ውክልና ማሳየት የሚሉ ዝርዝር አላማዎችም አሉት፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ቀዳማይና ካልአይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ተጠቅሟል፡፡ በመሆኑም በሶስት ተፈጥሯዊ መቸቶች ላይ በመገኘት ምልከታ ተደርጓል፡፡ ስለጭስ መታጠን ልማዱ ጥልቅ ግንዛቤ ካላቸውና የልማዱ ተጠቃሚ ከሆኑ መረጃ ሰጭዎች በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የተገኙ መረጃዎችም ተግባራዊ ንድፈሃሳብ በመጠቀም በገለጻ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ የወይባ ጭስ እጥነትን ለማከናወን የሚያስፈልጉ የወይባ እንጨት ፣ በለቅያ፣ ለጋ ቅቤ፣ ከሌ የመሳሰሉ ቁሶች ከጭሱ ጋር ያላቸውን ዝምድና ና ተምሳሌታዊ ውክልና ታይቶበታል፡፡ በመሆኑም የወይባ እንጨት ዘርን የማብዛትና የመተካት፣ አካልን የሚያሳምር፣ሰውነትን የሚያደረጅ ፣ፈውስና የጥንከሬ ተምሌት ያለው ሲሆን በለቅያ በማህበረሰቡ የማህበራዊ ደረጃ መለኪያ በመሆኑ ሴት በበለቅያዋ ትመሰላለች በለቅያዋ በጭስ የጠቆረና የደረጀ ከሆነ የታጣኟ ሰውነትም እንደዚያ ይደረጃልተብሎ ይታሰባል ፡፡ ለጋ ቅቤ በማህበረሰቡ የአዲስነት ፣ የልጅነት የንጽህነት ተምሳሌት ሲኖረው ጀንዲ(ከሌ) የትንካሬና የዘላቂነት ተምሳሌት እንዳለው ጥናቱ አስገኝቷል ፡፡

የወይባ ጭስ ለእጥነት ለማዋል ትል ያልወጋውን እንጨት ቆርጦ ወይም ከገበያ ገዝቶ ተመርጎና ተለቅልቆ በተዘጀጋጀ በለቅያ ልክ ፈልጦና ከርክሞ ለእጥነት እስከ ሚውል ድረስ ያሉ አዘገጃጀቶች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ የአሚሚቅ ስርአቱም በሶስት አጋጣሚዎች የሚከወን ነው፡፡ እነዚህም የጫጉላ ቤት፣ የአራስ ቤት እና የአዘቦት አጋጣሚዎች ናቸው፡፡ በነዚህ አጋጣሚዎች ጭስ በመሞቅ ስርአቱ የሚከወኑ የአለባበስ ፣የአመጋገብ፣ የቅቤ መለቅለቅ ባህላዊ ስርአቶች

ተቃኝተዋል። በነዚህ አጋጣሚዎች ወይባ ጭስ የሚሞቁ ሴቶች ጾታዊ ግንኙነት የጀመሩ መሆን እንዳለባቸውም ጥናቱ አሳይቷል ።

በኬሚሴ ማህበረሰብ የወይባ ጭስ የመታጠን ፋይዳ በዋናነት አካላዊና ስነልቦዊ ጤንነትን መጠበቂያ እንደሚውል ናውልደትን ማፋጠኛ /fertility/ እንደሚጠቀሙበት ጥናቱ አስገኝቷል። በዚህም በአካዊ ፈውሱ ጥንካሬና ብርታትን መፍጠር፣ መጥፎጠረኖችን በመቀየር ለጤና ተስማሚ ማድረግ ፣ አላስፈላጊ ፈሳሾችን በማድረቅ የማህጸን ጤንነትን መጠበቅ ። በጤንነት መጠበቂያነቱም በአካላዊ ጤንነት ሰውነትን ለማጠንከርና ከሰውነት የሚወጡ አላስፈላጊ ፈሳሾችን በማድረቅ ለማከም ሲጠቅም ማህጸንን ከተለያዩ ኢንፌክሽኖች ለማዳንና ለመከላከል የሚውል መሆኑን አሳይቷል። ሴቶች በማህበራዊ ኑሯቸውና የትዳር ሕይወታቸው የቀና እንዲሆን ስነ-ልቦዊ ጤንነትን እንደሚያስገኝ ተመላክቷል።ስነ ልቦናዊ ህክምናው ደግሞ በወይባ ተጠቃሚዋ ሴት ብቻ ሳይሆን በተጠቃሚዋ ባል ላይ ሁሉ መሆኑን አይተናል። ውልደትን በማፋጠን ፋይዳው የሴትን ልጅ የመራቢ አካላት ጤንነት በመጠበቅ እና ከተለያዩ በሽታዎች በመፈወስ እዲሁም ለጾታዊ ግንኙነት በማነሳሳትና በማላመድ ውልደትን የሚያፋጥን መሆኑን ጥናቱ አስገኝቷል። በተጨማሪም ወይባ የምትሞቅ ሴት በማህበረሰቡ ማህበራዊ ደረጃዋ ከፍያለና የሴቶች ተምሳሌት ተደርጋ ስትወሰድ ወይባ ጭስ የማትሞቅ ሴት ሰነፍ ፣ጽዳትና ሙያ የሌላት ተደርጋ ከመወሰዷም በላይ ከትዳር አጋሯ ከፍተኛ ነቀፊታ ይደርስባታል። ለትዳሯ መፍረስ ምክንያት እንደሚሆን ጥናቱ አሳይቷል።

## 6.2. ይሁንታ

የኬሚሴ ማህበረሰብ የወይባ ጭስን በመታጠን የተለያዩ ፋዳዎችን የማግኝት ባህል በሌላ ሳይተካ ባህላቸውን ጠብቀው እንዱቆዩ እና ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ ይጠቅማሉ የተባለ ሀሳቦች በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል።

- በጥናቱ በተገኘው መረጃ መሰረት የወይባ ጭስ እጥነት ያለው ዘርፈ ብዙ ጥቅም ከጤና አንጻር ያለው ፋይዳ የጎላ መሆኑን አሳይቷል ። በመሆኑም ይህን ልማድ ዞኑም ሆነ የከተማው ባህል ቱሪዝም ከጤና ቢሮ ጋር በመተባበር በባለሙያዎች በማገዝ ከአስራ ስድስቱ የጤና ፓኬጆች አንዱ ሆኖ ቢያዝ አስቀድሞ በሽታን የመከላከል ፖሊሲውን እውን ያደርጋል እላለሁ።

- በተገኘው መረጃ መሰረት የወይባ ጭስ የመሞቂያ ቁሶች ተምሳሌት ጥልቅ ግንዛቤ ካለመኖር የተነሳ በሌላ እየተተኩ በመሆኑ ባህላዊ ይዘቱን ይዞ እንዲቆይ ወጣቶቹ ስለ ባህላቸው እንዲያውቁ ስልጠናና ትምህርት ቢሰጣቸው መልካም ነው፡፡

- ጥናቱእንዳመላከተው የወይባ ጭስ መታጠን ፋይዳ በዋናነት በማህጸን አካባቢ የሚፈጠሩ ኢንፌክሽኖችን ለማከምና ለመከላከል በሃገር ብሎም በዓለም ደረጃ ለብዙ ሰዎች ህልፈት መንስኤ የሆኑትን እንደ ማህጸን በር ከንሰርና የወገብ መገጣጠሚያ ችግሮች ፈውስ በመሆን የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም በመስኩ የተሰማሩ ምሁራን ልማዱ ያለውን ፋይዳ በትኩረት በማጥናትና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በማበልጸግ ተግባር ላይ እንዲውል ቢደረግ ሰፊ አገራዊ ችግርን ይፈታል እላለሁ፡፡

- የባህል ቱሪዝም ቢሮ የአካባቢውን ባህል ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ማህበረሰቡ ተሳታፊ እንዲሆን የዞኑም ሆነ የከተማው ማስታወቂያ ጽህፈት ቤት በሬዱዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣ፣ መጽሔቶችንና በራሪ ጽሁፍችን በመጠቀም ማህበረሰቡ የወይባ ጭስ እጥነት ልማዱን ለመጠቀምና ለመጠበቅ እንዲነሳ ማነቃቃት ቢችል መልካም ነው እላሁ፡፡

## ዋቢ ጽሑፍ

ሊያ መዝገቡ፤፤ ( 2003)። **በኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ተዋህዶ ቤተ ክርሲቲያን የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ስርአት ክዋኔ**።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ሁለተኛ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ፅሁፍ ። ያልታተመ።

ማርታ እሸቱ ። (2001)። **ወይባ ባህላዊ ሴቶች መዋቢያ በወሎና በአዲስ አበባ**። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ሁለተኛ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ፅሁፍ ። ያልታተመ።

ሰይድ ይማም። (2002) ።**በኬሚሴ ከተማ ዙሪያ ባሉ ገጠር ቀበሌዎች የወጣት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ ፎክሎራዊ ፋይዳ** ። አዱስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል 2ኛድግሪ ማሚያ የቀረበ ጽሁፍ።ያልታተመ።

ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ። (2009) ። **በአማራ ብሄራዊ ክልል በደቡብ ጎንደር፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ እንዲሁም በኦሮሞ ብሄረሰብ ዞኖች ላይ የተመዘገቡ ኢንታጀብል ባህላዊ ቅርሶች**።ቅጽ 8፣ ክፍል ሁለት፣አዲስ አበባ ።አሳታሚ አልተገለጸም።

ዐብዩ አስማማው፡፡ (2000)፡፡ **በአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና ማጌጫ ቁሶች በአማራ ክልል ደቡብ ወሎዞን አርጎባ ልዩ ወረዳ**፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍልየ ሁለተኛ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ፅሁፍ ፡፡ ያልታተመ፡፡

የኬሚሴ ከተማ አስተዳደር። ( 2006) ።አርሂቡ መጽሄት፤፡ **የከተሞች ቀን በዓል ልዩ እትም**። ብርሃናና ሰላምማተሚያ ቤት።

---------------- ። (2008) **በጀት ዓመት ስታስቲካዊ የመረጃ መፅሂት**:: *ያልታተመ።*

-----------------።(2007)።*ባህልቱሪዝም* **ጽ/ቤት።ዳሰሳጥናት።ኬሚሲ፣**2007። *ያልታተመ።*

-----------------።(2007 )።*ገንዘብና ኢኮኖሚ* **ጽ/ቤት።የተዘጋጀ ሰነድ።** *ያልታተመ።*

*ያለው እንዳወቀ።* (1998) ። **የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር።**ንግድ

ማተሚያ ድርጅት።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። (1948) ።***መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ።*** አዲስ

አበባ።አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ፈቃደ አዘዘ። (1991) ። **የስነ ቃሌ መምሪያ።** አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ዴርጅት።

Bascom, William R. (1954). "Four Functions of Folklore." *Journal of American Folklore.*67:333-349.

Bauman, Richard. (1983). "*The Field Study of Folklore in Context.*" **In Handbook of American Folklore,** Richard Dorson, Bloomington: Indian University Press.

Ben- Amos, Dan.(1993)." Context in Context" . **Western Folklore** Vol.52, No, 2/4, in Theorizing Folklore; Toward New Perspective on the Politics of Culture.pp. 209-226

Best, J. W.(1981). **Research in Education** .New Delhi; Prentice Hall of India Private Limited.

Blum, N. B. (2007). "Benifical effect of sauna bathing for heart failer patients ." *clinical cardiology vol. 2*, 29.

Brown, Bobi, (2002).**Beauty Evalution.**New York harper Collins publishers.

Burkil .H. M. (2004:418).**The Useful Plants of West Tropical Africa**.
Publisher Royal Botanic Gardens;Kew.

David, Gray E .(2004).**Doing Research in the Real World**. London, SAGE
Publications Ltd.

Dorson.Richard. M. M (E.D). (1972). **Folklore and Folk life: An Introduciton.**
Chicago: The University of Chicago Prees.

Elizabeth, Willett.(1897). "Vagina steam." **The New york medical journal**.Vol.65 pp.134-136

Goldstein, Kenneth S.1964. **A Guide for Field Work in Folklore**. Hatboro
Pennsylvania: the American Folklor in Society.

Kapchan, Deborah A. (1995). "Performance ." **The Journal of American Folklore** .Vol.108, No. 430, pp. 479-508.

Kothari, C. R. (2004) .**Research Methodology: Methods & Techniques**.
2nd ed. India, New International (P) Limited, Publishers

LockWood, R.Yvonne.( 1981). "The sauna." **An Expression of Finnish-American Idenity**.Madison, university of Wisconsin press.

Lopatin, I. A. (1960). "Origin of the Native American Steam Bath."
**American Anthropologist**, New Series, , 977-993.

Mesfin Tadesse.(1997). **Flora of Ethiopia and Eritrea.** Volume 6 Publisher:
Uppsala university Paperback, #24399 | ISBN-13: 9789197128544.

Okpewho, Isidore. (1992.). **African Oral Literature** : **Backgrounds,**

**Characters And continuity.** Bloomington: Indiana University Press,

Read, Margaret. (1966). **Cultural health and disease**.London tavistock Publications limited.

Scoot, Vandaerstoep W. and Deirdre, Johnston D. (2009). ***Research Method For Every Day Life.***Jossy Bass, Sanfransisco.

Sims, Martha C. and Stephens, Martine.( 2005). **Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Tradition.** Logan: Utah State University Press,

WHO. ( 2001). **Legal Status of Traditional Medicine and Complementary Alternative Medicine**. AWorld Wide Review. Geneva.

## አባሪ

.አባሪ1 **ቁልፍ መረጃ አቀባዩች ዝርዝር**

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዩ ስም | ጾታ | ዕድሜ | አድራሻ | እምነት | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ አስማ ሙሃመድ | ሴ | 90 | 03 | ሙስሊም | የቤት እመቤት |
| 2 | ወ/ሮ ፋጡማ ይማም | ሴ | 35 | 03 | ሙስሊም | የቤት እመቤት |
| 3 | ወ/ሮ ማንጠግቦሽ ሙሃመድ | ሴ | 20 | 07 | ሙስሊም | የቤት እመቤት |
| 4 | ወ/ሮ አክዩ አህመድ | ሴ | 30 | 07 | ሙስሊም | የቤት እመቤት |
| 5 | ወ/ሮ ሶፍያትዕዛዙ | ሴ | 25 | 03 | ሙስሊም | ነጋዴ |
| 6 | ወ/ሮ የሽጥላ አመዴ | ሴ | 45 | 06 | ኦርቶዶክስ | የመንግስት |
| 7 | ወ/ሮ ፎዚያ ዑመር | ሴ | 34 | 06 | ሙስሊም | ነጋዴ |
| 8 | ወ/ሮ አይናለም ሰይድ | ሴ | 26 | 06 | ሙስሊም | አማተር ድምጻዊ |
| 9 | ወ/ሮ ጦይባ ሙሃመድ | ሴ | 26 | 06 | ሙስሊም | የመንግስት |
| 10 | ወ/ሮ ፋጦ እንድሪስ | ሴ | 45 | 07 | ሙስሊም | የቤት እመቤት |
| 11 | አቶ አብዱ ሰይድ | ወ | 60 | 06 | ሙስሊም | ጡረተኛ |
| 12 | አቶ ሁሴን ኢብራሂም | ወ | 46 | 03 | ሙስሊም | ገበሬ |
| 13 | አቶ አብዱ ሙሂ | ወ | 51 | 07 | ሙስሊም | ነጋዴ |
| 14 | አቶ ኑራን ሙሃመድ | ወ | 47 | 03 | ሙስሊም | ነጋዴ |

አባሪ 2 ንዑስ መረጃ አቀባዩች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዩ ስም | ጾታ | ዕድሜ | አድራሻ | እምነት | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ ፋጤ እንድሪስ | ሴ | 47 | ከርጳሜ | ሙስሊም | የመንግስት |
| 2 | ወ/ሮ ሽቶ ነጋ | ሴ | 57 | 03 | ኦርቶዶክ | ነጋዴ |
| 3 | ወ/ሮ አሚናት ሁሴን | ሴ | 38 | 06 | ሙስሊም | ነጋዴ |
| 4 | ወ/ሮ አሚናት መሂ | ሴ | 33 | 06 | ሙስሊም | ነጋዴ |
| 5 | ወ/ሮ ሰአዳ መሃመድ | ሴ | 37 | 06 | ሙስሊም | ነጋዴ |
| 6 | አቶ አህመድ ሁሴን | ወ | 22 | 07 | ሙስሊም | ነጋዴ |
| 7 | አቶ ግሩም ተሰማ | ወ | 24 | 03 | ኦርቶዶክስ | የመንግስት |
| 8 | ወ/ሮ ሃዋ ሙሃመድ | ሴ | 70 | 03 | ሙስሊም | የቤት እመቤት |

አባሪዎችአባሪ1. የምርምር ጥያቄዎች

ሀ.<<በኬሚሴ ከተማ የወይባ ጭስ አዘገጃጀት  አጠቃቀምና የጤና ፋይዳ >> በሚል ርዕስ ለሚሰራ ጥናት ከጭስ ተጠቃሚሴቶችበቃለ መጠይቅመረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጁ መነሻ ጥያቄዎች

**የመረጃ ሰጪዎች ግላዊ መረጃዎች**

የመረጃ ሰጪ ስም ፡ ----------

ዕድሜ ፡ ----------

ስራ፡ ----------

ፆታ፡ ----------

ሃይማኖት፡ ----------

የጋብቻ ሁኔታ፡ ----------

የትምህርት ሁኔታ፡ ----------

1. የወይባ ጭስ ምንድን ነው?
2. የወይባ ጭስ የሚሞቁ እነማን ናቸው?
3. ወይባ ጭስ መቸ ይሞቃል?
4. ወይባ ጭስ ሲሞቅ ምግብ ይበላል? ምን አይት ምግብ?
5. ወይባ ጭስ መሞቁ ለምን ይጠቅማል?
6. ወይባ ጭስ መታጠን የሚከለከሉ ሴቶች አሉ? ለምን ?
7. ወይባ ጭስ የምትሞቅና በማትሞቅ ሴት መካከል ልዩነት አለ?
8. ወይባ ጭስ ተጠቃሚ በመሆንዎ ምን ይሰማዎታል?
9. ወይባ እንጨት ከየት ይገኛል?
10. ወይባ ጭስ እንዴት ይዘጋጃል? ማን ያዘጋጀዋል?
11. ባለቤትዎ እርስዎ ወይባ በመሞቅዎ ምን አስተያት አላቸው?
12. .ይህ ልማድ መቸ ነው የተጀመረው?
13. ለመሞቅ ምን አይነት ቁስ ያስፈልጋል? እነዚህ ቁሶች ለምን ተመረጡ?

ለ. <<በኬሚሴ ከተማ የወይባ ጭስ አዘገጃጀት  አጠቃቀምና የጤና ፋይዳ >> በሚል ርዕስ ለሚሰራ ጥናት ከሴት ሙሽሮች በቃለ መጠይቅመረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጁ መነሻ ጥያቄዎች

**የመረጃ ሰጪዎች ግላዊ መረጃዎች**

**የመረጃ ሰጪ ስም : ----------**

**ዕድሜ : ----------**

ስራ፡ ----------

ፆታ፡ ----------

ሃይማኖት፡ ----------

የጋብቻ ሁኔታ፡ ----------

የትምህርት ሁኔታ፡ ----------

1. ወይባ መሞቅ የጀመሩት መቸ ነው? ለምን ከዚህ በፊት አልጀመሩም?
2. ማን ነው የሚያሞቅዎት?
3. ሲሞቁ ምን ተሰማዎት?
4. ወይባ ከመሞቅዎ በፊትና መሞቅ ከጀመሩ በኋላ በእርስዎ ላይ ያዩት ለውጥ አለ?
5. ወይባው በማን ይዘጋጃል?

ሐ<<በኬሚሴ ከተማ የወይባ ጭስ አዘገጃጀት  አጠቃቀምና የጤና ፋይዳ >> በሚል ርዕስ ለሚሰራ ጥናት ከሙሽራው አንደኛ ሚዜ ( ለባሪያው) በቃለ መጠይቅመረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጁ መነሻ ጥያቄዎች

**የመረጃ ሰጪዎች ግላዊ መረጃዎች**

**የመረጃ ሰጪ ስም : ----------**

**ዕድሜ : ----------**

ስራ፡ ----------

ፆታ፡ ----------

ሃይማኖት፡ ----------

የጋብቻ ሁኔታ፡ ----------

የትምህርት ሁኔታ፡ ----------

1. የእርስዎ የስራ ድርሻ ምንድን ነው?
2. ሎሽሪትን ወይባ የሚያሞቁት ለምን እንዲጠቅማት ነው?
3. የጭስ መሞቂያቀኑ መቸ ይጀምራል?
4. አልሞቅም ብትል ምን ያደርጋሉ?
5. እስካሁን ምን ያህል ሙሽሮች አሙቀዋል?

መ. <<በኬሚሴ ከተማ የወይባ ጭስ አዘገጃጀት  አጠቃቀምና የጤና ፋይዳ >> በሚል ርዕስ ለሚሰራ ጥናት ከጭስ ተጠቃሚሴቶች ባሎች /ወንዶች/ በቃለ መጠይቅመረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጁ መነሻ ጥያቄዎች

**የመረጃ ሰጪዎች ግላዊ መረጃዎች**

የመረጃ ሰጪ ስም ፡ ----------

ዕድሜ ፡ ----------

ስራ፡ ----------

ፆታ፡ ----------

ሃይማኖት፡ ----------

የጋብቻ ሁኔታ፡ ----------

የትምህርት ሁኔታ፡ ----------

1. ባለቤትዎ  ወይባ ጭስ ይሞቃሉ?
2. ለምን ጥቅም ነው የሚሞቁት ?
3. ባለቤትዎ ጭስ በመሞቋ እርስዎ ምን ይሰማዎታል? ባይሞቁስ?
4. የእርዎ ድርሻ ምንድን ነው?
5. ባለቤትዎ ጭስመሞቅ የጀመሩት መቸ ነው?

ሠ. <<በኬሚሴ ከተማ የወይባ ጭስ አዘገጃጀት  አጠቃቀምና የጤና ፋይዳ >> በሚል ርዕስ ለሚሰራ ጥናት ከእድሜ ጠገብ አዛውንቶች በቃለ መጠይቅመረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጁ መነሻ ጥያቄዎች

**የመረጃ ሰጪዎች ግላዊ መረጃዎች**

የመረጃ ሰጪ ስም ፡ ----------

ዕድሜ ፡ ----------

ስራ፡ ----------

ፆታ፡ ----------

ሃይማኖት፡ ----------

የጋብቻ ሁኔታ፡ ----------

የትምህርት ሁኔታ፡ ----------

1. ወይባ ምንድን ነው?
2. ወይባጭስ መሞቅ መቸ ነው ተጀመረው በማን?
3. ወይባ ከመታጠን ውጭ ጥቅም አለው? ለምን?
4. ወይባ ጭስ በኬሚሴ ማህበረሰብ እንዴት ይታያል? ለምትሞቅና ለማትሞቅ ሴት ያለው ?አመለካከት ምን ይመስላል ?
5. ወይባ ለጭስነት እንዴት ይጋጃል ?

ረ. <<በኬሚሴ ከተማ የወይባ ጭስ አዘገጃጀት  አጠቃቀምና የጤና ፋይዳ >> በሚል ርዕስ ለሚሰራ ጥናት ከጭስ ተጠቃሚሴቶች ቡድን ውይይት መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጁ መነሻ ጥያቄዎች

ለጭስ ተጠቃሚ ሴቶች የቀረቡ የመወያያ ጥያቄዎች

1. ወይባ እንዴት ይዘጋጃል?
2. ወይባ ጭስ የሚጠቀሙ እነማን ናቸው ለምን?
3. የወይባ ጭስ  አጠቃቀሙ እንዴት ነው?
4. ወይባ ጭስ መቸ መቸ ይሞቃል ?
5. ወይባ በማህበረሰቡ ምን አይነት ቦታ አለው?

ለ ወንዶች የቀረቡ የመወያያ ጥያቄዎች

1. ወይባ ጭስ መሞቅ የሚጀመረው መቸ ነው ለምን?
2. ወይባ ጭስ መሞቅ ምን ጥቅም አለው?
3. ወይባ የምትሞቅና የማትሞቅ ሴትን መለየት ይቻላል? እንዴት?
4. ማህበረሰቡ ወይባ ልትሞቅና ለማትሞቅ ሴት ያለው አመለካት ምን ይመስላል ?
5. በሴቶች ወይባ ጭስ እጥነት ላይ የወንዶች ድርሻ  አላቸው ? ምንድን ነው?

## አባሪ ሁለት ፎቶዎች

### የመስክ ጉዞ





ቀበሌ ሰባት ወደ ጫጉላ ቤት ጉዞ ከመንገድ መሪ ከወ/ሮ አይናም ሰይድ ጋር

## ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታና የቡድን ውይይት

















ከጭስ ተጠቃሚ ሴቶችባሎች ጋር የተደረገ ቡድን ውይይት



ከጭስ ተጠቃሚሴቶች ጋር የተደረገ ቡድን ውይይት



**የለጋቅቤ ገበያ በኬሚሴ**